«ለ50 ዓመቱ ሰቆቃ ክዳን አበጅተን ወደ ኢዩቤሊዩ ዘመን እንድንመጣ እንሻለን»

- ወይዘሮ ሰዋሰው ስለሺ
የትውልድ እናት ለእርቅና ለሰላም ድርጅት ስራ አስኪያጅ



ገጽ 6

ተስፋ ፈንጣቂ የቀደ ህክምና ክፍል

ገጽ 8

ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
81ኛ ዓመት ቁጥር 344 ነሐሴ 14 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## “እናቶች ተረባርበን በጦርነት የሚነግዱ ኃይሎችን ማስቆም አለብን”

- ወይዘሮ ሰዋሰው ስለሺ
የትውልድ እናት ለዕርቅና ለሰላም ድርጅት መሪ


ፎቶ፡- እዮብ ተፈሪ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የትውልድ እናት ለዕርቅና ለሰላም ድርጅት፣ በጦርነት የሚያልቀው የደሃው ልጅ እና ወጣቱ ስለሆነ እናቶች ተረባርበን በጦርነት የሚነግዱ ኃይሎችን ማስቆም አለብን ሲል ገለፀ፡፡

የትውልድ እናት ለዕርቅና ለሰላም ድርጅት መሪ ወይዘሮ ሰዋሰው ስለሺ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ቃለ ምልልስ፤ ለእናት ሽብረክ የማይል ትውልድ ይኖራል የሚል ግምት የለንም፡፡ በመሆኑም በጦርነት የሚያልቀው የደሃው ልጅ እና ወጣቱ ስለሆነ እናቶች ተረባርበን በጦርነት የሚነግዱ ኃይሎችን ማስቆም አለብን ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በምዕራቡ ዓለምና በሌሎች አካባቢዎች ተመሳሳይ የሆኑ የእናቶች ንቅናቄዎች እየተካሄዱ መሆኑን የተናገሩት ወይዘሮ ሰዋሰው፤ በሀገራችን እያንዳንዱ ክልል ውስጥ እና በአንዳንድ አካባቢዎች የሚደረገው ነገር ፖለቲከኞች ለፖለቲካቸው ማስፈፀሚያ ወጣቱን እንደልብ የሚነዱበት አጋጣሚ በማግኘታቸው የሚፈጠር ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን የመሩት ፖለቲከኞች አብዛኞቹ በህይወት እንዳሉ በማንፀሪያነት አንስተው፤ ወጣቶች ግን የእነሱን ዓላማ ለማስፈፀም አልቀዋል ብለዋል፡፡ ለዚህም እናቶች ይህንን ድርጊት ለማስቆም በንቃት መሳተፍና ንቅናቄ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ጠቁመዋል፡፡

«እናቶች ተረባርበን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ

## «ትኩረታችንን አገር መለወጥና የሕዝባችንን ኑሮ ማሻሻል ላይ አድርገን ያለምንም እረፍት እየሰራን ነው»

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ትኩረታችንን አገር መለወጥና የሕዝባችን ኑሮ ማሻሻል ላይ አድርገን ያለምንም እረፍት እየሰራን ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ አስታወቁ፡፡

«ትኩረታችንን አገር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «የሕወሓት ቡድን ለሰላም ድርድሩ እንቅፋት የሆኑ ሃሳቦችን ከማቅረብ አልተቆጠበም»

-ኮማንደር ገብረመስቀል ወልደሚካኤል
የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) አባል

**መኣርግ ገ/እግዚአብሔር**

አዲስ አበባ፡- የሕወሓት ቡድን ስልጣኑን ለማራዘም ሲል የሰላም ድርድርን የሚያደናቅፉ ሃሳቦችን ከማቅረብ አልተቆጠበም፤ ይህ የሚያሳየው ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን ነው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) አባል ኮማንደር ገብረመስቀል ወልደሚካኤል ተናገሩ።

ኮማንደር ገብረመስቀል ለኢ.ፕ.ድ እንደተናገሩት የሕወሓት ቡድን ለሰላም ዝግጁ ነኝ እያለ ነገር ግን ሰላምን በሚያደናቅፉ ሃሳቦች ላይ ተጠምዷል። በአንድ በኩል ለሰላም ዝግጁ ነኝ ሲል በሌላ በኩል ለሰላም ድርድር እንቅፋት የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጧል።

«የሕወሓት ቡድን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል












ከ350 በሚበልጡ የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ እርምጃ መውሰዱን ባለስልጣኑ አስታወቀ
- ጥናት ካካሄደባቸው 10 ሺ የትምህርት ማስረጃዎች 505ቱ ሀሰተኛ ናቸው

ገጽ 4

# ሰው የመሆን ጥጎች

**ሳሙኤል ወንደሰን**

በጎ ፍቃደኝነት ሰዎች ትርፍ ወይም ጥቅም ሳይፈልጉ በራሳቸው ተነሳሽነት ሌሎችን ለማገዝ የሚያከናውኑት ተግባር ነው። ይህን በጎ ተግባር ሰዎች በራሳቸው ፍቃድ ሲያከናውኑ ታዲያ ዘርን፣ ፆታን፣ የቆዳ ቀለምን፣ ሃይማኖትን፣ ቋንቋንና ፖለቲካን መሰረት አድርገው አይደለም።

በዚህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከሚሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ወጣቶች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። እስከ አሁንም በርካታ ወጣቶች በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ውስጥ በመሳተፍ የዜግነት ግዴታቸውን ተወጥተዋል። በዚህም ብዙዎች ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በዚህ የክረምት ወቅት ወጣቶች በስፋት ከሚሳተፉባቸው ጉዳዮች አንዱ ይኸው የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ነው። ወጣቶች በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ ያላቸው ግንዛቤ ከፍ እያለ በመምጣቱም በአገልግሎት የመሳተፍ መጠናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል።

ወጣት ሎሚ ፍቃዱ የምትኖረው አራት ኪሎ አካባቢ ነው። ጠዋት ከ1 ሰዓት እስከ 4 ሰዓት ከሰዓት ከ10 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት በትራፊክ በጎ ፍቃድ ታገለግላለች። እግረኞችና አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብ እንዲከተሉ ለማድረግ ሲሞክሩ ሕግጋቱን የሚያከብሩ እንዳሉ ሁሉ ከበጎ ፍቃደኞቹ ጋር እሰጣ ገባ የሚይዙም አይጠፉም ትላለች።

‹‹የትራፊክ ሥራ በመሥራቴ አንድ ሕይወት እንኳን ባተርፍ ቀላል አይደለም፤›› የምትለው ወጣት ሎሚ፣ ለወደፊት ትራፊክ መሆን እንደምትፈልግ ትናገራለች። የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱን የምትሰጠው መደበኛ ትምህርቷን እስከምትጀምር ቢሆንም በክረምት የእረፍት ጊዜዋ ማኅበረሰቡን በማገልገሏ ደስተኛ ናት።

እንደሷው በበጎ ፈቃደኝነት የክረምት በጎ ፍቃደኛ የሆኑ ከ30 ሺህ በላይ ወጣቶች በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ እያገለገሉ ይገኛሉ። የአዲስ አበባ ወጣቶች ማሕበር ዋና ፀሐፊ አቶ ይሁነኝ መሀመድ እንደሚናገሩት፣ ወጣቶቹ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ባለባቸው አደባባዮችና የመንገደኛ ማቋረጫዎች ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ።

በዘንድሮ ክረምት በከተማዋ ከ30 ሺህ በላይ ወጣቶች በቆሻሻ ማጽዳት፣ በችግኝ ተከላ፣ የትራፊክ ፍሰቱን



ወጣት ሎሚ ፍቃዱ

የተሳለጠ ለማድረግ በማስተባበር፣ በሰላምና ጸጥታ ስራና በመሳሰሉት በጎ ተግባራት መሰማራታቸውን ጠቁመው፤ ይህም የበጎ ተግባር አገልግሎቶች በገንዘብ ሲተመን ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመቱ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ወጣት ማሕበሩ ሀገር ተረካቢ ወጣቶችን ከማፍራት አኳያም በክረምት ወራቱ በቤታቸው የሚገኙ በርካታ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአልባሌ ቦታ እንዳያሳልፉ ከማድረግ በተጨማሪ በገንዘብ የማይተመን የማጠናከሪያ ትምህርት የመስጠት ስራ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን የአደጉ አገራትም የክረምት፣ የበጋ በሚል የራሳቸው የበጎ ፈቃድ ዘመቻዎች እንዳላቸው ያስታወሱት ኃላፊው፤ በቋሚነት ሰውን ለማገዝ ተደራጅተው የሚሰሩ እንዳሉም ገልጸዋል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ አገራትም ብዙ የበጎ አድራጎት ስራ የሚጠይቁ በርካታ ተግባራት መኖራቸውን አብራርተዋል።

የወጣት ማሕበሩ ቀጣይ ትኩረትም በበጎ ፈቃድ ስራ የከተማዋ እና የሀገራችን ሰላምና ጸጥታ ማስጠበቅ፣ የወጣቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እና የለማች አገር ለማድረግ በሚደረገው ሁለተናዊ ጥረት ወጣቱ ጉልህ ተሳታፊ እንዲሆን ማሕበሩ በትኩረት እንደሚሰራም ጠቁመዋል።

ወጣት ናትናኤል ተስፋዬ በጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን፤ “በበጎ ፍቃድ ስራ በመሰማራት ሰዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ከማድረግ በላይ የሚያስደስት ስራ የለም” ይላል።

ወጣቱ እንደሚለው፤ ወጣቶች በሚሰጡት ትራፊክን የማስተናበር ስራ ላይ ችግር የሚፈጥሩ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ለአደጋ የሚያጋልጡ ሰዎች ናቸው።



ወጣት ናትናኤል ተስፋዬ

ነገር ግን ወጣቱ እንዲህ አይነት ሰዎችን ሳይመለከት የበጎ ተግባር ስራውን አጠናክሮ መቀጠል አለበት።

በስራ ቀናት ሰዎች ራሳቸውን ከተሽከርካሪ አደጋ እንዲጠብቁ፣ ግራ ጠርዛቸውን ይዘው እንዲንቀሳቀሱና ዜብራ መንገዶችን ተጠቅመው እንዲያቋርጡ የማስገንዘብ ሥራ እየሰራ መሆኑን ተናግሯል።

ሕብረተሰቡ ራሱን ከትራፊክ አደጋ እንዲከላከል ከማስገንዘብ ባለፈ አሽከርካሪዎች የመንገድ ትራንስፖርት ህግና ሥርአትን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ላይ እንገኛለን ብሏል።

“በበጎ ፈቃድ የሚሰራው ስራ ለራሳችንና ለወገናችን ነው” የሚለው ወጣቱ፤ ሁሉም ለስራው ትብብር ማድረግ እንዳለበት አስረድቷል።

በሌላ በኩል ጎላ ሚካኤል አካባቢ የሚኖረው ብሩክ ነጋሽ ክረምትን የሚያሳልፈው የበጎ ፈቃደኛ መምህር ሆኖ ነው። ይህም ሰዎችን በአዎንታዊ መንገድ እንደረዳና እውነተኛ ለውጥ እንዳመጣ አስችሎኛል ይላል።

ትምህርት የማህበረሰቡ ምሰሶ ነው። የሰው ልጅ ስልጣኔ የተቀረፀው በትምህርት ነው። እድገታችን በተማርነው ላይ የተመሰረተ ነው። ትምህርት እንዴት እንደምንሰራ፣ በአካባቢያችን ካሉ ሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት የምንደርስበትን የእውቀት አለም ቀርጾታል ሲልም ተናግሯል።

በጎ ፈቃደኝነት ስለራስህ የበለጠ እንድታውቅና ከተሰጠህ ውስጥ ትንሽ እንድትመልስ እድል የሚፈጥር ነው። የአንተን ፈለግ ለሚከተሉ ሰዎች የተሻለ ወደፊት የምትፈጥርበት መንገድ ነው። በበጎ ፈቃድ ማስተማር



ወጣት ብሩክ ነጋሽ

አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ኢንቨስትመንት ነው ሲልም ያለውን ጠቀሜታ ተናግሯል።

ወጣቱ እንዳለው፤ በጎ ፈቃደኝነት ማስተማር መልካም ተግባር ብቻ አይደለም። እንደ ህዝብ ማንነታችንን የሚገልጽ መግለጫ ነው። እውቀትን ለማካፈል ብዙ መንገዶች አሉ። ነገር ግን በጣም ጠቃሚ ከሆኑ መንገዶች አንዱ በበጎ ፈቃድ ማስተማር ለአለም የምትሰጡት ስጦታ ነው። በሌሎች ሰዎች አእምሮ ውስጥ የተከልከው ዘር ነው እንዲያድጉ የሚረዳው።

እውቀት ለሁሉም ሰው የተሻለ ሕይወት ለማምጣት የሚያስችል ኃይል አለው። ሌሎችን ስታስተምር ከአንተ የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ ትፈቅዳለህ ሲልም ተናግሯል።

በበጎ ፈቃደኝነት ማስተማር ሰዎች እንዲማሩ ለመርዳት ጊዜዎን እና ጉልበትዎን በመስጠት የማስተማር ልምድ የሚያገኙበት ድንቅ መንገድ ነው ያለው ወጣት ብሩክ፤ ፍላጎትዎን ለማሟላት እድል የሚሰጥ ምርጫ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን በመርዳት እና በህይወታቸው ላይ እውነተኛ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችለውን ደስታ እንዲለማመዱ ያስችላል ብሏል።

በጎ ፈቃደኝነት እንደ መምህርነት የሌሎች ሰዎችን ህይወት ለመለወጥ ብቻ ሳይሆን የራስህንም ጭምር የሚለውጥ ነው። የህይወት ልምድን እና ስለመረጡት መስክ የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት ብቻ አይደለም፤ ከህዝቡ ጎልተው እንዲወጡ በማድረግ የስራ ልምድን ይገነባል ብሏል።

“በሌሎች ሰዎች ህይወት ላይ ለውጥ ማምጣት የምትፈልግ ከሆነ የበጎ ፍቃድ አስተማሪ ሁን” ሲልም ወጣት ብሩክ አስገንዝቧል።

# “ነዳጅ” የተሰኘ የነዳጅ ክፍያ መተግበሪያ ስራ ጀመረ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነዳጅ የተሰኘውን ዘመናዊ የነዳጅ ክፍያ መተግበሪያ የዲጂታል ቴክኖሎጂን ከአበልጻጊው ኤግልላዮን ሲስተምስ ቴክኖሎጂ ድርጅት ጋር በመፈራረም በይፋ ስራ አስጀመረ።

መተግበሪያው ከንግድ ባንክ ሲስተም ጋር በመገናኘት በቀላሉ የነዳጅ ግብይትን በዲጂታል መንገድ መፈፀም የሚያስችል ነው ተብሏል።

የዲጂታል ቴክኖሎጂ መተግበሪያውን ስራ ላይ ለማዋል የተደረገውን ስምምነት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዲጂታል ባንኪንግ ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ ድሃላክ ይገዙ እና የኤግልላዮን ሲስተምሰ ቴክኖሎጂ ድርጅት መስራችና ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ በሱፈቃድ ጌታቸው በመፈራረም በትናትናው እለት በይፋ ስራ አስጀምረዋል።

በእለቱ አቶ ድሃላክ ባደረጉት ገለጻ፣ የዲጂታል ቴክኖሎጂ መተግበሪያውን በአገር ውስጥ የሚገኘው ኤግልላዮን ሲስተምሰ ቴክኖሎጂ ድርጅት ያበለጸገው መሆኑን ተናግረዋል።

የመተግበሪያው አላማም ለድርጅቶችና ግለሰቦች በነዳጅ ማደያዎች የሚስተዋለውን ችግር ዘመናዊና ቀልጣፋ በሆነ የቴክኖሎጂ መተግበሪያ በመጠቀም መቅረፈ ነው።

መተግበሪያው ድርጅቶችና ግለሰቦች ነዳጅን ሲቀዱ በቀጥታ የነዳጅ ማደያ ተጠቃሚ ድርጅቶችና ግለሰቦች ነዳጅ በሚቀዱበት ማዳያ ከንግድ ባንከ ሒሳብ ቁጥራቸው ጋር በማስተሳሰር በቀልጣፋና በዘመናዊ መንገድ የተፈቀደላቸውን የነዳጅ መጠን እንዲቀዱ የሚያስችል ነው ሲሉ አቶ ደሃላክ ተናግረዋል።

መተግበሪያው በጥሬ ገንዘብ የሚከናወነውን የነዳጅ ግብይት በዲጂታል ክፍያ ስርዓት የሚቀይርና መንግስት ያወጣውን የነዳጅ ድጎማ ስርዓት በተሻለ መንገድ ለመተግበርና ለመቆጣጠር የሚያስችል እንሆነም ገልጸዋል።



ለአሽከርካሪዎች፣ ለነዳጅ ማደያዎችና ለነዳጅ ተቆጣጣሪ የመንግስት አካላትም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቁመዋል።

የኤግል ላይን ሲስተም ቴክኖሎጂ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ በሱፍቃድ ጌታቸው፤ መተግበሪያው ሞተር ብስክሌቶች፣ መለስተኛና ከባድ ተሽከርካሪዎች ከማደያዎች ነዳጅ እንዲቀዱ ያስችላቸዋል ብለዋል።

መተግበሪያው አሽከርካሪዎች በብድር የነዳጅ ግብይት ለመፈፀም የሚያስችል ሲሆን ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊጠቀምበት እንደሚችልም ተመልክቷል።

ሁሉም የተሽከርካሪ ባለንብረቶችና ድርጅቶች በየትኛውም በአገሪቱ ክፍል ከሚገኙ ማደያዎች መተግበሪያውን በመጠቀም ከንግድ ባንክ ሒሳብ ቁጥራቸው ጋር በማስተሳሰር ያለምንም የጥሬ ገንዘብ ንክኪ መቅዳት ያስችላቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ አቶ በርሱፈቃድ ገለጻ፣ መተገበሪያው ኔትወርክ ወይንም ኢንተርኔት ቢቋረጥም እንኳ አማራጮች ስላሉት በቴሌ ብር የሚታየውን የሲስተም ችግር ዩ ኤስ ኤስ መተገበሪያን በመጠቀም ችግሩን ይቀርፋል።

ቴክኖሎጂው በጥሬ ገንዘብ ነዳጅን ከመግዛት ያድናል፤ የነዳጅ የግብይት ስርዓትንም ለማፋጠን ያግዛል ያሉት አቶ በሱፈቃድ፣ በተጨማሪም መተግበሪያው ለሳይበፈር ጥቃት ሰለባ እንዳይሆን ተደርጎ የተዘጋጀ እንደሆነም ተናግረዋል።

# ስምንት የስኳር ፋብሪካዎች ለጨረታ ቀረቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር ስምንት የስኳር ኢንተርፕራይዞችን ወደግል ለማዛወር በወጣው ጨረታ ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ጥሪ አቀረበ። በኢኮኖሚው ውስጥ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ የተለያዩ ማሻሻያዎች መደረጋቸውም አስታውቋል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ መንግስት በግሉ ዘርፍ እያደረጋቸው ካሉ ዘርፈ ብዙ ማሻሻያዎች ውስጥ አንዱ በስኳር ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚደረገውን ተሳትፎ ማሳደግ ሲሆን ከዚህ አንጻርም የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ባለሀብቶች የስኳር ፋብሪካዎች ላይ እንዲሳተፉ ወደግሉ ዘርፍ ለማዛወር ውሳኔ አሳልፏል፡፡

በዚህ መሰረት በወጣው ጨረታ ላይ ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ጥሪ መቅረቡን የገለጸው መግለጫው፤ ፋብሪካዎቹም ኦሞ ኩራዝ 1፣ ኦሞ ኩራዝ 2፣ ኦሞ ኩራዝ 3 ፣ ኦሞ ኩራዝ 5፣ አርጆ ደዴሳ፣ ከሰም፣ ጣና በለስ እና ተንዳሆ መሆናቸው ታውቋል።

ጨረታው ተወዳዳሪነትን እና የስኳር ምርታማነትን በማሳደግ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ለማሟላት ያለመ መሆኑንም ሚኒስቴሩ በመግለጫው አመላክቷል።

የስኳር ፋብሪካዎች መስፋፋት ኢትዮጵያ ለስኳር ግዢ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ በማስቀረት፣ ገቢን ለማሳደግ ብሎም የሸንኮራ አገዳ አምራቾችን ህይወት ለማሻሻል እንደሚረዳም ይታመናል።



ኦሞ ኩራዝ አንድ ስኳር ፋብሪካ

ከዚህ ባለፈም ጥሬ እና ያለቀለት የሸንኮራ አገዳ ምርትን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት እንደሚረዳም ነው በመግለጫው የተመላከተው።

የሀገራችን ኢንዱስትሪ በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነቱን ሚና እንዲጫወት የላቀ አስተዋጽኦ ካላቸው ትላልቅ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ከሆኑት የስኳር ፋብሪካዎች የግሉ ባለሀብቶች ቢሳተፉባቸው ኤክስፖርት መር የሆነ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለማስፋፋትና ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚያስችል ይሆናል ተብሏል፡፡

በተለይም ሀገሪቱ ለሸንኮራ አገዳ ልማት ተስማሚ አየር ንብረት፣ በመስኖ ሊለማ የሚችል ሰፊ የእርሻ መሬት እንዲሁም በቂ ውሃ ያላት በመሆኑ ዘርፉ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡ ከዚህ ባሻገር መንግሥት የሀገሪቱ ህዝቦች ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚከተለው የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት በመንግስት ባለቤትነት ተወስኖ የቆየውን የስኳር ኢንዱስትሪ የግሉ ዘርፍም እንዲሳተፍበት በሩን ክፍት ማድረጉን ያሳያል፡፡

ዜና

# በክልሉ በሕወሓት ጉዳት የደረሰባቸውን ከተሞች ወደነበሩበት ስመመለስ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ

- በወረራው በ228 ከተሞች 42 ሺህ ቤቶች ጉዳት ደርሶባቸዋል

**ቤዛ እሸቱ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሕወሓት ጉዳት የደረሰባቸውን ከተሞች ወደነበሩበት ለመመለስ በእልህ እየተሰራ መሆኑን የክልሉ ከተሞችና መሠረተ ልማት ቢሮ ገለጸ። በሕወሓት ወረራ በ228 ከተሞች ከ42 ሺህ በላይ ቤቶች ጉዳት እንደደረሰባቸውም ተጠቁሟል።

የአማራ ክልል ከተሞችና መሠረተ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢያዝን እንኳሆነ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ ሕወሓት የአማራ ክልል ላይ ወረራ በፈጸመበት ወቅት በ228 ከተሞች 42 ሺህ ቤቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል።

በወቅቱ በክልሉ 228 ከተሞች በወረራ ውስጥ ነበሩ ያሉት አቶ ቢያዝን፤ ያልተወረረውም አካባቢ ጦርነት ውስጥ የነበረ በመሆኑና እንደክልል የሞራል ኪሳራ ለማድረስ ዘመቻ በመካሄዱ ከፍተኛ ኪሳራ ደርሶ እንደነበር ጠቁመዋል። ሆኖም የመከላከል ሥራው እንደተጠናቀቀ ፊታቸውን ወደ ልማት ሥራ ማዞራቸውን ገልጸዋል።

በዚህም መሰረት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴርና ሌሎች አጋር አካላት እንዲሁም በክልሉ ውስጥ ያልተጎዱ ከተሞች የተጎዱትን የመደገፍ ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል። በዚህም 194 እህት ከተሞች በመፍጠር ጉዳት ለደረሰባቸው ከተሞች ድጋፍ በማድረግ ሥራ የሚያስጀምሩበት ሁኔታ መፈጠሩን ገልጸዋል።

በዚህም አመራሩን እና መዋቅሩን ወደነበረበት መመለስ መጀመሪያ በትኩረት የተሠራበት እንደሆነም ጠቁመዋል።

በክልሉ እየተሰራ ያለው ስራ ጦርነት እልህ ውስጥ ያስገባል የሚለው በተግባር የታየበት ነው ያሉት አቶ ቢያዝን፤ በሁሉም ደረጃ ለምነን ያገኘነውን ማጣት የለብንም በሚል ስሜት ቀን ከሌሊት በመስራት ወረራ ውስጥ የነበሩት አካባቢዎች ካልተጎዱት አካባቢዎች ተመሳሳይ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ማድረግ መቻሉን ጠቅሰዋል።

በተጎዱት አካባቢዎች በከተሞች ምግብ ዋስትና የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ወደ 150 ሚሊዮን ብር ድጋፍ እንደሰጠና 18 ፕሮጀክቶች መሰራታቸውንም ጠቁመዋል። ሥራዎች በእልህ በመካሄዳቸው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የስምንት ትምህርት ቤቶች፣ ሰባት የአንድ ማእከል የወጣቶች አገልግሎት መስጫ ማእከላት እና የሦስት ጤና ጣቢያ ግንባታ መጠናቀቁን ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በአገልግሎት አሰጣጡ የሕብረተሰቡ እርካታ ከ50 በመቶ በታች ነው። ከሕብረተሰቡ ጥያቄ አንዱ የመልማት ጥያቄ በመሆኑ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ማስቀጠል እና በክልሉ በከተማ ብቻ ጉዳት የደረሰባቸውን 42 ሺ ቤቶች መገንባት በትኩረት ይሠራበታል ብለዋል።





አቶ ቢያዝን እንኳሆነ

በክልሉ ሁሉም ዘርፍ የጠላት ኃይልን በመከላከል ወደ ሥራ የተገባው ባለፈው ጥር ወር መጨረሻ ላይ ነው።





ኡስታዝ አቡበከር አህመድ

# ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎሉ መድረኮች እየሰፉ መምጣት እንዳለባቸው ተጠቆመ

**አስናቀ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት «ስለ ኢትዮጵያ» በሚል የሚያዘጋጃቸው አይነት ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎሉ መድረኮች እየሰፉ፣ እያደጉና እየጎለበቱ መጥተው ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆን እንደሚገባቸው የሃይማኖት አስተምህሮ ሊህቁ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ ተናገሩ።

ኡስታዝ አቡበከር አህመድ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎሉ መድረኮች መፈጠር ኢትዮጵያውያን ችግሮቻቸውንና ያሉበትን ሁኔታ እንዲገነዘቡና ስለመፍትሄው እንዲያስቡ የሚያደርግ በመሆኑ መልካም አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

እነዚህና መሰል መድረኮች በተጠናከሩ ቁጥር ማህበረሰቡ ጋር ሃሳቦች በትክክል እንዲደርሱ እንደሚያስችሉ የገለጹት ኡስታዝ አቡበከር፤ ሁልጊዜም ሃሳብ ማሸነፍ እንዲችል፣ በሃሳብ የበላይነት እንዲታመንና ነገን የተሻለ ለማድረግ ሁሉም የራሱን አበርክቶ እንዲያደርግ አጋዥ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

ችግሮችን በትክክል በማየት ለመፍትሄ በጋራ መንቀሳቀስ አለብን የሚለውን እሳቤ ይዘው ስለሚመጡ መድረኮቹን መፍጠር፤ ወደ ማህበረሰቡ ማውረድና ሁሉም ማህበረሰብ የራሱን አስተዋፅኦ እንዲያደርግና የድርሻውን እንዲወጣ በማድረግ ሁሉም ከመናገርና ከመስማት ባለፈ ወደተግባርና ለውጥ እንዲገባ መስራት እንደሚገባም አመልክተዋል።

ሁሉም ዜጋ የችግሩ ባለቤት እኔ ነኝ ብሎ የራሱን ድርሻና አበርክቶ መስጠት ወይም መጨመር ቢችል ወደመፍትሄ መድረስ እንደሚቻል፤ ይህ ካለተቻለ ግን እጅን ከከፋት መሰብሰብ እንደሚገባም ገልፀዋል።

‹‹እንደሀገር በብዙ ፈተናዎች ውስጥ አልፈናል” ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ “እስካሁን ድረስ ሁሉንም በሮች ሞክረናቸዋል፤ ስለሆነም ይበቃናል” ሲሉም ተናግረዋል። መነጋገር፣ ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስቦ ለመፍታት መሞከር፣ ለሀገርና ለህዝብ ተብሎ የሚከፈል መስዋእትነት መሸነፍ ሳይሆን ማሸነፍ ነው ሲሉም አያይዘው ገልፀዋል።

አንዱ ከፋትን ሲያስብ የዛ ክፋት አካል በመሆን ፤ በተቃራኒና በበቀል ስሜት ውስጥ በመግባት ሳይሆን በይቅር ባይነት ሁሉም ስለሀገርና ስለቀጣዩ ትውልድ በማሰብ የራሱን አበርክቶና ሚና ለመወጣት ለሰላም የአቅሙን ያህል መልፋት እንደሚገባም አስታውቀዋል። ሰላም አማራጭ የሌለው መፍትሄ ስለሆነ ወዶ ሳይሆን በግድ በጋራ ፈልጎ በመምጣትና እድሎችን በመጠቀም በሰላም ችግሮችን ለመፍታት መወሰንና ለዛም ቁርጠኛ የሆነ እንቅስቃሴ ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑንም ኡስታዝ አቡበከር ተናግረዋል።

# ሦስት የአገር ውስጥ ኩባንያዎች ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር የውል ስምምነት ተፈራረሙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከ430 ሚሊየን ብር በላይ የኢንቨስትመንት ካፒታል ሦስት የአገር ውስጥ ኩባንያዎች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች ለመሰማራት ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር የውል ስምምነት ተፈራረሙ።

የውል ስምምነቱን ‘አፊያን’ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ማምረቻ፣ ‘አሊያኪም’ የምግብ ዘይት ፋብሪካና ‘ዶሜን አልሙኒየም ኮምፖሲት ፓኔል’ የተሰኙ ኩባያዎች ከኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሳንዶካን ደበበ ጋር ተፈራርመዋል።

ስምምነቱን አስመልክቶ የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሳንዶካን እንደገለጹት፤ መንግሥት አቅም ያላቸው የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተሰማርተው እንዲሰሩ በትኩረት እየሰራ ነው።

በተለይም የአገር ውስጥ ባለሃብቶችን ለማበረታታት በተደረገው የአሰራር ማሻሻያ ባለፉት ሁለት ወራት ብቻ አራት ባለሃብቶች በፓርኮቹ ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች እንዲሰማሩ የማግባባት ሥራ ተሰርቷል ብለዋል።

በዛሬው ዕለትም ከአራቱ ድርጅቶች ውስጥ ሦስቱ አስፈላጊውን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ያሟሉ በመሆኑ ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስችላቸውን የውል ስምምነት መፈረም አስፈልጓል ነው ያሉት።

ስምምነቱ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለባለሃብቱ ምቹ የሥራ ሁኔታን በመፍጠር አገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንድታገኝ ያግዛል።

በተጨማሪም ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ከመፍጠር ባሻገር በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የተለያዩ ምርቶችን ማምረትና ከአገር ውስጥ አልፎ ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንደሚቻል የሚያሳይ ነውም ብለዋል።

የውል ስምምነት የፈረሙት ድርጅቶች የምርቶቻቸውን ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃን ያሟሉና ለዚህም የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው መሆኑንም ተናግረዋል።

ኩባንያዎቹ በአጠቃላይ ከ430 ሚሊየን ብር በላይ ኢንቨስትመንት በማስመዝገብ ዘርፉን እንደተቀላቀሉም አብራርተዋል።





የድርጅቶቹ የሥራ ኃላፊዎችና ተወካዮች በበኩላቸው፤ ኮርፖሬሽኑ ወደ ዘርፉ እንዲቀላቀሉ በግብዓትና መሰል ጉዳዮች ድጋፍ ሲያደርግ እንደነበር ተናግረዋል።

በፓርኮቹ ውስጥ የተሰማሩበትን ዘርፍ በማሳደግ ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለማምረት በቁርጠኝነት እንደሚሰሩም አረጋግጠዋል።

የ’አፊያን’ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ዋና ሥራ አስኪያጅ አበራ አህመድ ኩባንያቸው በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከ6 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ መሬት መረከቡን ተናግረዋል።

ኩባንያው የጨርቃጨርቅና አልባሳት ምርትን ለውጭ ገበያ ማቅረብን ዓላማው አድርጎ መቋቋሙን ገልጸው፤ ለዚህም ከ239 ሚሊየን ብር በላይ ኢንቨስት ማድረጉን ገልጸዋል። በዚህም ለ250 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር መታቀዱን ነው የጠቆሙት።

ከአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ 5 ሺህ 500 ካሬ ሜትር መሬት መረከቡን እና በአልሙኒየም ውጤቶች ምርት ላይ መሰማራቱን የጠቀሱት ደግሞ የ’ዶሜን አልሙኒየም ኮምፖሲት ፓኔል’ ተወካይ ስምኦን ገብረመስቀል ናቸው። ከ65 ሚሊየን ብር በላይ ኢንቨስት መደረጉንም በዚሁ ጊዜ ተናግረዋል።

ድርጅቱ ለ60 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ያቀደ ሲሆን፤ ምርቱን ሙሉ ለሙሉ ለአገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርብ ይሆናል ብለዋል።

በተመሳሳይ ‘አሊያኪም’ የምግብ ዘይት ማምረቻ ሥራ አስኪያጅ ሳምሶን እስራኤል በበኩላቸው፤ ድርጅቱ በጅማ ኢንዱስትሪ ፓርክ 3 ሺህ ካሬ ሜትር ሼድ ተረክቧል ብለዋል፡፡

የአቮካዶ የምግብ ዘይትን በስፋት ለማምረትና ተደራሽ ለማድረግ የተቋቋመው ኩባንያው ከ 125 ሚሊየን ብር በላይ ኢንቨስት እንዳደረገም ገልጸዋል። ኩባንያው ለ210 ዜጎች የሥራ እድል የሚፈጥር ሲሆን ምርቶቹን ለዓለም አቀፉ ገበያ የማቅረብ እቅድ እንዳለውም መገለጹን የዘገበው ኢዜአ ነው፡፡

# ከ350 በሚበልጡ የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ እርምጃ መውሰዱን ባለስልጣኑ አስታወቀ

## - ጥናት ካካሄደባቸው 10 ሺ የትምህርት ማስረጃዎች 505ቱ ሀሰተኛ ናቸው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን በ2014 በጀት አመት የስነ ስርዓት ጥሰት በፈጸሙ ከ350 በላይ የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ እርምጃ መውሰዱን አስታወቀ፡፡ ባለስልጣኑ በበጀት አመቱ ከአረጋገጣቸው 10 ሺ የትምህርት ማስረጃዎች 505 ቱ ሀሰተኛ ናቸው ብሏል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ዳሬክተር ዶክተር አንዷለም አድማሴ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ በ2014 በጀት አመት ከየትኛውም በጀት አመት የበለጠ የትምህርት ጥራትን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን የማጽዳት ስራ ተከናውኗል፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተቋሙን የስራ እንቅስቃሴ ገምግሞ አቅጣጫ ካስቀመጠ ጊዜ ጀምሮ ከ350 በላይ በሚሆኑ የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ እርምጃ ወስዷል፡፡

መንግሥት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እየወሰዳቸው ካሉ ተጨባጭ እርምጃዎች ውስጥ ሕገ ወጥ የትምህርት ተቋማትን መቆጣጠር አንዱ ተግባር ነው ያሉት ዶክተር አንዷለም፤ አሁን ላይ የትምህርት ጥራት



ፎቶ በእዩብ ተፈሪ

**ዶክተር አንዷለም አድማሴ**

በኢትዮጵያ ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ኃላፊነት የማይሰማቸውና ትርፍን ብቻ አላማ ያደረጉ ሕገ ወጥ የግል የትምህርት ተቋማት መስፋፋት መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ተቋምና ፕሮግራም መዝጋት አማራጭ አይደለም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ነገር ግን የእውቅና ፈቃድ ሳይሰጣቸው በትውልድ ህይወት የሚነግዱ አካላት ላይ ጥብቅ እርምጃ ይወሰዳል ነው ያሉት፡፡

እንደ ዶክተር አንዷለም ገለጻ፤ በርካታ ዜጎች እውቅና በሌለው የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ገንዘባቸውን ከፍለው ከተማሩ በኋላ ባለስልጣኑ ማረጋገጫ ሲሰራላቸው ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ሲሆንባቸው ለተመሰቃቀለ ህይወት እየተዳረጉ ነው፡፡ በተቋማት ላይ ድንገተኛ ፍተሻ በማድረግ በ355 የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ ከፕሮግራም መዝጋት እስከ ተቋሙን ሙሉ በሙሉ እስከ መዝጋት የደረሰ የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ለዚህም መገናኛ ብዙሃን የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥ ስራ በበጀት አመቱ በትኩረት ከተሰራባቸው መካከል መሆኑን ያስታወሱት ዶክተር አንዷለም፤ በዘርፉ የጤና ሚኒስቴርና ጉምሩክ ኮሚሽን ለሚቀጥሯቸው ሰራተኞች ቅጥር ከመፈጸማቸው በፊት የትምህርት ማስረጃቸው በባለስልጣኑ እንዲረጋገጥ የሚያደርጉበት አግባብ ለህገ ወጥ የትምህርት ማስረጃ ቁጥጥር ጉልህ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡ዕድገትና ቅጥር ሲያከናውኑም በሙሉ ሳያስፈትሹ እንደማያከናውኑ ተናግረዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ፤ የትምህርት ማስረጃ ሲረጋገጥ በቀጣሪ መስሪያ ቤቶች ተገደው የሚመጡ አካላትን የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥና ከውጭ አገር የተገኘ የትምህርት ማስረጃን አቻ ግምት በመስጠት በሁለት መልኩ የሚረጋገጥ ነው ብለዋል፡፡ የማረጋገጥ ስራ የሚጀምረው ከአገር አቀፍ ፈተናዎች እንደሆነና በወቅቱ ከነበረው የመቁረጫ ነጥብ በመጀመር እያንዳንዱ የትምህርት ማስረጃ ተፈትሾ እስከ ዲፕሎማና ዲግሪ እንደሚረጋገጥም ጠቁመዋል፡፡

በ2014 በጀት አመት የጤና ሚኒስቴርና የጉምሩክ ኮሚሽንን ሳያካትት ተገደው ከመጡ ከ10 ሺ በላይ የትምህርት ማስረጃዎችን ማረጋገጥ ተችሏል ያሉት ዶክተር አንዷለም፤ ከተረጋገጡት የትምህርት ማስረጃዎች 505 የሚሆኑት ትክክለኛ ያልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች እንደሆኑም ተናግረዋል፡፡

ፈቃድ ሳያገኙ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ክፉኛ እየጎዱ ያሉ ትውልድን እያቀጨጩ የሚገኙ ሕገ ወጥ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ለመቆጣጠር በሚደረገው ሂደት ህብረተሰቡ ጥቆማ በመስጠት ድጋፍ እንዲያደርግም ዶክተር አንዷለም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

---

## “እናቶች ተረባርበን በጦርነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብዙዎቹ በ50 ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ፖለቲከኞችና መሪዎች አብዛኞቹ በህይወት አሉ ያሉት ወይዘሮ ሰዋሰው፤ “ማገዶ የሚሆነውና የሚያልቀው የድሃው ልጅና ወጣቱ ነው፤ በመሆኑም የትውልድ እናት ለዕርቅና ለሰላም ድርጅት ወጣቱ ለምን ብሎ እንዲጠይቅና ግንዛቤ እንዲኖረው ልጆቻችንን እንደናት መምከር እንፈልጋለን” ሲሉ አብራርተዋል።

ከዚህ በኋላ እኛ እንደ እናት የትውልድን ማለቅ የምንቀበልበት አቅም የለንም ያሉት የድርጅቱ መሪ፤ ተቃውሞ፣ ረብሻና ግጭቱን እንዲሁም ሰልፍ፣ ግድያና ትጥቅ ትግሉን ለብዙ ዘመን ረጅም መንገድ ተጉዘንበታል። ያልሞከርነው ቀሪ መንገድ ተረጋግተን ወደ እርቅና ወደ ሰላም መምጣት ነው ሲሉ ገልፀዋል።

እንደ ወይዘሮ ሰዋሰው ገለፃ፤ በፊት የነበረውን ችግር አንዱ ላይ ማሳበብ ይቻል ነበር፤ አሁን ግን ሁሉም ችግር ሕዝብና ሕዝብ መካከል እየወረደ የሚገኝ ነው። የሚገዳደለው ወንድምና ወንድም ነው። እናት ደግሞ በልጆቿ መካከል እንደማታዳላው ሁሉ የትውልድ እናት ለዕርቅና ለሰላም ድርጅትም የእናትነት ዕሴት በመያዝ በሀገር ደረጃ ለሚፈጠሩ ችግሮች ለማንም ሳያደላ ለዕርቅና ለሰላም ይሠራል።

ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ያለቀው ትውልድ በርካታ ነው ያሉት ወይዘሮ ሰዋሰው፤ አሁንም እየሞቱ ያሉትን ለአንድ ሰሞን ብቻ መነጋገሪያ አጀንዳ ከማድረግ በዘለለ ወንጀለኞቹ በአግባቡና በፍጥነት ሳይቀጡ ድርጊቱ እንደሚረሳ ጠቁመዋል። ይህን ነገር በመቅረፍ በተለያየ ሁኔታ ቤተሰባቸውን ያጡና የተገደሉባቸውን ቤተሰቦች ቀረብ ብለን የጎደለባቸውን መሙላት እና ሃዘናቸው ሃዘናችን መሆናቸውን በማፅናናት ልንገልፅ ይገባል ሲሉ አብራርተዋል።

ሁኔታው ወደ ሕዝብ ወርዶ ገዳይም ሟችም እኛው ከሆንን ሁሉን በደል በጋራ እንውሰድና የጋራ መፍትሄ እናምጣ ሲሉም አክለዋል።

ድርጅታቸው የመጀመሪያ ጉባዔውን በቅርቡ አድርጎ እንደነበረ የገለፁት ወይዘሮ ሰዋሰው፤ በጉባዔያቸው ላይ የሃይማኖት ተቋማት፣ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት፤ የሀገር ሽማግሌዎች ወጣቶችና ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች መገኘታቸውን ተናግረዋል።

ጉባዔው የመጀመሪያ የእርሾ ሥራችን መነሻ ሲሆን፤ ይህ ሥራ ወደ ታላቅ ደረጃ አድጎ የእናቶች ንቅናቄ እንዲሆን አቅደን ነው የምንሠራውም ብለዋል። የእናቶች ንቅናቄ በትውልድ ላይ የሚደርሰው ግፍና እልቂት እንዲበቃና ወደምድር ሰላም ማምጣት ላይ ያተኮረ ንቅናቄ እንደሚሆንም ነው የገለፁት።

እንደ ወይዘሮ ሰዋሰው ገለፃ፤ ፖለቲካ ድርጅቶች እስካሁን የሄዱበት የቁርሾ መንገድ ለሀገርም ሆነ ለሕዝብ የሚፈለገውን ለውጥ አላመጣም። ክልልም ነፃ እናወጣለን ብለው ለሚሉት ሕዝብ ምንም ነገር ያደረጉለት ነገር የለም። ፖለቲከኞች ከዚህ በፊት የተከተሉት መንገድ ከሽፏል፤ ነገር ግን ምድሪቷ ትውልዶችን አጥታለች።

መስዋዕትነት የከፈሉት ሁሉ ደግሞ የኛም ልጆች ናቸው ያሉት ወይዘሮ ሰዋሰው፤ ማናቸውንም በዚህ ዘመን በፖለቲካ ላይ ላሉ በሙሉ ከእንግዲህ ወዲያ የትውልድ ሞት ያመናል፣ በልጆቻችን ህይወት እንድትጫወቱ አንፈቅድላችሁም ልንላቸው ይገባል ሲሉም አክለዋል።

## ‹‹ትኩረታችንን አገር መለወጥና የሕዝባችንን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በትናንትናው ዕለት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ‹‹የ60 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች›› የምረቃ ሥነ ሥርዓት በተካሄደበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፤ አዲስ አበባ እንድትለወጥና እንደ ስሟ አበባ እንድትመስል ፕሮጀክቶችን በፍጥነት ሰርተን ማጠናቀቃችንን እንቀጥላለን።

አዲስ አበባ ከተማ እንደ ስሟና ተወዳዳሪ ከተማ የምትሆነው በሁላችንም ትብብር በመሆኑ በመተባበርና በመተጋገዝ በቀላሉ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል።

ትኩረታችንን አገር መለወጥና የሕዝባችንን ኑሮ ማሻሻል ላይ አድርገን ያለምንም እረፍት እየሰራን ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ ሌት ተቀን የሚሰሩ ዜጎችን በማፍራት በርካታ ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ ለአገልግሎት ክፍት እያደረግን ነው ብለዋል።

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፤ ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም የተረዳነው ከአካባቢዎች ማማርና ከስራ እድል ፈጠራው በላይ የስራ ባህላችን መቀየር የሚችል መሆኑን ነው። የበለጸጉ አገሮችን መንገድ ለመከተልና የስራ ባህላችንን ለመቀየር የሚያስፈልገው በትጋትና በመተባበር መስራት ነው።

ከንቲባ አዳነች “በብዙ ባለሀብቶች ድጋፍ ያስመረቅናቸው በርካታ ፕሮጀክቶች አገርን የሚለውጡና የዜጎችን ተስፋ ማለምለም የቻሉ ናቸው። ከወጣቶች ጀምሮ ስራ ሰርተው ውጤታማ የሆኑ ሰዎችን ከተቋማት ጋር እያገናኘን የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለመለወጥ እየሰራን ነው። የአዲስ አበባ ሕዝብ ከፍተኛ የሆነ የቤት ችግር አለበት፤ ይህን ችግር ለመፍታት በመንግስት ብቻ አይቻልም። ስለሆነም የተለያዩ የቤት መስሪያ መስመሮችን ዘርግተናል። የመንግስትና የግል ተቋማት የጋራ አጋርነትን በመፍጠር በስፋት የቤት ግንባታ መገንባት እንደሚያስፈልግ አምነን ከባለሀብቶች ጋር መስራት ጀምረናል” ብለዋል።

ከተመረቁት ፕሮጀክቶች ውስጥ በ69 ቀናት ውስጥ በኦቪድ ግሩፕ የተሰራው ባለ 11 ወለል መኖሪያ ቤት አንድ ማሳያ መሆኑን የጠቆሙት ከንቲባ አዳነች፤ ከመንግስት ምንም አይነት ወጪ ሳይወጣ የተገነባው የመኖሪያ ቤት ስንተባበር ያለንን አቅም ያሳያል ሲሉ ተናግረዋል።

ከንቲባ አዳነች፤ የግንባታውም ሙሉ ወጪ 50 ሚሊዮን ብር በአቢሲኒያ ባንክ መሸፈኑን በመግለጽ ምስጋና ያቀረቡት ከንቲባ አዳነች፤ ለሚቀጥለው ትውልድ የምናስረክባት ኢትዮጵያ የበለጸገች እንድትሆን ሁላችንም ተባብረን መስራት እንዳለብን አስገንዝበዋል።

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ዘመኑ ደሳለኝ በበኩላቸው፤ የ60 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች በክፍለ ከተማው 845 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው 105 የተለያዩ ፕሮጀክቶች መመረቃቸው ለከተማችን ልዩ ትርጉም አለው ብለዋል። በትጋት፣ በመተጋገዝና በቁርጠኝነት ሰርተን በማጠናቀቅ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት እንዲሰጡና የኑሮ ጫናን እንዲያቃልሉ ለማድረግ ችለናልም ብለዋል።

እንደ ስራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ አገርን መለወጥ የሚችሉ በርካታ ዜጎች አሏት፤ በዚህም በ60 ቀናት ውስጥ ስድስት የዕሁድ ገበያ ማዕከላትን ማስፋፋት ተችሏል፤ ከአምስት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል፤ በቀን አንድ ሚሊዮን ዳቦ ማምረት የሚችሉ ስድስት የዳቦ ፋብሪካዎች ተገንብተዋል፤ 931 መኖሪያ ቤቶችን ማደስ ተችሏል። እንዲሁም ባለ አስራ አንድ ወለል የመኖሪያ ቤት ህንፃ በ69 ቀናት ውስጥ ተሰርቶ ተጠናቋል። ይህም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ኑሮን ለማሻሻል ትልቅ እገዛ ይኖረዋል።

---

## ‹‹የሕወሓት ቡድን ስለሰላም ድርድሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሕወሓት ፖለቲካዊ ባህሪያት በግጭት ላይ የተመሰረቱ ናቸው ያሉት ኮማንደር ገብረመስቀል፤ ሰላምን ከማደፍረስ በስተቀር በሰላም የመኖር ባህሪ የለውም፤ በጥላቻና በመከፋፈል ላይ የተመሰረተ አመለካከትና ባህሪ ነው ያለው፤ ሰላም ይፈጥራል የሚል እምነት የለኝም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሕወሓት ባህሪያት ለሰላም የሚመች አይደለም፤ በጠረጴዛ ዙሪያ በሃሳብና በድርድር ከማመን ይልቅ ሁሉንም ነገር በኃይል እና በጉልበት እፈታለሁ የሚል አመለካከትና እምነት ነው ያለው፤ በሃሳብ የሚያምንና የሚገዛ አይደለም ብለዋል፡፡

‹‹ቡድኑ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የግጭት ባህሪ ነው ያለው ያሉት ኮማንደሩ፤ በአንድ በኩል ለውይይት ዝግጁ ነኝ እያለ በሌላ በኩል ለሰላም ድርድር እንቅፋት የሆኑ ሃሳቦችን ከማቅረብ አልተቆጠበም፤ ለሰላም ዝግጁ ነን ቢልም ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማታለል ነው›› ብሏል።

የሕወሓት ቡድን ለስልጣኑ እንጂ ለትግራይ ህዝብ የሚቆረቆር ስላልሆነ ህዝብ ከህዝብ እያጋጨ ከመኖር አልፎ ወደ ሰላም ድርድር ይገባል የሚል እምነት የለኝም ሲሉ አክለዋል፡፡

የሕወሓት ቡድን ሰላም ፈላጊ ቢሆን ኖሮ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት መንግስት ደጋግሞ ሲለምነው ሰላም ይፈጥር ነበር ብለዋል።

የትግራይ ህዝብ ዳግም እንዳይጎዳ የሕወሓት ቡድን የሰላም መንገድ እንዲመርጥ የተለያዩ ጫናዎችን ማድረግ አለበት፤ ይህ ድጋሚ ወደ ጦርነት ካመራ በሀገሪቱ በተለይም በትግራይ ህዝብ ላይ የባሰ ቀውስ ያስከትላል፤ በጦርነቱ ምክንያት ህዝቡ በምግብና መድኃኒት እጦት በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንደሚገኝ ግልፅ ነው ብለዋል።

የፌዴራል መንግስት እየተከተለው ያለው የሰላም መንገድ የሚመሰገን ቢሆንም የሕወሓት ቡድን ግን ሰላምን ከማደናቀፍ አልፎ አወንታዊ ሚና ሲጫወት አይስተዋልም፤ ባህሪው ለሰላም የተፈጠረ አይደለም፤ ምክንያቱም በግጭት የሚያምን ሀይል ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የሕወሓት ቡድን አለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማታለል ሰላም ፈላጊ ነኝ ቢልም፤ አሁንም የትግራይን ህዝብ ወደከፋ ችግር ለመክተት ከሀሰት ፕሮፓጋንዳና ማጭበርበር አልወጣም፤ ‹‹ዘመቻ ሦስት›› በሚል ስም ጦርነት ከመቀስቀስ ወደ ኋላ አላለም፤ የባሰ ቀውስ እንዳይፈጠር ህዝቡ ሕወሓትን ለሰላም ዝግጁ እንዲሆን አዎንታዊ ሚና ሊጫወት ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሄት



የካበተ ልምድና ዕውቀትን እንደ መነሻ ካፒታል

ገጽ 13





በሁለት ዩኒቶች ሁለተኛው ግዙፍ ግድብ

ገጽ 14




መልካም ሚስት - የባሏ ዘውድ

ገጽ 16

## ‹‹ለ50 ዓመቱ ሰቆቃ ክዳን አበጅተን ወደ ኢዩቤሊዩ ዘመን እንድንመጣ እንሻለን››

- ወይዘሮ ሰዋሰው ስለሺ
የትውልድ እናት ለእርቅና ለሰላም ድርጅት ስራ አስኪያጅ

ገጽ 6

## በውስጥ ገጾች

የሕዳሴ ግድባችን ሕዝባዊ ልዑካን ገጽ 9

የድንበር ሀሳብ ይፍረስ ገጽ 11

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ለ50 ዓመቱ ሰቆቃ ክዳን አበጅተን ወደ ኢዮቤሊዩ ዘመን እንድንመጣ እንሻለን››

- ወይዘሮ ሰዋሰው ስለሺ
የትውልድ እናት ለእርቅና ለሰላም ድርጅት ስራ አስኪያጅ

አስቴር ኤልያስ


ፎቶ፡- እዮብ ተፈራ

**ወይዘሮዋ አንድ ጩኸት አላቸው፤ የሚጮኹት ደግሞ እንደፖለቲከኛ አሊያም ምሑር አይደለም። እንደእናት እንጂ። እኚህ ኖርዲያዊ ኢትዮጵያዊት የሚጮኹት የየትኛውንም የኃይማኖት ተቋም እና የብሄረሰብ አጀንዳ ለማስፈጸም አይደለም። የመንግስትንም ሆነ የተፎካካሪውን ሐሳብ ለማራመድም አይፈልጉም። ቋንቋቸውም እንደዲፕሎማት ልቅም ያለ እንዲሆንም አይደክሙም። ነገር ግን እንደ እናት ጮኸው እንደ እናት መሰማትን ይሻሉ። እንደ እናት ሆነው ለመጮህ ያስገደዳቸው ደግሞ አንድ ነገር በውስጣቸው ለሳለ ነው፤ እርሱም ላለፉት ብዙ ዓመታት ለጣሩለት ለእርቅና ለሰላም ጉዳይ ጆሮ እንዲሰጠው ስለሚሹ ነው። በተለይም በኢትዮጵያ ብሔራዊም ፍትሃዊም እርቅ እንዲኖር በጽኑ ይፈልጋሉ። የኖርዌይ ዜጋ ቢሆኑም የትውልድ ሐረጋቸው የሚመዘዘው ከሚወዷት ኢትዮጵያ በመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረገው መልካም ነገር ልባቸው በሐሴት እንደሚዘል ሁሉ፤ መልካም ባልሆነው ነገር ደግሞ ክፍት ትክዝ ይላሉ። ኢትዮጵያ ባሳለፈቻቸው ግማሽ ምዕተ ዓመት ውስጥ ስለጠፋው የንጹኃን ደም ግድ ይላቸዋል። ስለዚህም የሚፈልጉት በኢትዮጵያ ከልብ የሆነ ይቅርታና እርቅ ማውረድን ነው።**

**እኚህ የዛሬዋ የዘመን እንግዳችን ወይዘሮ ሰዋሰው ስለሺ ይባላሉ። የትውልድ እናት ለእርቅና ለሰላም ድርጅት ስራ አስኪያጅ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ እናቶች የሰላም ጥሪ አስተባባሪ ናቸው። ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ከተማ፣ ለገሃር አካባቢ ሲሆን፣ ባለትዳርና የሁለት ልጆች እናት ናቸው። ከኢትዮጵያ ከወጡ ወደ ሶስት አስርት ዓመታት አልፏቸዋል። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቋንቋና ስነ ጽሁፍ ዲግሪያቸውን በመማር ላይ እያሉ ነበር ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ወደ ኖርዌይ ያቀኑት። በዚያም ኑሯቸውን ቢመሰርቱም ወደእናት ምድራቸው ኢትዮጵያ ግን ከመመላለስ አልተቆጠቡም። ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ቆይታ አጠናቅረን አቅርበነዋል።**

**አዲስ ዘመን፡- የእርስዎ ጩኸት እንደ እናት እንጂ እንደፖለቲከኛ፣ እንደምሁር ብሎም እንደኃይማኖተኛ አይደለም፤ የእናት ጩኸት ከጠቀሷቸው አካላት የሚለየው እንዴት ነው በሚለው ጥያቄ ጭውውታችንን እንጀምር?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** መልካም ነው፤ የእናት ጩኸት ርህራሄን ከተላበሰው ከእናትነት አንጀት የሚፈልቅ ነው። በሁሉም ብሔር ውስጥ ይህች እናት አለች። በሁሉም ኃይማኖትም ውስጥ ትገኛለች። የፖለቲከኛውም የምሁሩም ወላጅ ይህችው እናት ነች። እናትነት ሁሉም ዘንድ ውስጣዊ ስሜቱ አንድ ነው። የልጇቿን ክፉ ማየት አትሻም፤ ሃዘናቸው ያስከፋታል። ቁስላቸውም ይጠዘጥዛታል። ለዚህም ነው ‹‹የኢትዮጵያ እናቶች የሰላም ጥሪ›› በሚል መርህ እናቶችን አካተን ለአገራችን ሰላም የበኩላችንን ለማድረግ ጩኸታችንን ለማሰማት እየጣርን የምንገኘው።

**አዲስ ዘመን፡- ከሰሞኑን €€የኢትዮጵያ እናቶች የሰላም ጥሪ« በሚል መርህ እንቅስቃሴ መጀመሩ ይታወቃል፤ በቅርቡም ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ባሉበትም ውይይት ተካሂዷል፤ በዚህ መርህ የተካተቱት እነማ ናቸው? ዓላማውስ ምንድን ነው?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** የኢትዮጵያ እናቶች የሰላም ጥሪ የሚል እንቅስቃሴ ጀምረናል። በዚህ የኢትዮጵያ እናቶች የሰላም ጥሪ በሚለው ውስጥ ያለነው አስራ አንድ ድርጅቶች ነን። እነዚህ 11 ድርጅቶች የዓለም የእርቅና ሰላም ግብረ ሰናይ ድርጅት፣ የኢትዮጵያውያንና የአሜሪካውያን የሰላም ትብብር ምክር ቤት፣ የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣ የሴቶችና የልጃገረዶች ድጋፍ ኢትዮጵያ፣ ዲቦራ አብሪ የሴቶች አገልግሎት፣ የኢትዮጵያ የሰላም እናቶች ማህበር፣ ምቹ ቤት መልቲ ሚዲያ፣ ተስፋ ኢትዮጵያ ወጣቶች፣ አሻጋሪ የበጎ አድራጊ ድርጅት፣ ቤዛ ኢንተርናሽናል የሴቶች ህብረት እና እኔ የምመራው የትውልድ እናት ለእርቅና ለሰላም ድርጅቶች ሲሆኑ፣ የ11ዱም አስተባባሪ እኔ ነኝ።

አንደኛው ድርጅት የወጣት ድርጅት ሲሆን፣ እነርሱም ለስራችን በጣም የሚያስፈልጉን ሆነው አግኝተናቸዋል። ሁላችንም በተለያየ አቅጣጫ ይሁን እንጂ በሰላም እና በእርቅ ስራ ላይ በአገር ውስጥም ይሁን ከአገር ውጪ ስንሰራ ቆይተናል። የዚህም ስብስብ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ያለን ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እናቶች ነን። እናም ከዚህ በፊት በግል እና በተናጠል ስንሰራ የነበረውን ስራ በአሁኑ ወቅት ወደጋራ ስራ አምጥተን በአንድ አቋም እና በአንድ ዓላማ በመነሳሳት በአገራችን ላይ የበኩላችንን አሻራ ለምን አናስቀምጥም በሚል ነው የተነሳነው።

ስብስቡ ከተጀመረ ብዙ ጊዜ ያስቆጠረ አይደለም። ይሁንና ርቀት ሳይገድበን በማህበራዊ ሚዲያም ሆነ በኦንላይን እንዲሁም ሲቻል ደግሞ በአካልም ስንገናኝ ቆይተናል። በመጨረሻም ስምምነት ላይ በመድረሳችን አገራችን ካለችበት ከፍተኛ የሰላም ችግር መላቀቅ ስላለባት እንዴት እኛ እናቶች ዝም ብለን እንቀመጣለን? እንደ እናት አንድ ነገር ማድረግ አለብን፤ ይህንንም ለማድረግ ለመንግስትም፣ ለተፎካካሪውም፣ ለሚዲያውም፣ ለማህበረሰብ አንቂውም እንደ እናት ጥሪ ማቅረብ አለብን ብለን ነው፤ ሌላው ያስብነው አገራችን ባለፉት 50 ዓመታት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፈጣሪ የለም በሚል የማርኪስዝም ሌኒዚዝም ርዕዮተ ዓለም የተመራች አገር ነበረች። እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከ95 በመቶ በላይ በሚያስብል ደረጃ በፈጣሪው የምናምን ህዝብ ነን።

ከዚህም የተነሳ ፈጣሪውን እንደሚያምን ሕዝብ ከፈጣሪው ጋር መታረቅ አለብን ብለን እናምናለን። ከዚህ የተነሳ ሁሉንም የኃይማኖት ተቋማት አነጋግረን ከፈጣሪ ምህረት እንድንለምን የሚል ተነሳሽነት ነው የያዝነው። በመጀመሪያ ምድራችን መታረቅ ያለባት ከፈጣሪዋ ጋር ነው። በአገራችን ውስጥ 50 ዓመታት ያህል የፈሰሰው ደም በምድሪቷ ላይ እርም ነው። ይህንን እርም እንዳላየ አይተን፣ እንዳልሰማ ሰምተን ብንሄድ ምህረት በምድራችን ላይ ሊመጣ አይችልም። ስለዚህ ፈጣሪ ምህረትንም ፍትህንም እንዲያመጣልን ይህንን የተደረገውን በደል አውቀን አምነን ገዳይም ሟችም እኛው እራሳችን ነንና ከፈጣሪ ጋር አስቀድመን መታረቅ አለብን።

ብዙ ጊዜ የእከሌ ብሔር የእነእከሌን ብሔር ገደለ ወይም ደግሞ የእነእከሌ ተፎካካሪ ፓርቲ የእነእከሌን ብሔር ገደለ በማለት ልክ እኛ ምንም እንዳላደረግን ሆነን ወደሌላው የመግፋት ችግር አለብን፤ አሁን ግን አገራችን ላይ በደረሰው ሁኔታ ግድያው አልፎ ተርፎ በመንደርና በቤተሰብ ውስጥ ገብቷል። ስለዚህ የገዳይም የሟችም እናት እኛው ነን። ችግሩን ለሌላ የምንሰጠው አይደለም። መከራውንም መውሰድ፤ ለመፍትሄውም መጋደል ያለብን እኛው እናቶች ነን። ለመፍትሔው በጋራ መቆም ይጠበቅብናል፤ ከዚህ በላይ ልጆቻችን እንዲያልቁ መፍቀድ የለብንም። ስለሆነም ልጆቻችንን እረፉ ማለት እንዳለብን ሁሉ እንዲሁ ልጆቻችንን የሚማግዷቸውን እረፉ ልንላቸው ይገባል። ከዚህ በኋላ እኛ እናቶች ምድሪቱ ትውልድ የሚጨነግፍባት እንድትሆን አንፈቅድም። ይህንን መከራ አይሆንም ስንልም እንደ እናት እንቆጣለን።

ከፈጣሪ ምህረት እንጠይቃለን ስንልም የደረሱብን በደሎች ቁጠኞች አድርጎናል፤ ሆደ ባሻ አድርጎናል፤ ቂመኞች አድርጎናል። ከዚህም አልፎ ተርፎ ለበቀል ያስሮጠናል። ስለዚህ ይህንን የማይበጀንን ነገር ትተን እኛም ራሳችን ከራሳችን ጋር መታረቅ አለብን ማለት ነው። እንደገና ከወንድማችን ጋር መታረቅ አለብን ብለን ነው ተነሳሽነቱን ወስደን እየተንቀሳቀስን ያለነው። መንግስትም በጉዳዩ ዙሪያ እንዲተባበረን እንሻለን። እስከ ዛሬ ልጆቻቸው ያለቁ እናቶች ዛሬም ያነባሉ። የትዳር አጋራቸውን በግፍ የተነጠቁ ሚስቶች ዛሬም ይቆዝማሉ። እናትና አባታቸውን በጭካኔ የተቀሙ ህጻናት ዛሬም ያለቅሳሉ።

ታዲያ ይህንን ፈተና እንዳልሰማና እንዳላየ ሆነን የምናልፈው እስከ መቼ ነው? ጉዳዩ የአንድ ወቅት የፖለቲከኞችና የማህበረሰብ አንቂዎች ማድመቂያ ሆኖ እስከመቼስ ይቀራል? ጉዳያቸው ተዳፍኖ ቢቀር የእነርሱ እንባና ሰቆቃ ከባድ ነው የሚሆነው። በመሆኑም ነው ለእነዚህ ሰዎች እውቅና ሰጥተን በደላችሁ በደላችን ነው፤ ሃዘናችሁ ሃዘናችን ነው ልንል የሚገባው። ምንም እንኳ የጠፋን ሕይወት መመለስ አሊያ መተካት ባንችልም በሕይወት ያጧቸው ቤተሰቦች ያጎደሉባቸውን ጎድለት እኛ እንደኢትዮጵያ ሕዝብ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ አገር ያለነው ካሳ ልንክሳቸው ይገባል ባይ ነኝ።

የአካል ጉዳትም ሆነ የስነልቦና ጥቃት ለደረሰባቸው በተለይ ደግሞ የመከራውም የጦርነቱም ገፈት ቀማሾች ሴቶች ስለሆኑ እነርሱን እንደእናት ማየት አለብን። ይህን ለማድረግ መንግስት እንዲተባበረን እንፈልጋለን። እስከዛሬ ላለቀው ትውልድ አንድ ቀን ብሔራዊ የሐዘን ቀን ተብሎ በማወጅ ለ50 ዓመቱ ሰቆቃ ክዳን አበጅተን ወደኢዮቤሊዩ ዘመን እንድንመጣ እንሻለን። ይህንን ጥያቄያችንን ለመንግስት እናቀርባለን። ከዚህ በኋላ ምንም እንዳልተፈጠረ እያስመሰልን መሄድ የለብንም።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ እናቶች የሰላም ጥሪ በሚል ስያሜ የተመሰረተው ድርጅት በውስጡ ያካተታቸው አስራአንድ ድርጅቶችን እንደሆነ ገልጸዋል፤ የስብስባችሁ ስብጥር ምን ይመስላል?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** የስብስባችን ስብጥር በተለያየ የእድሜ ክልል ያለንና የተለያየ ኃይማኖትን ያካተተ ነው፤ ለአብነትም ኦርቶዶክሶች፣ ሙስሊሞች፣ ካቶሊኮች፣ ፕሮቴስታንቶች ከዚህ በተጨማሪ የተለያየ ሙያ ባለቤቶች የሆንን አለን። እንዲሁም ከዚህ ቀደም የሰላም እናቶች በመሆን እርቅና ሰላም ይኖር ዘንድ በብዙዎች እግር ላይ ወድቀው ሲማጸኑ የነበሩ እናቶች በስብስባችን ውስጥ የተካተቱ ናቸው። ከዚህ በፊት በእርቅና በሰላም ስራ ላይ ልምድ ያላቸውም የሌላቸውም አሉበት። ያሰባሰበን ዋና ዓላማ እናትነት ነው። እንዳልኩሽ በስብስባችን ውስጥ ወጣቱንም አካተናል። ምክንያቱም ወጣቶች ሰላም ያለባት አገር ውስጥ መኖር አለባቸው ከሚል ነው። ስለዚህ እኛ እናቶች ልጆቻችንን መውቀስ ብቻ ሳይሆን ከጎናቸው በመሆን መከራውን በመካፈልና የሕይወት ልምዳችንንም በማጋራት የማንም ለራሱ ፍጆታ ለሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ማገዶ እንዳይሆኑ የበኩላችንን እንወጣለን።

**አዲስ ዘመን፡- አባላቱ በአገር ውስጥም በውጭ አገርም ያላችሁ እንደመሆናችሁ የመሰባሰባችሁና በጋራ መፍትሔ የማምጣታችሁ ጉዳይ እንዴት ይገለጻል?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** በየጊዜው እንሰበሰባለን። በአካል የመገናኘቱ እድል ያለን በአካል እንገናኛለን። በአካል መገናኘት የማንችለው ደግሞ በዙም እንሰበ ሰባለን። እኛ ዓላማችን ከአስራ አንዱ ባለፈ በአገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በውጭ አገር ያሉትን ሌሎች እናቶችንም ማካተት ነው። ሁኔታዎች ከተመቻቹልን በሚቀጥለው ሳምንት በአዲስ አበባ ከተማ ቢቻል በስታድየም ወይም በመስቀል አደባባይ ከተፈቀደልን ታላቅ ጉባኤ ለማድረግ አቅደናል።

ይህንን ጉባኤ ማድረግ የምንፈልገው እናቶች

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ተያይዘን ትውልድ እናስመልጥ በሚል ተነሳሽነት ነው። እግረ መንገዳችንን ደግሞ አስቀድሜ እንደጠቀስኩት ጥያቄያችንን ለመንግስት ለማቀረብ ነው። ባለፈው ጊዜ ባዘጋጀነው ጉባኤ በርካታ የመንግስትና የኃይማኖት መሪዎችም ተገኝተዋል። የተገኙ እነዚህ መሪዎች ከጎናችን እንደሚሆኑም ገልጸውልናል። በዚህም መሰረት አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ቢሮ ድረስ ሄደን አነጋግረናቸዋል። በወቅቱም ያሉን ነገር እኛ ወደእናተ ፈልገን መምጣት ሲገባን እናንተ ፈልጋችሁን መጥታችኋልና እናመሰግናለን ነው። በሚያስፈልገን ጉዳይ ሊረዱንም ቃል ገብተውልናል። ይሁንና በምን አይነት ሁኔታ ለመስራት እንደምንፈልግ ገና እቅድ እያወጣን ነው። በተመሳሳይ ደግሞ ታገኟቹኋላችሁ በተባልነው መሰረት ከቀናት በፊት የኢፌዴሪን ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴን ለማግኘት ችለናል። በዚህም በጣም ደስተኞች ነን። እርሳቸውም ከጎናችን እንደሚሆኑ ቃል ገብተውልናል። በአገሪቱ ላይ ስላለው የሰላም ጉዳይ የሰላም ሚኒስቴር የሚመለከተው በመሆኑ ወደእነርሱም አቅንተን አነጋግረናቸው በነበረበት ወቅት በከፍተኛ ደስታ ከጎናችን እንደሆኑ ገልጸውልናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሳምንታት በፊት ባካሄዳችሁት ስብሰባ እርስዎም እንዳሉት የመንግስት ባለስልጣናትን ጨምሮ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነርም ነበሩና በዋናነት ያካሄዳችሁት ውይይት ምን ነበር?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** የተሰባሰብነው የሰላም እናቶች የምንፈልገው የሰላም ጥሪ ማቅረብ በመሆኑ ይህን አስመልክተን ሐሳባችንን አቅርበናል። በተመሳሳይ በእነርሱ በኩልም ያለውን ሁኔታ ለመስማትም ነበር በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የጠራናቸው። በእርግጥ በወቅቱ በሙሉ የነበሩ የመንግስት ተወካዮች ከኃይማኖት መሪዎች በስተቀር እነርሱ የመጡት ራሳቸውን ወክለው እንደሆነ ነው የገለጹት። እኛ ደግሞ ራሱን ወክሎ የሚመጣውን ብቻ ሳይሆን መንግስትንም ወክሎ የሚመጣ አካል እንፈልጋለን። ለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት የመንግስትን በሮች በማንኳኳት ላይ የምንገኘው። ነገር ግን ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት በጠራነው መድረክ ላይ ተገኝተው ንግግር አድርገዋል። በጉዳዩም በጣም ተነክተው ከጎናችን እንደሚቆሙ ቃል ገብተውልናል። ይሁንና ጉዳዩን ወደመንግስት ይዘው ሄደው የደረሱበት ውጤት ምን እንደሆነ አናውቅም። እንዲያም ሆኖ እኛ አሁንም ለመንግስት ጥያቄያችንን ማቅረብ እንቀጥላለን።

**አዲስ ዘመን፡- ወደመንግስት ያደረሳችሁት ጥያቄ ብሔራዊ የሃዘን ቀን ቢታወጅ ከሚል ሌላ ምን ምን ጥያቄ አካታችኋል?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** ከጥያቄያችንም አንዱ በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉትን የኢትዮጵያ እናቶች ለማስተባበር ድምጻችንን ማሰማት እንፈልጋለንና ሁኔታዎች ይመቻቹልን ነው፤ ምክንያቱም የመጀመሪያውን ጉባኤ ከሁለት ሳምንት በፊት ስናደርግ ሆቴል ተከራይተን ነው። እንዲህ ስናደርግ ግን ማናችንም የረባ አቅም ኖሮን አይደለም፤ ነገር ግን የአገር ጉዳይ ነው በሚል ተነሳሽነት እንጂ። በእርግጥ ደግሞ አካሄዳችን አገር እንዲረጋጋ መንግስትን እናግዝ በሚልም ነው። ስለዚህ መንግስትም እንደ ግል ጉዳዩ አድርጎ ድጋፍ እንዲያደርግልን እንሻለን፤ በምናደርጋቸው የተለያዩ ጉባኤዎችም አደራሾች እንዲመቻችልን እንፈልጋለን። ድምጻችንን ወጣቶቻችንም እንዲሰሙ እንሻለን። ለጠፋው ትውልድ የአባቶችም ሃዘን አለበትና እነዚሁ የትውልድ አባቶችም ከጎናችን እንዲቆሙ እንፈልጋለን። በተለይ ወጣቶች በእነርሱ የወደፊት ሕይወት ላይ የተሻለ አሻራ ለማስቀምጥ በምንጥርበት ጊዜ በባለቤትነት ስሜት እንዲያግዙን እንሻለን። በጥቅሉ እኛ መንግስትን እናግዛችሁ እንጂ የገዥውንም ሆነ የተፎካካሪውን አጀንዳ ልናስፈጽም አይደለም ሩጫችን። ምክንያቱም በአገሪቱ ላይ ሕጋዊ የሆነ መንግስት አለ፤ ይህ መንግስት በሕጋዊ መንገድ ዜጎቹን የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ነው። ታጥቆ የዜጋውን ደህነት ከሚጠበቀው ሕጋዊ መንግስት ወጭ ያለው አካል ግን እየበዛ ሕይወት እያጠፋ ሲሄድ እኛ እናቶች ዝም የሚያስብል ልብ ስለሌለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ብሔራዊ የሐዘን ቀን እንዲታወጅ የተፈለገበት ዋና ዓላማ ምንድን ነው?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** ዓላማው በግማሽ ምዕተ ዓመት ውስጥ የነበረው የፖለቲካ ቁማር፣ የነበረው የፖለቲካ ጦስ ይህን ያህል ዓመት ሙሉ ትውልድ አሳጥቶናል። በእርግጥ እኛ የመቶ ዓመቱን ታሪክ ልንኖር አንችልም፤ የምንናገረው በእድሜያችን ያለውን ነው። እስካሁን ድረስ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው ትውልድ በመጨረስም ሆነ በማስጨረስ ተግባር ላይ የነበሩት እንጂ መንግስት ብቻ አይደለም። ምክንያቱም እነርሱ ወጣቱን ተነስ፤ ታጠቅና ጫካ ግባ ይላሉ፤ ወጣቱ ደግሞ ጫካ ሲገባ ሊገድልም ሊሞትም ነው። ይሁንና እኛ አሁን የሚንቀሳቀሰው በማንም ላይ ክስ የመመስረት ዓላማ ኖሮን አይደለም። ማንንም ወደ ፍርድ አደባባይ የማመጣት እቅድም የለንም። ነገር ግን ጥፋት መንግስት ዘንድ ብቻ ነው ያለው ማለት አይቻልም። በ50 ዓመት ውስጥ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችም የየራሳቸውን ጥፋት አጥፍተዋል። ስለሆነም እነርሱም ይቅርታ እንዲጠይቁ ነው። በ50 ዓመት የገደብነው ዋናው ነገር አሁን ላይ እየታየ ያለው መከራ የዚያ ውጤት በመሆኑ ነው።

ስለዚህም የሃዘን ቀኑ ከዚህ በኋላ ትውልድ እንዳይረግፍ ለማድረግ ታስቦም ጭምር ነው። ለምሳሌ በውጪው ዓለም አንድ ሰው ሞተ ተብሎ ብሔራዊ የሀዘን ቀን ይደረጋል። ብሔራዊ የሃዘን ቀን መታወጁ በተለያየ ምክንያት ሰዎች የሞቱባቸው አካላትን ሃዘናችሁ ሃዘናችን ነው ለማለት ጭምር ነው። ጎረቤት አስተዛዝኖት ይሆናል እንጂ እኛ በእነዚህ 50 ዓመታት ሕዝቡን ለቅሶ አልደረስነውም። እንደ አገርም ሆነ እንደ መንግስት እና ሕዝብ ሀዘኑን አልተጋራነውም። ሰዎች የሞቱት አገሬን ነጻ አውጣለሁ ወይም ብሔሬን ነጻ አወጣለሁ በሚል ጉዳይ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ሁሉን ያደረገው ከአገሩ አሊያም ከብሔሩ ጋር በተያያዘ ነውና የሞተባቸው ሰዎች ሃዘናችሁ ሃዘናችን ነውና ለዚህም እውቅና እንሰጣችኋለን ለማለት ነው።

ለምሳሌ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ መንበረስልጣን ሲመጡ እኛ ነን የገደልነው፣ አሸባሪዎች እኛ ነበርን እያሉ ሲናገሩ ነበር፤ እርሳቸው ገድለው አስረው ላይሆን ይችላል። ነገር ግን መንግስት የሰራው ስህተት ነው ብለው ነው ይቅርታ የጠየቁት። ልክ እንደእርሱ አይነት የአገሪቱ ርዕሰብሔር ያለፈውን የ50 ዓመቱን በደል መንግስትን ወክለው ይቅርታ ማለት ይችላሉ ማለት ነው። እኛ ሕዝቦች ደግሞ በ50 ዓመቱ ውስጥ መንግስትን አላሰራም ብለናል፤ ግማሻችን በትጥቅ ትግል፣ ገሚሳችን በብዕራችን ችግር ፈጣሪዎች ነበርንና እንደ ሕዝብ ደግሞ ይቅርታ ልንጠይቅ ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ ለአገር ብዙ የመጥቀሙን ያህል አብዛኛው የፖለቲካ ቀውሱም የሚመጣው በዳያስፖራው በኩል ስለሆነ በዳያስፖራውና አገር ቤት ባለው መካከልም እርቅ እንዲመጣ እንሻለን።

**አዲስ ዘመን፡- እንደሚታወቀው አገራዊ የምክክር ኮሚሽን መሰረታዊ የሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶችን ለማጥበብና እርስ በእርስ መግባባት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችለውን ስራ በይፋ ጀምሯል፤ የእናንተ ስራ ከእነርሱ የሚለየው በምንድን ነው?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** እነርሱ አላግባቡ ባሉ አገራዊ ጉዳዮች ላይ በየቦታው ህዝብን ማወያየት ለምሳሌ በኢፌዴሪ ሕግ መንግስት ላይ የማይስማማ ሰው ይኖራል፤ በሰንደቅ ዓላማ የማይግባባ አለ። በአዋሳኝ ቦታዎች የሚጣሉ አሉ። እንዲሁ ሌሎችም መሰል ጉዳዮች ይኖራሉ፤ በእነዚህ ጉዳይ ውይይት ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል። ይህም የራሱ የሆነ ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል ይታወቃል። በዚህ መሃል ደግሞ የሰው ልጅ እያለቀ ነው። ታድያ ውይይቱ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ በተቃራኒው ደግሞ ህዝብ እያለቀ ከሆነ ለማን ነው ውይይቱ የሚያስብለን ነገር አለ። ስለዚህ ውይይቱ ይቀጥል፤ እኛ ደግሞ የምንለው ጥርጊያ መንገዱን እንስራ ነው። ከወዲሁ አገር ማረጋጋት አለብን። እኛ ምድሪቷን ከሰማይም ከምድርም ጋር ማስታረቅ አለብን ነው የምንለው። ይህ ደግሞ ከእነርሱ ጋር የሚጣረስ ሳይሆን ይልቁንም የሚያግዛቸው ነው። እነርሱ ደግሞ በአሁኑ ወቅት የማግባባት እንጂ የማስታረቁ ስልጣን አልተሰጣቸውም።

በፊት የነበረው የእርቅ ኮሚሽን ይህን ሰርቶት ቢሆን ኖሮ ብዙ ጥርጊያ መንገድ በመጣ ነበር። በእርግጥ የበፊቶቹ የሚችሉትን ያህል ሞክረዋል። በአዋጅ ተቋቁመው በአዋጅ ፈርሰዋል። እርግጠኛ ነኝ እነርሱ በእጃቸው ላይ ያለውን ስራ ወደአሁኑ ኮሚሽን እንደሚያሸጋግሩ አስባለሁ። ምን ያህል ግብዓት እንደሆናቸው አላውቅም። እኛ ግን የምንሰራው እንደ እናት ነጻ ሆነን ነው። ዲፕሎማሲያዊ ቋንቋ ነው፤ ፖለቲካዊ አባባል ነው ሌላም ሌላም ነው ሳንል ልክ እንደ እናት ነው የምንነጋገረው። ሌላውም እንዲሰማ የምንፈልገው እንደ እናት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሰው ከራሱም፣ ከፈጣሪውም፣ ከመሰሉም፣ ከአካባቢው እንዲሁም ከተፈጥሮ ጋር ሰላማዊ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረው እንፈልጋለን በሚል መርህ ነው እየተንቀሳቀሳችሁ ያላችሁት፤ ይህ ምን ማለት ነው?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** ኢትዮጵያውያን እንዳልኩሽ ፈጣሪ አለ ብለው የሚያምኑ ናቸው። ይህ በሙስሊሙም፣ በክርስትያኑም በስፋት ያለ ነው። በምድሪቱ እስካሁን በፈሰሰው ደም የተነሳ ያለው እርም ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ስለምድሪቷ እየጮኸ ነው። ስለሆነም የፍትህ አምላክ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር መታረቅ አለብን። ፍትህ እንዲመጣልን ደግሞ እግዚአብሔርን ምህረት እንጠይቅ ነው። ሌላው ከራሳችን ጋር ያልነው በደረሰብን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ጉዳት የተነሳ ቁጡዎች ብሎም አኩራፊዎች ሆነናል። ግማሾቻችን የምናኮርፈው በመንግስት ነው፤ ገሚሳችን ደግሞ በተፎካካሪ ፓርቲዎች ነው፤ ሌሎቻችን ደግሞ በሌላ ምክንያት ነውና እሱ ነገር ቁጣ፣ ምሬት፣ እልህና ብስጭት እንዲሁም በቀል ሞልቶብናል። ይህ አይነቱ አስተሳሰብ ደግሞ ከራስ እንደመጣላት ነውና ከራሳችን ጋር መታረቅ አለብን።

እንዲህ አይነቱን አስተሳሰብ ባለፉት 50 ዓመታት ያህል ሞክረነዋል፤ ቂመኛም ጸበኛም ሆነን፣ የትጥቅ ትግል ብለን፣ በከተማም መሃል ሆነን ድንጋይ ወርውረን አይተነዋል። ነገር ግን የትም አላደረሰንም፤ አያደርሰንምም። እስኪ አሁን ያልሄድንበት መንገድ ቢኖር ይህ አሁን ይዘነው የመጣነው የእርቅና የሰላም መንገድ ነውና ከአምላካችን ጋር እንታረቅ፤ እርስ በእርሳችንም እንታረቅ ነው። ያስቀየምናቸውን ጨምሮ እኛ መሳሪያ ታጥቀን ሰዎች ባንገድል እንኳ ሰዎች የሞቱባቸውን ይቅርታ እንጠይቃቸው ነው። ከተፈጥሮ ያልነው እንደሚታወቀው መንግስትም የጀመረው በጎ ተግባር አለ። ያንንን መከተልና ዛፉንም ዝም ብሎ አለመቁረጥ በራሱ ከተፈጥሮ ጋር እርቅ እንደማካሄድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን በያዛችሁት ዓላማ መንዝ የምትፈልጉት የት ድረስ ነው? ምንስ ሲሳካ ነው እርካታ የምታገኙት?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** እኛ እርካታችን ምድሪቷ እፎይ ስትል ነው። እርስ በእርስ መገፋፋቱ፣ መገዳደሉ አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርሰው የአዕምሮም የስነ ልቦና ጫናው ቆሞ መተባበር፣ መግባባትና መተሳሰብ ሲኖር ነው። ይህ ደግሞ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል፤ ያለንስ ጉልበት የት ድረስ የሚያደርስ ነው ቢባል አናውቀውም። እኛ ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ቢሆን ደስተኞች ነን። ነገር ግን ይህ እስኪሆን ድረስ እንተጋለን። ከዚህ በተረፈ ግን ብዙዎች አሁን የሐሳባችን ተካፋይ እየሆኑ ስለሆነ የተነሳንበትን ዓላማ ብዙ ሰው መደገፍ መቻሉ በራሱ የመከራችንን ዘመን ለማሳጠር ወሳኝ ነው ብለን እናምናለን። በቀጣዩ ዓመት እርቅና ሰላም የሰፈነባት፣ የለቅሶ ድንኳን ሳይሆን የወጣት ሙሽሮች ድንኳን የሚተከልባትን ምድር እናያለን ብለን ነው የምናምነው፤ የምንናፈቀውና ተስፋ የምናደርገውም እሱ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በምትሰሩት ስራ መንግስትን ማገዝ ነው የምትፈልጉት፤ እናንተስ መንግስት ምን እንዲያደርግላችሁ ነው የምትፈልጉት?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** በመጀመሪያ ደረጃ መንግስት ይዘን የተነሳነውን ዓላማ እንዲያምንበት እንፈልጋለን። መንግስት እንግዲህ እያልነው ነውና አቅም በሚያንሰው ቦታ ሁሉ እንዲተባበረን እንሻለን። በእርግጥ እኛ እንደ ሕዝብ መንግስትን አላሰራ ብለነዋል። ሚዲያዎችም እንዲሁ እንዲተባበሩን ፍላጎታችን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለኢትዮጵያ እናቶች የሚያስተላልፉት መልዕክት ካልዎ?**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** የኢትዮጵያ እናቶች ሆይ! እኛ ከዚህ በኋላ ትውልድ እንዲነጠቅብን አንፈልግምና ልጆቻችሁን ላልተገባ አካል አትስጧቸው። በየጫካው በመሆን ሰዎችን የምትገድሉብን እባካችሁ ያንን አታድርጉ፤ ልጆቻችንንም የዚያ አይነት ዓላማ ውስጥ አታስገቡብን እንዲሉ ነው የምንፈልገው። የራሳቸውን የፖለቲካ ሒደት ለማጋጋል ልጆቻቸውን የሚያሸፍቱባቸውን አካላት ይብቃችሁ እንዲሏቸው ነው የምንፈልገው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ወይዘሮ ሰዋሰው፡-** አዲስ ዘመን እድሉን ሰጥቶን ይህን የእናቶች የዘመናት የሰቆቃ ድምጽ እንዳሰማ ስለፈቀደልኝ እኔም አመሰግናለሁ።



# ማህደረ ጤና

# ተስፋ ፈንጣቂ የቀዶ ህክምና ክፍል

**አስናቀ ፀጋዬ**



ፎቶ፡- በአለርት ሆስፒታል

የቀዶ ህክምና ክፍሉ በቀን እስከ 20 የሚደርሱ ህፃናትን የማስተናገድ አቅም አለው፤

ዓለም አቀፍ ጥናቶች እንደሚያሳዩት 30 ከመቶ ያህሉ የበሽታ ጫና በቀዶ ህክምና አማካኝነት ሊታከም ይችላል። ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገራት በአማካይ 0 ነጥብ 03 የህፃናት ቀዶ ሐኪም ለ100 ሺ ህፃናት እንዲሁም አንድ የህፃናት ልዩ ቀዶ ሐኪም ከ3 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ህፃናት እንደሚደርስ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ በተቃራኒ ግን ባደጉት አገራት አንድ ልዩ የህፃናት ቀዶ ሐኪም ለ47 ሺ ህፃናት በአማካይ ተደራሽ ይሆናል። ይህም ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገራት አሁንም ድረስ ህፃናት ጥራት ያለው የቀዶ ህክምና እንደማያገኙ ያሳያል።

በኢትዮጵያ ላንቃና ከንፈራቸው ተሰንጥቆ የሚወለዱ ህፃናት ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ በውል የሚያሳይ መረጃ ባይኖርም ቁጥሩ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ስለመምጣቱ በርካታ ጠቋሚ ምልክቶች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ የላንቃና ከንፍር መሰጠንቅ ቁጥር እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ታዲያ መንግስትም ሆነ ሌሎች የግል ህክምና ተቋማት በሌሎች በሽታዎች ህክምና ላይ ትኩረታቸውን በማድረጋቸው የቀዶ ህክምና አገልግሎቱ ሰፋ ባለና በተሻለ ሁኔታ ሲሰጥ እምብዛም አይታይም።

በእርግጥ መንግስታዊ ባልሆኑ የውጭ ድርጅቶች አማካኝነት አልፎ አልፎ የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና አገልግሎት የሚሰጥ ቢሆንም ያን ያህል አጥጋቢ አይደለም። ተደራሽነቱም ቢሆን አጠያያቂ ነው። በዚህም ምክንያት በርካታ ህፃናትና ታዳጊዎች ለስነ-ልቦናና ሌሎች ተያያዥ የጤና ጉዳቶች ሲጋለጡ ይስተዋላል።

ሆኖም ከብዙ ጥረት በኋላ እንዲህ አይነቱ የላንቃ ስንጥቃትና የከንፈር ጉዳት ቀዶ ህክምና አገልግሎት «ኪድስ ኦር» እና «ስማይል ትሬን» በተሰኙ የግል ድርጅቶችና በጤና ሚኒስቴር ትብብር አዲስ አበባ በሚገኘው አለርት ሆስፒታል ውስጥ በልዩ ሁኔታ ተገንብቶ በቋሚነት አገልግሎቱ መሰጠት መጀመሩ ለወላጆች እፎይታን ለህፃናት ደስታን ፈጥሯል።

የቀዶ ህክምና ማእከሉ መገንባት ከዚሁ የላንቃ ስንጥቃትና የከንፈር መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና አገልግሎት ጎን ለጎን ሌሎች የህፃናት ቀዶ ህክምና አገልግሎቶችም በተሻለ መልኩ እንዲሰጡ በር ከፍቷል።

የአለርት ማእከል ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶክተር እስማኤል ሸምሰዲን እንደሚናገሩት በአለርት ሆስፒታል የላንቃና ከንፍር ስንጥቃት ቀዶ ህክምና ክፍል የተገነባው በ«ኪድስ ኦር» እና «ስማይል ትሬን» በተሰኙ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማትና በጤና ሚኒስቴር ትብብር ሲሆን ቀዶ ህክምና ክፍሉን ገንብቶ ለማጠናቀቅ 8 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ፈጅቷል።

የማእከሉን ግንባታ ለማከናወን አንድ አመት የፈጀ ሲሆን አራት የቀዶ ህክምና ክፍሎችን ያጠቃልላል። አንደኛው በ«ኪድስ ኦር» እና «ስማይል ትሬን» ድጋፍ ሙሉ የህክምና መሳሪያዎች ተሟልቶለት ሙሉ በሙሉ ለህፃናት ብቻ የቀዶ ህክምና አገልግሎት ይሰጣል።

ይህም የፕላስቲክና ሪኮንስትራክቲቭ ቀዶ ህክምናዎችን ማለትም በተፈጥሮ በፊት ላይ፣ እጅና እግር፣ ነርቭና ጅማቶች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች ቀዶ ህክምናዎችን ያጠቃልላል። ከዚሁ ጎን ለጎን የአጥንት ህክምናም ይካሄድበታል። ሶስቱ ክፍሎች ደግሞ የላንቃና የከንፈር ስንጥቃት ቀዶ ህክምና አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በአራቱ የቀዶ ህክምና ክፍሎችም በአንድ ጊዜ አራት ህፃናትን ቀዶ ማከም ይቻላል። በቀን ደግሞ ከ15 እስከ 20 የሚሆኑ ህናፃናትን ቀዶ ለማከም ያስችላል።

የነዚህ የቀዶ ህክምና ክፍሎች መገንባት ቀደም ሲል አገልግሎቱን ሲጠባበቁ የነበሩትን ህፃናት በአፋጣኝ ህክምና እንዲያገኙና የነበረውንም ውዝፍ ወረፋ እንዲቀንስ ያደርጋል። በርካታ ታካሚ ህፃናትንም በአንድ ጊዜ የቀዶ ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል። የአልጋ እጥረትና ከቀዶ ህክምና ጋር ተያይዞ ያለውን ችግርም ይቀርፋል። እንደ አገር በቀዶ ህክምና ያለውን ተደራሽነትም ያሰፋል።

የከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና ከዚህ ቀደም በተለያየ መልኩ በነፃ ሲሰጥ ቆይቷል። ሆኖም ህክምናው በአለርት ሆስፒታል ውስጥ የራሱ የቀዶ ህክምና ክፍል ተከፍቶለት ስራ መጀመሩ ከዚህ ቀደም በተበጣጠሰና በተቆራረጠ መልኩ ሲሰጥ የነበረውን አገልግሎት በቋሚነት ለመስጠት ያስችላል።

በአለርት ሆስፒታል ፕላስቲክና ሪኮንስትራክቲቭ ሰርጀሪ ክፍል ነርስ ኃላፊ ሲስተር አምሳለ ገላዬ እንደሚናገሩት በ«ኪድስ ኦር» እና «ስማይል ትሬን» ትብብር አስፈላጊ የህክምና መሳሪያዎችን በማሟላት የላንቃና ከንፈር መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና ክፍል በአለርት ሆስፒታል ተቋቁሟል።

የቀዶ ህክምና ክፍሉ አራት ትላልቅ የቀዶ ህክምና ክፍሎች ያሉት ሲሆን በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የተለያዩ የህፃናት፣ የአጥንት፣ የመልሶ ጥገና ሌሎች የነርቭና የጅማት ቀዶ ህክምና አገልግሎቶች ይሰጣሉ። በቀዶ ህክምና ሂደቱም ከአስራ አምስት እስከ ሃያ የሚደርሱ የጤና ባለሙያዎች ይሳተፋሉ። እነዚህም በፕላስቲክና ሪኮንስትራክቲቭ ቀዶ ህክምና ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ ከተባሉት ውስጥ ቀደምቶቹና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በመምህርነት እያገለገሉ የሚገኙ ናቸው። ስምንት የአጥንት ስፔሻሊስት ሐኪሞችም አሉ።

በተጨማሪም በተለያዩ የአገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሐኪሞችና ጠቅላላ ሐኪሞች በቀዶ ህክምና ክፍሉ ውስጥ ይሰራሉ። አርባ ነርሶችና አስራ ስድስት የሰመመን ባለሙያዎች በዚህ የቀዶ ህክምና ስራ ይሳተፋሉ። በፅዳትና በሌሎች ስራዎች ላይ የሚሳተፉ ሃያ ሰራተኞችም አሉ።

በላንቃና ከንፈር መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና አገልገሎት ለማግኘት በርካታ ህፃናት ይመጣሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በርካታ ውዝፍ ወረፋዎችም በዚሁ አገልግሎት መከፈት ምክንያት ይቀንሳሉ ተብሎም ይታሰባል። በቀን በቀዶ ህክምና ክፍሉ እስከ ሃያ የሚደርሱ ህጻናት የነርቭ፣ የጡንቻ፣ ቃጠሎና የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ አገልግሎቶችን እያገኙ ነው።

ከዚህ ቀደም የላንቃና ከንፈር መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና በረጂ የውጭ ድርጅቶች አማካኝነት በዘመቻ መልክ ሲሰጥ የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ አገልግሎቱ በቋሚነት በአለርት ሆስፒታል ውስጥ ራሱን ችሎ መሰጠቱ በሁለንተናዊ መልኩ የህፃናትን ጤንነትና እንቅስቃሴ የሚያሻሻል ነው። ለህክምና ባለሙያዎችም ስራው እርካታን ያጎናጽፋል።

የስማይል ትሬን የምስራቅ አፍሪካ ቅርንጫፍ ኃላፊ ወይዘሮ ሲስኒ ዘሚካኤል በበኩላቸው እንደሚገልፁት ስማይል ትሬን እ.ኤ.አ በ1999 በአሜሪካን አገር የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን በዋናነት የከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ነፃ የቀዶ ህክምና አገልግሎት ይሰጣል። በኢትዮጵያም እ.ኤ.አ ከ2006 ጀምሮ ይህንኑ የቀዶ ህክምና አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በዚህም ወደ 36 ሺ የሚሆኑ ህፃናትና አዋቂዎች የዚህ ነፃ የቀዶ ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። አሁንም ድርጅቱ ይህን ነፃ የቀዶ ህክምና አገልግሎት እያስፋፋ ይገኛል።

የከንፈርና ላንቃ መሰንጠቅ ችግር ያለባቸው ህፃናት የአመጋገብ ችግር አለባቸው፤ ለመጥባትም ይቸገራሉ። በዚህም በትንታ፣ በኢንፌክሽንና ሌሎች መሰል ችግሮች ይሰቃያሉ። ባስ ሲልም ከነዚህ ችግሮች ጋር በተያያዘ አምስት አመት ሳይሞላቸው ሕይወታቸው ያልፋል። ነገር ግን ደግሞ ይህ የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ችግር በቀላል ቀዶ ህክምና በመቅረፍ የህፃናቱን ሕይወት ማስተካከል ይችላል።

በመሆኑም ይህን ቀላል ቀዶ ህክምና ተደራሽ በማድረግ ህፃናቱ ሕይወታቸው እንዳይጎዳ፤ የመናገር፣ የመስማትና ሌሎች የስነ ልቦና ችግሮች እንዳይደርሱባቸው ስማይል ትሬን በርካታ ኢትዮጵያውያንን አግዟል። አሁንም ድርጅቱ ይህንኑ ፕሮግራም በማስፋፋት ሂደት የቀዶ ህክምና የሚካሄድባቸው ክፍሎች ዘመናዊነት እንደሚጎላቸው አረጋግጧል። ቀዶ ህክምና ሲደረግ ለህፃናት የሚስፈልጉ ቁሳቁሶች ካልተሟሉ በቀዶ ህክምና ወቅት ለሚፈጠሩ ችግሮች እንደሚጋለጡም ተመልክቷል።

ይህንኑ ታሳቢ በማድረግም ድርጅቱ የአቅም ግንባታ በማድረግ የህፃናት የላንቃና ከንፈር መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና ክፍል ከ300 በላይ በሚሆኑ የቀዶ ህክምና መሳሪያዎች እንዲሟሉ በማድረግ በአለርት ሆስፒታል አዲስ፣ በተለየና ለህፃናት ምቹ በሆነ መልኩ ተገንብቷል።

ይህም ሆስፒታሉ የመንግስት እንደመሆኑ በርካታ ህፃናት ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች መጥተው በተመጣጣኝ ዋጋ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ከዚህ አኳያም ቅድሚያ በመስጠት በአለርት ሆስፒታልና የካቲት 12 ሆስፒታል የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና ክፍል እንዲገነባ ተደርጓል። ይህም በሚቀጥሉት ሶስት አመታት በትንሹ በሺዎች የሚቆጠሩ ህፃናት ይገለገሉበታል ተብሎ ይታሰባል።

እንደ ኃላፊዋ ገለፃ በክልልም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ድርጅቱ ለረጅም አመታት የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና አገልግሎቱን ለረጅም አመታት ሲሰጥ ቆይቷል። ነገር ግን በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገለገሉት በመንግስት ህክምና ተቋማት በመሆኑ ከግል ተቋማት ይልቅ የመንግስት ተቋማት በርካታ ድጋፍ ይፈልጋሉ።

ከዚህ አንፃር ድርጅቱ የመንግስት የህክምና ተቋማትን በማጠናከር፤ አሰራራቸውንም በማዘመን ለታካሚዎች ሰፊ የሆነ አገልግሎትን የመስጠት ራዕይ አለው። ከግል ይልቅ የመንግስት የህክምና ተቋማት ብዙ ክፍተቶች ያሉባቸው በመሆኑም በስልጠና፣ በቁሳቁስና የተለያዩ ድጋፎችን ይሰጣል። ያለውን የባለሙያ እጥረት ለመቅረፍም ድርጅቱ የነፃ የትምህርት እድል ፕሮግራሞችን ያመቻቻል።

ድርጅቱ በዋናነት የከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና ቢሆንም ስራው ከዚህም ሰፋ ያለ ነው። በአለርት ማእከል የተቋቋመው የቀዶ ህክምና ክፍል ግልጋሎቱ የከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ለደረሰባቸው ህፃናት ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ቀዶ ህክምና ለሚፈልጉ ህፃናትም ጭምር ነው። ስለዚህ ፕሮግራሙ ሰፊና ታዳሽነት ያለው ነው።

በዚህ በአዲስና በተለየ መልኩ በአለርት ሆስፒታል ውስጥ በተቋቋመው የቀዶ ህክምና ክፍል ውስጥ ከከንፈርና የላንቃ መሰንጠቅ ቀዶ ህክምና በተጓዳኝ ሌሎችም የህፃናት የቀዶ ህክምና አገልግሎቶችም ይሰጣሉ። የቀዶ ህክምና ክፍሉ ለሁሉም የቀዶ ህክምና አገልግሎቶች ሁሌም በሩ ክፍት ቢሆንም ታዲያ የባለሙያና የአልጋ ጉዳይ አብሮ የሚነሳ በመሆኑ እነዚህን ማሟላት ያስፈልጋል።

የቀዶ ህክምና ማገገሚያ ክፍሎችም መስፋት አለባቸው። በዚሁ መሰረትም ሆስፒታሉ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ከዚህ አኳያ የቀዶ ህክምና ክፍሉ ከዚህ በፊት የነበረውን ችግር በመቅረፍ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ ቢኖረውም ሌሎች ተጓዳኝ ስራዎች መሰራት አለባቸው። ይህን ማድረግ ከተቻለ ደግሞ የአገልግሎቱን ተደራሽነት ማሳደግ ይቻላል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# የሕዳሴ ግድባችን ሕዝባዊ ልዑካን

**ዘመን አይሽሬው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፤**

የዓለም ሀገራትን ለዘርፈ ብዙ የጋራ ጥቅምና ለማሕበራዊ መስተጋብር ከሚያገናኙ ዕድሜ ጠገብ መድረኮች መካከል አንዱ የሕዝብ ለሕዝብ ዲፕሎማሲ በቀዳሚነቱ የሚጠቀስ ነው፡፡ ሺህ ዘመናት የተቆጠረለት ይህን መሰሉ "የሰላም ማብሰሪያ ግንኙነት" የሩቅና የቅርብ ሕዝቦችን ከማቀራረብ አልፎ ተርፎ በብዙ በጎ ጉዳዮች ያቆራኘ "በረከት" ጭምር እንደሆነ በስፋት ይታመናል፡፡ የጂኦግራፊ ርቀትና ቅርበት፣ የባህል፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት ልዩነት፣ የኢኮኖሚ ከፍታና ዝቅታ ለሕዝቦች የእርስ በእርስ ግንኙነት ከቶውንም ቢሆን መሰናከልም ሆነ ገደብ የመጣል ብርታት የላቸውም፡፡ ምክንያቱም ተፈጥሯዊ ስለሆነ፡፡

በዚህ "ዘመናዊ ዓለምም" ቢሆን መደበኛውን የመንግሥት ዲፕሎማሲ ማገዝ ብቻም ሳይሆን ፍሬያማነቱ እጅግ ልቆ የሚነገርለት ይህን መሰሉ ሕዝባዊ ተልዕኮ (Publice Diplomacy) በተደራጀና ተገቢውን ተቋማዊ ቅርጽ ይዞ በሀገራችን መተግበር የጀመረው ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ነው፡፡ "ጥንት ጥንት" የሚባለው ዕድሜው የሚጠቀስለት በኢመደበኛ ባህርይው እንጂ ለመደበኛ "ተጽእኖ ፈጣሪነቱ" ሀገራችን ተቋም ፈጥራለት ተገቢው እውቅና መስጠት የተጀመረው በዋነኛነት የታላቁ ህዳሴ ግድባችን የግንባታ ዜና ከተበሰረ በኋላ ነበር፡፡

ዜናው ተበስሮ የግንባታው እንቅስቃሴ ወደ ሥራ ከተገባበት ጊዜ ጀምሮ በሕዝባችን ዘንድ የተፈጠረውን ደስታ፣ ሁሉን አቀፍ ያልተቆጠበ ተሳትፎና ድጋፍ በተመለከተ ምሳሌነቱን ለወደፊቱ የዓለም ታሪክ ተገቢውን አክብሮት በመስጠት "በወርቅ ቀለም" ከትቦና ሰንዶ እንደሚያስቀምጠው ለመገመት አይከብድም፡፡ የታላቁ የህዳሴ ግድባችን ለእኛ ለባለጉዳዮቹ "የእያንዳንዱ ዜጋ አሻራ የታተመበት" የደስታና የሃሴት ምንጭ፤ "ለተቀናቃኞቻችንና" ለበርካታ የዓለም መንግሥታት ደግሞ የጀርባ ሴራ መጎንጎኛና መነጋገሪያ ዋና አጀንዳ ስለምን ሆነ ብለን መጠየቁ አስፈላጊ የማይሆነው መልሱ ለማንኛውም ባለሀገርም ይሁን ባእድ እንግዳ ስለማይሆን ነው፡፡

የአባይ ወንዝ ፖለቲካ መጦዝ የጀመረው በዚህ በእኛ ዘመን ብቻም አይደለም፡፡ የውሃዎቻችን ጌቶች እንዳንሆን፤ በተለይም አባይ ወንዛችንን ጥቅም ላይ ማዋል እንዳንችል የብዙ ጦርነት ወዳድ ሀገራት "የእብሪት ክንድ" እየተደጋገመ ሲሰነዘርብን ኖሯል፡፡ በጥቋቁር ሰንዱቆች ውስጥ የቆለፍንባቸው አብዛኞቹ የውጭ ባእዳን የወረራ ታሪኮች መንስዔያቸው በዋነኛነት ቢመረመር ሰበቡ የአባይ ወንዛችንን እንዳናለማ እና በተፈጥሮ ሀብታችን እንዳንጠቀም ለማንበርከክ ታስቦ መሆኑ ለጥርጥር አይጋብዝም፡፡ "ውሃ" ብለው የመጡ ወራሪዎች "ውሃ ውሃ" እያሉ የተመለሱትና እንደ ፈሰሰ ውሃ ላይታፈሱ ከንቱ ሆነው የቀሩት በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ክንድ ደቀውና ተዋርደው ስለመሆኑ ደጋግሞ ስለተጻፈ ደግመን በዚህ ጽሑፍ በዝርዝር አናስታውሰውም፡፡

የአባይ ወንዛችንን በተመለከተ በዘመናት ውስጥ ሀገራችን እምነቷን ስታስተጋባ የኖረችው "በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ ተመሥርተን ውሃችንን ለልማት እናውለው" እንጂ "ከራሴ ማህጸን የሚፈልቀውን ፀጋ ለብቻዬ እጠቀምበታለሁ" በሚል ግትርነት እንዳልሆነ እንኳን ወዳጆቻችን ጠላቶቻችንም አይጠፋቸውም፡፡

እስከ ዛሬ ድረስ ሀገራችን ካከናወነቻቸው እጅግ አስልቺና ውጤታማ የመደበኛ ዲፕሎማሲ ሥራዎች መካከል በአባይ ወንዝ አጠቃቀምና በህዳሴ ግድባችን ዙሪያ የደከመችበት አታካችና እልህ አስጨራሽ ጥረት በምንም መመዘኛ ቢለካ ወደርም ሆነ መጠን ያለው አይመስልም፡፡ አብዛኞቹ የዓለም ታላላቅ የሚዲያ ተቋማትም እንዲሁ የአባይን ወንዝና ይሄንንው "የብርሃን ተስፋችንን" ማዕከላዊ ጉዳይ በማድረግ የሰሩትን ዜናና ዘገባ ያህልም በሌሎች ጉዳዮች ላይ ስለማተኮራቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ እንደዚያም ቢሆን ግን ኢትዮጵያ የሰላማዊ የዲፕሎማሲ መርሆዋን ሳትለቅ በእውነቷና በእምነቷ እንደፀናች አለች፡፡ በዚህ ጽሐፍ ለመዳሰስ የሚሞከረውም ከመደበኛው ዲፕሎማሲ ጎን ለጎን የተካሄደውን አስመስጋኝ የሀገራችንን የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጥረት ይሆናል፡፡

"ልበ ሰፊዋ ሀገሬ" የታሪካዊ ጠላቶቿንና ወደረኞቿን "ዛቻና የእጅ አዙር ዘመቻ" ለመመከት እየተጋች ያለችው በመደበኛ የዲፕሎማሲ አሰራሯ ብቻ አልነበርም፡፡ ከመቶ ሚሊዮን በላይ ዜጎቿን ይወክላሉ በማለት ከተለያዩ የሙያ ዘርፎችና አደረጃጀቶች ባዋቀረችው ገለልተኛ የሕዝብ ተወካዮች የልዑካን ቡድን (ፐብሊክ ዲፕሎማሲ) አማካይነትም ጭምር እንጂ፡፡

የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን የተቋቋመው የህዳሴ ግድባችን መሠረት በተጣለበት ማግሥት ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስም በቀላሉ ሊታዩ የማይገባቸው ተልዕኮዎች በስፋት ተካሂደዋል፡፡ የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን የመጀመሪያ ጉዞውን ያደረገው በ2007 ዓ.ም ወደ ግብጽ ካይሮ ነበር፡፡ ይዞት የሄደው የሀገር መልእክትም አጭርና ግልጽ ነበር፤ "በአባይ ወንዛችን ላይ እየተገነባ ያለው የታላቁ ህዳሴ ግድባችን የታችኛውን የናይል ተፋሰስ ሀገራት በምንም መልኩ የሚጎዳ አይደለም፡፡ መርሁ የጋራ ተጠቃሚነትን (win win strategy) የሚያከብር እንጂ በፍጹም የትኛውንም የተፋሰሱን ሀገር የሚጎዳ እንዳልሆነ በሕዝብ ስም እናረጋግጣለን" የሚል ነበር፡፡

ይህ መልእክት በቅድሚያ የደረሰው ለክቡር የግብጽ ፕሬዚዳንት አብድል ፈታህ ኤል ሲሲ ነበር፡፡ ክቡርነታቸውም በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም በቤተመንግሥታቸው ተገኝቶ ቡድኑ ያቀረበላቸው መልእክት "የአባይ ወንዝ የጋራ ተጠቃሚነት መርህ የማይናወጥና የህዳሴ ግድቡም ቢሆን በፍጹም በተፈጥሯዊ የውሃ ድርሻቸው ላይ ተጽእኖ እንደማይኖረው" በማረጋገጥ ሲሆን፤ ፕሬዚዳንቱም መልእክቱን በደስታና በአክብሮት መቀበል ብቻም ሳይሆን "መርሁ እንዳይሸረሸር ለላካችሁ መንግሥታችሁና ሕዝባችሁ አደራውን አስተላልፉን" በማለት ነበር፡፡

ለክቡር ፕሬዚዳንቱ ብቻም ሳይሆን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎድሮስ ዳግማዊ በኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የእስክንድርያ ፖፕ እና ፓትርያርክ ዘመንበረ ማርቆስ በጽ/ቤታቸው በመገኘት ተመሳሳይ መልእክት አቅርቦላቸዋል፡፡ በተከታታይ ቀናትም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና ለውሃ ሚኒስትሩ፣ ለግብጽ ምሁራንና በእረፍት ላይ ለሚገኙ የሀገሪቱ ዲፕሎማቶች (retired diplomats) እና ለበርካታ የማሕበረሰብ ተወካዮች የማያወላውለው የኢትዮጵያ አቋም በሚገባ ተገልጾላቸዋል፡፡

የግብጽ ጉዞ ከተከናወነ ከጥቂት ወራት በኋላ የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ክቡር አብድል ፈታህ ኤል ሲሲ ለአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ አዲስ አበባ በተገኙበት ወቅት የመጀመሪያ ሥራቸው ያደረጉት የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድንን በሸራተን ሆቴል አግኝተው የማይናወጠውን የኢትዮጵያን አቋምና መልእክት ቡድኑ በሀገራቸው ተገኝቶ ስላቀረበላቸው ልባዊ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን በተመሳሳይ ዓመት በሱዳን ሪፐብሊክ፣ በ2012 ዓ.ም ደግሞ በዩጋንዳ ሪፐብሊክ በመገኘት ለርዕሳነ ብሔሮቹ፣ ለሚኒስትሮች፣ ለሕዝብ ተወካዮችና ለየሀገራቱ ምሁራንና በተጽእኖ ፈጣሪነታቸው ለሚታወቁ ዜጎች ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ አጠቃቀምና በህዳሴ ግድቡ ዙሪያ የምታራምደውን የጋራ ተጠቃሚነት የፀና አቋም በሚገባ ለማስረዳት ተሞክሯል፡፡

የልዑካን ቡድኑ ተልዕኮ ያተኮረው በአባይ ተፋሰስ ሀገራት ብቻ አልነበረም፡፡ በጂቡቲና በኤርትራ ሀገራት በመገኘትም ከሁለቱ ሀገራት ጋር ያለው ጠንካራ ጉርብትናና ወዳጅነት ይበልጥ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ለመንግሥታቱ መሪዎችና ለሚመለከታቸው ተቋማት መሪዎች ሕዝባዊ መተማመኛውን በታላቅ አክብሮትን በግልጽ ቋንቋ አስረድቷል፡፡ በመደበኛው የዲፕሎማሲ አሰራርና በፐብሊክ ዲፕሎማሲ አማካይነት የተከናወነው ይህን መሰሉ ጥረት በቀላሉ የሚታይ ሳይሆን ሀገራችን ለሰላማዊ ጉርብትናና ለጋራ ተጠቃሚነት መርህ ምን ያህል የማይናወጥ አቋም እንዳላት ጥሩ ማሳያ ሊሆን የሚችልና የሚያስመሰግን ተግባር ነው፡፡

በመሠረቱ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ ተቋማዊ ሆኖ በአንድ አቅጣጫ ብቻ የተቃኘ ሳይሆን በርካታ መንገዶች ስላሉት ሀገራችን በአግባቡ ብትጠቀምበት ብዙ ልታተርፍበት ትችላለች፡፡ ለምሳሌ፡- በስፖርት አደባባዮች ጀግኖቹ ባለ ድል አትሌቶቻችን የሀገራቸው ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብና ስሟ በክብር እንዲጠራ ማድረጋቸው ከሚያገኙት ሜዳሊያና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች በዘለለ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ትሩፋቱ ከፍ ያለ ነው፡፡ በእነዚህ መሰል መድረኮች የኢትዮጵያን የሰላም ፈላጊነት መርህ፣ የገለልተኛነት አቋምና ከጎረቤቶቿ ጋር በጋራ ተባብሮ ለማደግ ያላትን ጽኑ ፍላጎትና አቋም የስፖርቱን መርህ በማይጻረር መልኩ መግለጽና ማስተዋወቅ ቢቻል የሚገኘው ውጤት በቀላሉ የሚገመት አይሆንም፡፡

በኪነ ጥበባት ዘርፎች፣ በንግድ እንቅስቃሴና በሃይማኖታዊ ጉዞ ወዘተ. በመሳሰሉት ተሳትፎዎች ዜጎች በግልም ሆነ በቡድን ተደራጅተው ወደ ተለያዩ ሀገራት ሲጓዙ ሀገራቸውን ለማስተዋወቅ እንዲችሉ ልዩ ድጋፍና ግልጽ ተልዕኮ ቢሰጣቸው ውጤታማ ሥራ ሊሰሩ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

ይህ ጸሐፊ የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን አባል ሆኖ በተገኘባቸው በርካታ ሀገራት የተገነዘበው ዋነኛ ጉዳይ ቀደም ካለው ዘመን ጀምሮ ሀገራችን አገልግሎቱን አጠናክራ ባለመያዟ ብዙ እድሎች እንዳመለጧት ለመረዳት አላዳገተውም፡፡ በዋነኛነት ግብጽ ለዚህን መሰሉ ጉዳይ ትጉህ ስትሆን ሱዳንን የመሳሰሉ ጎረቤት ሀገራት ደግሞ ተጽእኖ ፈጣሪ ዜጎቻቸውን በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድኖች በማደራጀት ጠንካራ ሥራዎችን ለመሥራት ሲሞክሩ እያስተዋልን ነው፡፡ የሁለቱ ሀገራት መሰል ብድኖች ኢትዮጵያ ውስጥ መምጣታቸውም አይዘነጋም፡፡

ወቅቱና ዘመኑ ከመደበኛው ዲፕሎማሲ ባልተናነሰ መልኩ የዜጋ ተኮር ሚሽን እጅግ ውጤታማ ፍሬ እየተስተዋለበት መሆኑን መንግሥታት በሚገባ ተረድተውታል፡፡ በተለይም እኛን መሰል "ለብዙ ጥቃቶች ጥርስ ለገባ ሀገር" የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አገልግሎት ተጠናክሮ መቀጠሉ ጊዜም ሆነ ቀጠሮ ሊሰጠው የሚገባ ሀገራዊ ጉዳይ አይደለም፡፡ በቅርቡ በጥቂት የሀገራችን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እየተጣለ ያለው የፐብሊክ ዲፕሎማሲ መሠረት እጅግ ተጠናክሮና በኔት ዎርክ ተሳስሮ በጋራ መንቀሳቀስ ቢቻል ለሀገር የሚጠቅሙ በርካታ ውጤቶችን ማስመዝገብ ይቻላል፡፡

በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ላይ በግላቸው ሀገራቸውን ወክለው ከምሁራን ጋር ሙግትና ክርክር በማድረግ የዜግነት ድርሻቸውን እየተወጡ ያሉ ግለሰቦችም በአንድ ጥላ ሥር በቡድን ተሰባስበው በጋራ መመሥረት ቢችሉ ይበልጥ ፍሬያማ ውጤቶች ሊዘመርበት እንደሚችል ለማመን አይከብድም፡፡

በቅርቡ የተጠናቀቀው የሦስተኛው ዙር የህዳሴ ግድብ የውሃ ሙሌትና የሁለተኛው ተርባይን ሥራ መጀመር በወደረኞቻችንና ከእነርሱ ጀርባ "አለንላችሁ" በሚሏቸው ታላላቅ ሚዲያዎች ሳይቀር ምን ያህል መንጫጫት እያስከተለ እንዳለ የምናየው ነው፡፡ በተለይም ከእውነት ባፈነገጠ እምነት "አባይ የሚመነጨው ከግብጽ ተራሮች ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እየሠራች ያለችው ይህንን ተፈጥሯዊ ፀጋችንን ልታጎድልብን ነው" እየተባሉ በሀሰት ትርክት የተሞሉትን የዋህ የግብጽ ዜጎች ከስህተታቸው ማረምና እውነቱን ማሳየት የሚቻለው ጠንካራ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን በመሥራት ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ደራስያን ማሕበር ሃምሳኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን ሲያከብር ከጋበዛቸው ዓለም አቀፍ እውቅና ካተረፉ ደራስያንና ደራሲያት መካከል አንዷ የግብፅ ደራስያንን ወክለው የተገኙት ዶ/ር ኢክባል ባራካ ነበሩ፡፡ እኚህ በሀገራቸውና በአረቡ ዓለም ዘርፈ ብዙ ዝናን የተጎናጸፉት ደራሲትና ጋዜጠኛ ኢትዮጵያ በተገኙበት ወቅት የተመለሱት አዲስ አበባን ረግጠው ብቻም ሳይሆን በርቀት የሚያውቁትን የአባይን ወንዝ "በኢትዮጵያዊ ጠረንነቱ በአካል ተገኝተው እንዲያሸቱት" ወደ ጎጃምና ጎንደር ጉዞ ተመቻችቶላቸው ነበር፡፡ ከእርሳቸው ጋርም ስድስት የሱዳን ደራስያንና አንድ የሊቢያ ደራሲ እንዲገኙ ተደርጓል፡፡

ቡድኑ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላ ስለ አባይ ወንዝና ስለ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በነበረ ውይይት ላይ በተለይም ዶ/ር ኢክባል በተሳሳተ መረጃ ሀገራቸው ግብጽ ሕዝቧንና ታዳጊ ልጆቿን "አባይ የሚመነጨው ከግብጽ ተራሮች ላይ ነው" የሚለውን የውሸት ትርክት በመጥቀስ የደራስያን ማሕበሩን አመራር ይቅርታ ጠይቀው ነበር፡፡

እኒሁ የተከበሩ ደራሲት የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን ግብጽ በተገኘበት ወቅት በአንድ የምሁራን ጉባዔ ላይ ተገኝተው "የግብጽ ምሁራን፣ ዲፕሎማቶቻችንና ሚዲያው በውሸት ትርክት ‹የናይል ወንዝ የሚመነጨው ከግብጽ ተራሮች ላይ ነው› በማለት ለዘመናት ሲያደናግሩን መኖራቸው ውሸት ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የጎረቤቶቿን ጥቅም ሳትነካ ከራሷ ምድር የሚመነጨውን የናይል ወንዝ ለሕዝቦቿ ጥቅም እንደፈለገች ማዋሏ መብቷ ነው፡፡" በማለት የመሰከሩት በአደባባይና በይፋ ነበር፡፡

እንዲያውም ተሰብሳቢውን ፈገግ ለማስደረግ የሞከሩት "እባካችሁ በግብጽ የኢትዮጵያ አምባሳደር አድርጋችሁ ሹሙኝ" በማለት ጭምር ነበር፡፡ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አገልግሎት በምርጫ የሚደረግ ሳይሆን ዘመኑ ግድ ስለሚል ነው፡፡ ይህ አሰራር የሕዝብ ለሕዝብ ማቀራረቢያ አንዱና ዋነኛ መንገድ ስለሆነ ኢትዮጵያ በዚህ ዘርፍ የጀመረችውን ሥራ አጠናክራ ልትቀጥል ይገባል፡፡ ኃላፊነቱን ወስዶ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድኑን ላደራጀው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ከፍተኛ አመራሮች ይህ ጸሐፊ የአደራ መልእክቱን የሚያስተላልፈው በቆይ ብቻ ዝንጋዬ ይህ ታላቅ አገልግሎት ቸል እንዳይባልና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ነው፡፡ ሰላም ይሁን!

# ተናጋሪው ዶሴ

# የባጃጅ ሹፌሮች ገዳዮች

አስመረት ብስራት



ሰው የዕለት ጉርሱን አግኝቶ ለመኖር የተለያዩ ሥራዎችን ይሠራል። ከዕለት ጉርሱ አልፎ የነገ ኑሮውን ለማቃናት ደፋ ቀና የሚለውም በርካታ ነው። ተሳክቶለት የሥራ መሥመሩ የተቃናለት ያገኘው ላይ ለመጨመር የሚታትረው እንዳለ ሆኖ የሰው መሥራትና ማግኘት በቅናት የሚያንገበግበውን ቤቱ ይቁጠረው። አይኑ በቅናት ደም ከመልበስም አልፎ ለመንጠቅ ለመቀማት የሚያሰላስለው ብሎም ወደ ተግባር የሚቀይረው ብዙ ነው። ከሥራ ወዳዶቹ መካከል ለህዝብ የትራንስፖርት አገለግሎት የሚሰጡት የባጃጅ ሹፌሮችና ባለቤቶች ተጠቃሽ ናቸው።

እነዚህ ሥራ ወዳድ የባጃጅ ሹፌሮችና ባለቤቶች ማልደው ከቤት በመውጣት ለሥራቸው መቃናት ደፋ ቀና ይላሉ። ለሥራቸው መቃናት በጠዋት የሚወጡት የባጃጅ ሹፌሮችና ባለቤቶች በአከባቢው በፍጥነት ውር ውር ሲሉ ይታያሉ። የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ብሎም ጥሪት ለማፍራት የእለት ሥራቸውን በጠዋት ከሚጀምሩት የባጃጅ ሹፌሮች መካከል ወጣት ማናየ እንየው አንዱ ነው።

**ታታሪው የባጃጅ ባለቤት**

ወጣቱ ማናየ እንደ ልማዱ በጠዋት ተነስቶ ባለቤቱ ያዘጋጀችለትን ቁርስ ቀማምሶ ወደ ሥራው ተሰማርቷል። በጠዋት ወደ ሥራው ለመድረስ የተጣደፈውን ተሳፋሪ ሲያመላልስ ውሎ ረፋድፋድ ሲል ሥራውም ጋብ አለለትና አረፍ ብሎ ከጓደኞቹ ጋር ሲጨዋወት ቆየ ። የሥራ መውጫ ሰዓት ሲደርስም ጠዋት የሸኘውን ሰው ወደየቤቱ ሲመልስ አመሸ።

የዕለቱን ሥራ አብቅቶ ወደ ቤቱ ለመግባት በሚዘጋጅበት ወቅት ተገልጋዮችን አገኘ።ከእነዚህ ተሳፋሪዎች ጋር በሰላሳ ብር ኮንትራት ይዘው ለመሄድ ይስማማሉ። ተሳፋሪዎቹ ወደ ማናየ ቤት አቅራቢያ ይሄዱ ስለነበር ሳያቅማማ የባጃጁን በር ከፍቶ አስገባቸው። ሀገር ሰላም ብሎ ሲሠራ የዋለው የባጃጅ ሹፌር ቀኑን ሙሉ ያጠራቀማትን ይዞ ወደ ቤቱ ሊገባ እግረ መንገዱን የያዛቸውን ተሳፋሪዎች ይዞ ተጓዘ።

**ያልታሰበ ዱብዳ**

ጥር ሀያ ሰባት ቀን ሁለት ሺ አስራ ሶስት አመተ ምህረት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ከሰላሳ አከባቢ ነበር። ሁሉም ሰው ቤቱ ተከቷል፤ የተወሰኑ ባጃጆች በአካባቢው ከመታየታቸው በቀር ዝር የሚል አንድም ፍጥረት አልነበረም። በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ አስራ ሁለት ክልል ልዩ ቦታው ቦሌ ቡልቡላ ሙሉ ወንጌል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነው። የባጃጅ ባለቤት የሆነው ማናየ እንየውን በሰለሳ ብር ኮንትራት በማናገር ወደ ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን እንዲወስዳቸው በመስማማት ወደ ባጃጁ ገቡ። ተሳፋሪዎች በፀጥታ ተጓዙ፤ አሳቻ ሥፍራ ከደረሱ በኋላ ቀድመው ያቀዱትን ተግባር መፈፀም ጀመሩ።

ወደ መንገድ ዳር ጠጋ ብሎ ከባጃጁ ሊያወርዳቸው ሲቆም አንደኛው ተሳፋሪ አስራት አበበ የባጃጁን ሹፌር ማናየ እንየውን በክርኑ አንቆ በመያዝ ትንፋሹን አሳጥሮ ህይወቱ እንዲያልፍ አደረገ። ዮሃንስ ማጠሉ እና አስራት አበበ የማናየን እግር በጋራ ይዘው በማውረድ መሞቱን ሲያረጋግጡ ከቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ካለ የመንገድ ቱቦ (የውሃ መውረጃ) በመከተት መዝረፍ ይጀምራሉ። ማናየ ማለዳ ወጥቶ ላቡን አፍስሶ ያገኘውን አምሰት ሺ ብር የሚገመት ስልክ እና አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ብር የሚገመት ባጃጅና ገንዘብ ወሰዱ፡፡

**እንደገና ጥፋት**

በተመሳሳይ ምትኩ መለሰ የተባለ ሌላ የባጃጅ ሹፌር እሱም እንደሥራ ባልደረቦቹ በጠዋት ወደ ሥራው ወጥቶ የሚለፋ ወጣት ነበር። ከጠዋት እስከ ማታ ያለ እረፍት የሚሥራው ይህ ወጣት፤ ከባጃጅ ሥራ ሊያወጣው የሚችል ጥሪት ለማጠራቀም እረፍት ብሎ ነገር አያውቅም። አንዴ በተራው ሌላ ጊዜ በኮንትራት ሥራውን ሲያጧጡፍ እንደሚውል የሚያውቁት ይናገራሉ። ልረፍ ቢል እንኳን ምግብ ለመቀማመስ ካልሆነ ሥራና ሥራ ብቻን ዓለማው አድርጎ የሚንቀሳቀስ ወጣት ነበር።

ከሥራ ቤቱ፤ ከቤቱ ወደ ሥራ ብቻ መገላጫው የሆነው ይህ ወጣት ገንዘቡን ለማጠራቀም እቁብ ገብቶ በየቀኑ ለሚጥለው እቁብ ገንዘቡ እንዲሞላለት ሲጣጣር ይውላል። ከእቁብ ተርፎም ቤተሰቡን ለማስተዳደር የሚበቃው ገንዘብ ለማግኘት አንድም ቀን ሰለቸኝ ታከተኝ ሳይል ይሠራል። እቁብ ሲደርሰው በከንቱ ከማጥፋት ይልቅ ለአለማው መሳካት በባንክ ይቆጥባል። በላብ በጥረቱ የህልሙ ቦታ ለመድረስ ሥራን አማራጭ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ወጣት ነበር።

በተቃራኒው ደግሞ በሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን በጥበቃ ሥራ የሚተዳደሩት ነገር ግን ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ ብቻ የሆነባቸው የራሳቸውን ስራ ፈጥረው ታሪካቸውን ከመቀየር ይልቅ ማልደው ከቤታቸው ወጥተው ለሥራ ውር ውር የሚሉት ባጃጆች ላይ አይናቸውን የሚጥሉት ነፍሰበላዎች እንደልማዳቸው ምትኩ ላይ አይናቸውን ጥለዋል። ከላብ አዳሪዎች መካከል ምትኩን ወይም ሌላውን አንዱን ገለው ዘርፈው በወንጀል ላይ ወንጀል ለመጨመር ዝግጅት ላይ ናቸው። በተለይ ምትኩ መለሰ ላይ አይናቸውን ጥለዋል።

ቀድመው ከዘረፉት ንብረት ላይ ያየዙትን ይዘው ከአከባቢው የተሰወሩት ወንጀለኞች ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም ሆኖባቸው የመጀመሪያውን ወንጀል ከፈጸሙ ከአምስት ቀናት በኋላ፤ የካቲት ሁለት ቀን ሁለት ሺ አስራ ሶስት አመተ ምህረት ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ከሰለሳ አከባቢ ፤ አስራት አበበ ወጣት ምትኩ መለሰን የጀኔሬተር ባትሪ ሊሸጥለት መሆኑን በመግለፅ እና በማስማማት ምትኩን ደውሎ እንዲመጣ በማድረግ አስራት እና ተባባሪው ዮሃንስ ማጠሉ በጥበቃ ሠራተኝነት ከሚሰሩበት ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጊቢ ውስጥ እንዲገባና እንዲደበቅ አደረጉ።በኋላም ዮሃንስ ማጠሉ “ሌባ ሌባ” በማለት ምትኩን በያዘው የጥበቃ ዱላ ጭንቅላቱን ሲመታው አስራት ተከትሎ ምትኩ በወደቀበት ተባብረው በመቀጥቀጥ ህይወቱ እንዲያልፍ አደረጉ።

ይህን እኩይ ተግባር በመተባበር ከፈፀሙ በኋላ ቀደም ሲል የገደሉትን የማናየ እንየውን አስከሬን በከተቱበት ውሃ መውረጃ ቱቦ ውስጥ በድጋሚ ያጠፉትን የምትኩ መለሰን አስከሬን በመደበቅ ለሌላ ጥፋት ይዘገጃጁ ጀመር። ተከሰሾቹ ቀጥቅጠው ከገደሉት ከወጣት ምትኩ መለሰ ባጃጁን አራት ሺ አምስት መቶ ብር የሚገመት ስልክ እና ይዞት የነበረውን ሶስት ሺህ ብር በመውሰድ ከአከባቢው ይሰወራሉ።

**የፖሲስ ምርመራ**

ዋል አደር ሲል በጠዋት ወጥተው ወደ ቤታቸው ያልተመለሱት የባጃጅ ሹፌሮች ጉዳይ ያሳሰባቸው ቤተሰቦቻቸው ጉዳዩን ይዘው ፖሊስ ጋር ቀረቡ። ሁለቱም እጅግ ሰለማዊ ብዙውን ጊዜያቸውን በሥራ ከማሳለፍ በስተቀር ከሰው ጋር ግጭት ያልነበራቸው ሰዎች እንደነበሩ ተገለፀ። የሟቾቹ ቤተሰቦች ባጃጃቸውን ይዘው ከወጡ በኋላ ወደ ቤት ሳይመለሱ ቀናቶች ያሳለፉት ወጣቶች ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ፖሊስ መፍትሄ ይስጠን ሲሉ ጥያቄ አቀረቡ።

መጣላት የማይወዱ ከሆነ ከቤታቸው በሰላም ከወጡ ምን ገጠማቸው ? ሲል ፖሊስ አሰሳውን ጀመረ። በሌላ በኩል ደግሞ የአከባቢው ጠረን መቀየር ያሳሰባቸው እነዛ የሟች አስክሬኖች የተጣሉበት የውሃ መውረጃ ቱቦ አከባቢ ነዋሪዎች ጉዳዩ ምን እንደሆነ ለማጣራት አፍንጫቸውን ተከትለው ፍለጋ ጀመሩ። ያን ጊዜ የሁሉም ሰፈርተኞች እግር አንድ ቦታ ላይ ተገናኘ። ይህ ሰፈሩን የበከለው መጥፎ ሽታ ከሚመጣበት ትቦ ስር ጎንበስ ብለው ሲመለከቱ ባልጠበቁት ሁኔታ የሁለት ሰዎችን አስክሬን አዩ።

ያኔ ለፖለስ ጥቆማ ደረሰው።ፖሊስ በአከባቢው ሲደርስ ቀድሞ በደረሰው የሰው ጠቁብን ጥቆማ መሰረት ሟቾቹ የባጃጆቹ ሹፌሮች ሊሆኑ ይችላሉ በሚል ጥርጣሬ አስክሬናቸውን ወደ ፎረንሲክ ምርመራ በመላክ ሟቾቹ እነሱ መሆናቸው እንዲረጋገጥ ተደረገ።

ለሥራ የወጡት ከነባጃጃቸው ለቀናት ወደ ቤታቸው ያልተመለሱት ሹፌሮችን ማን ሊገላቸው እንደሚችል ፖሊሰ መርመራውን ይጀምራል። ከበርካታ እልህ አስጨራሽ ጥረት በኋላ አንዱ ዘራፊ ባልተለመደ ሁኔታ ገንዘብ በብዛት ሲያወጣ የተመለከቱት የአከባቢው ነዋሪዎች ለፖሊስ ጥቆማ ያደርሳሉ። ያኔ ምርመራው ተጠናክሮ ሲቀጥል አንዱ አንዱ ላይ እየጠቆመ ተጠርጣሪዎች ተይዘው ሲጣራ፤ የውንብድና ወንጀል መፈፀማቸው እና የባጃጆቹን ሹፌሮች መግደላቸው ተረጋገጠ።

ተከሳሾች በፖሊስ ክትትል እና በህብረተሰቡ ድጋፍ ተይዘው፤ ፖሊስ ያገኘውን ማስረጃ በማጠናከር ለዐቃቤ ህግ አቀረበ። በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ በመተላለፍ በፈጸሙት የሰው መግደል እና ከባድ የውንብድና ወንጀል ክስ ተመሰረተባቸው።

## ውሳኔ

የዐቃቤ ህግ የክስ መዝገብ እንደሚያሳየው፤ ተከሳሾቹ በተለያየ ጊዜ በመገናኘት ባጃጅ ከግለሰቦች ላይ በሀይል ለመንጠቅ ሲመካከሩ እና ሲዘጋጁ ቆይተው ድርጊቱን በመፈፀማቸው ይህ ግምት ውስጥ ገብቶ በከባድ የውንብድና ወንጀል እንዲጠየቁ ለፍርድ ቤቱ ክሱ ቀረበ።

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሰው መግደል ወንጀል ችሎት የቀረቡት ተከሳሾች ድርጊቱን አልፈፀምንም በሚል የእምነት ክህደት ቃላቸውን የሰጡ በመሆኑ፤ ዐቃቤ ህግ ያሰባሰባቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በማቅረብ ተከራከረ። ተከሳሾችም መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ያሰሙ ቢሆንም፤ በዐቃቤ ህግ የቀረበውን ሰው እና የሰነድ ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻላቸው ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹን በተከሰሱበት አንቀፅ ሥር ጥፋተኛ ናቸው በማለት ብይን ሰጠ፡፡

በመጨረሻም ሐምሌ ሀያ አምስት ቀን ሁለት ሺ አስራ አራት አመተ ምህረት በዋለው ችሎት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የፈፀሙት ተደራራቢ ወንጀል በመሆኑ፤ በሁለቱም ክሶች አንድ የቅጣት ማክበጃ በመያዝ እያንዳንዳቸው በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ተወሰነ፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የድንበር ሀሳብ ይፍረስ

**አቤል ገ/ኪዳን**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ወሰን ዙሪያ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን በዚህ ሳምንት አሳውቀዋል። የተስማሙባቸው ጉዳዮች ዝርዝር ገና ይፋ ስላልተደረገ ብዙ ማለት ባይቻልም ሁለቱም ተደራዳሪዎች ደስተኛ እንደሆኑ ግን ግልጽ ነው። ሁለቱም አንድ ቀን ፈንድቶ ብዙ ህዝብን እንዲያጠፋ ታስቦ የተጠመደን ቦንብ (ታይም ቦንብ) አምክነናል በማለት የሁነቱን ግዝፈት ለማስረዳት ሞክረዋል። ውሳኔው እንደተባለው ታሪካዊ ቦንብ ማምከን መሆን አለመሆኑን ሰንብተን የምናየው ሆኖ ይህ የወሰን ጉዳይ ግን ብዙ ጣጣዎች ይዞ የተቀመጠ እንደነበር ማወቅ ከባድ አይደለም። ስለዚህም ይህን ችግር ለመፍታት በሁለቱም ወገን እንቅስቃሴ መደረጉ የሚደነቅ ነው።

የሆነ ሆኖ ወደ ዋናው ጉዳይ ስንገባ የእኛ ህዝብ የድንበር ፍቅር ያለው ነው። አጥር ፤ ቅጥር ፤ ወሰን ፤ ድንበር ፤ ይዞታ ምናምን ለሚባሉ ነገሮች ያለው ፍቅር ከፍተኛ ነው። አጥሬን ገፋ በሚል በኩርማን መሬት ሊጋደል ይችላል። 50 ገበሬዎችን የማታኖር መሬት ህምሳ ሺዎች ለሚሞቱበት ጦርነት መንስኤ ልትሆን ትችላለች። እርግጥ መሬት ዋነኛ ሀብት እና የሀብት ምንጭ በሆነበት አገር ሰው መሬትን ቢወድ እና ድንበርን ቢያጠብቅ አይፈረድበትም። ነገር ግን አንዳንዴ በመሬት እና በድንበር ዙሪያ የምናደርገው ትግል መሬቱ ካለው ጥቅም አንጻር ሳይሆን ስለ መሬት እና ድንበር ካለን እሳቤ አንጻር የተቃኘ ነው። በዚህም የተነሳ የመሬት እና የድንበር ጉዳይ ሁሌም የተጋነነ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ የድንበር እና የመሬት እሳቤያችን ዛሬ ላይ ዓለም ካለበት ሁኔታ አንጻር ሲታይ ኋላቀር ነው ማለት እንችላለን። ዛሬ ላይ በመላው ዓለም የድንበር እሳቤ እየከሸፈ ነው። ሉዓላዊነት(ግሎባላይዜሽን) አገራት ድንበራቸውን መጠበቅ እንዳይችሉ እንዲያውም ክፍት እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል። በዚህም የተነሳ ዛሬ ላይ ብዙ አገራት የድንበር ሀሳብን ትተው የአስተዳደር ወሰን ማበጀት ላይ ጠንክረዋል። አውሮፓ ብንሄድ የአውሮፓ ህብረት አገራት ድንበሮቻቸውን ክፍት አድርገው አንዱ አባል አገር ዜጋ ወደ ሌሎቹ ከሃያ በላይ አገራት ያለምንም ችግር ይንቀሳቀሳል። አሜሪካ ብንሄድ አንድ አሜሪካዊ 54 ግዛቶችን ያለ ከልካይ መንቀሳቀስ ይችላል። በሌሎች ዓለም ክፍሎችም እንዲህ አይነት ልማድ እየሰፋ ነው። አሁን ላይ አገራት በድንበሮቻቸው ላይ ወታደር እና ዘመናዊ መሳሪያ ሳይሆን መደበኛ ፖሊስ እና የደህንነት ካሜራዎች ብቻ ነው ያላቸው። አንዳንድ አገራት በድንበሮቻቸው ላይ የግለሰብ ቤት በማረፉ የሰውየውን ቤት ሳይነኩ ቀጭን መስመር በማስመር ብቻ ወሰናችን ይሄ ነው ብለው ሲወስኑ እና በሰላም ኑሮራቸውን ሲቀጥሉም አይተናል። ተቋማቶቻቸው አጥር አልባ፤ የዜጎቻቸው መኖሪያም እንዲሁ ቅጽር አልባ ናቸው። በአጭሩ የድንበር ዘመን እያለፈ ነው።

እኛ ጋር ነገሩ በተቃራኒ ነው። ዛሬም ቢሆን ሰዎች ድንበር በጣም ይወዳሉ። ረገኘዥም አጥሮች ፤ የአጥር ሽቦ ፤ ተናካሽ ውሾች ወዘተ አሁንም አሉን። ተቋማቶቻችን በፌደራል እና በክልል የጸጥታ ኃይሎች ከዚያም በተቀጣሪ ጥበቃዎች ይጠበቃሉ። በክልሎች መሀል ያለው ድንበር ማለቂያ በሌለው የፍተሻ ኬላ የተሞላ ነው። ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል መሄድ ከአገር ወደ አገር ከመንቀሳቀስም የከበደ ነው። አይደለም በክልሎች መሀከል በአንድ ክልል ውስጥ ያሉ ወረዳዎች እንኳን በግጦሽ መሬት እና በእርሻ ወሰን ይቆራቆዛሉ። አንዳንዶች አቅም አጥተው እንጂ ዶናልድ ትራምፕ በአሜሪካ እና በሜክሲኮ መሀከል ያቆሙትን አይነት የኮንክሪት ድንበር በክልሎች መሀል ቢያቆሙ ደስ ይላቸዋል። ይሄ አደገኛ እና አሳፋሪ ልማድ ነው።

አሁን የሚያስፈልገን ድንበር አይደለም። ወደፊትም የሚያስፈልገን ድንበር አይደለም። የሚስፈልገን የአስተዳደር ወሰን ነው። በተለይም በክልሎች መሀከል የሚያስፈልገን ይሄ ነው። የአዲስ አበባ እና የኦሮሚያ ጉዳይም በዚያ መንፈስ የተቃኘ ነው ተብሏል። ጥሩ ነው። በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ መሀከል ድንበር ኖሮ አያውቅም፤ ሊኖርም አይገባም። ያልነበረው የአስተዳደር ወሰን ነው። የሚያስፈልገውም የአስተዳደር ወሰን ነው። አሁን ተደረገ የተባለውም ይሄ ነው። ይህ ልምድ በአማራ እና በትግራይ ፤ በኦሮሚያ እና በሶማሌ፤ በአፋር እና በሶማሌ ፤ ወዘተ ያስፈልጋል።

አሁን ላይ ለዚያ ትምህርት የሆኑ አንዳንድ ተግባራት በመንግስት ደረጃ እየታዩ ነው። ለምሳሌ ያህል የአብርሆት ቤተ መጻህፍትን እንመልከት። አጥር የለውም። ስለዚህም ድንበሩ የቱጋ እንደሆነ አይታወቅም። ነገር ግን ቤተ መጻህፍቱ ወሰን አለው። በህግ በሚታወቅ ወሰኑ ላይ ቤተ መጻህፍቱ የፈለገውን ልማት ያለማል። ከዚያ ካለፈ የሚመለከተው አካል ይጠይቀዋል። ቤተ መጻህፍቱ የራሱ ወሰን እንዳለው ለማሳወቅ ግን አጥር ማጠር አላስፈለገውም። መሬቱን የሚያስተዳድረው አካልም ቤተ መጻህፍቱ ከወሰኑ አልፎ መንቀሳቀስ አለመንቀሳቀሱን ለማወቅ አጥር አያስፈልገውም። አጥር ሳይገነባ በካርታ ላይ ያለች ቀጭን መስመር ሁሉንም ነገር ግልጽ ታደርጋለች።

ቤተ መጻህፍቱ የድንበር አምሳያ የሚሆነው አጥር ስለሌለው ምን ተጠቀመ? አንደኛ ሳቢ ሆነ፤ ያ ውብ ህንጻ ከነሙሉ ክብሩ እና ከነሙሉ ውበቱ ታየ። አሁን በ4 ኪሎ ያለፈ በሙሉ ዓይኑን ቤተ መጻህፍቱ ላይ ሳያሳርፍ ማለፍ አይችልም። አጥር አልባ መሆኑ ተመልካችን ግቡብኝ ግቡብኝ የሚል ጉጉት ውስጥ እንዲገባ አደረገው። ሁለተኛው ጥቅም፤ አጥር አለመኖሩ የእንቅስቃሴ ነጻነትን ፈጠረ። ተጠቃሚዎች በፈለጉት አቅጣጫ ያለምንም ችግር ይገባሉ ይወጣሉ። ሶስተኛ በአጥር ተከልሎ ይሰራ የነበረ የማይጠቅም እና የማያምር ተግባር በሙሉ ቀርቷል። አላፊ አግዳሚ ስለሚያያቸው የቤተ መጻህፍቱ ሰዎች የማይሆን ነገር ከመስራት ተቆጥበዋል። እንዲህ እያልን ሌሎች ጥቅሞችንም ልንጠቅስ እንችላለን። ይህን እሳቤ ወደ ወረዳዎች ፤ ዞኖች እና ክልሎች ድንበር እናዙረው። እስኪ እነዚህ ክልሎች ድንበር የሚል እሳቤን ትተው ይሄን የማይጠቅም የድንበር ሀሳብ ነፍስ እንዲዘራ ያደረጉትን ኬላዎች፤ ልዩ ኃይሎች ፤ እና መሰል ነገሮች ከድንበር አካባቢ ቢያንቀሳቅሱ ምን ያህል የሀሳብ ፤ የገንዘብ፤ የእውቀት ዝውውር ሊኖር እንደሚችል አስቡት እስኪ።.... የክልሎች ሉዓላዊነት በሚል እሳቤ ክልሎች ድንበር የሚመስል ነገር ገድግደው በክልላቸው ውስጥ የሚሰሩትን ህገወጥ ተግባር ምን ያህል ሊያጋልጠው እንደሚችልም ገምቱ።.... ድንበር ባይኖር ለኗሪዎች ስለለመዱት ብዙም የማይታያቸው የክልሎች እምቅ የተፈጥሮ አቅም ምን ያህል ለሌሎች ፍንትው ብሎ እንደሚታይም አስቡት ።

ለማለት የተፈለገው ነገር አንድ ነው ..እሱም ፤ እንደ አገር የሚያስፈልገን የአስተዳደር ወሰን ነው። አስተዳደር ወሰናችንን ለማሳወቅ ደግሞ ወሰኑን ድንበር የሚያስመስል ነገር ከማድረግ መቆጠብ አለብን። ይህን ለማድረግ ደግሞ የሚያስፈልገን የመጀመሪያው ነገር የድንበርን ሀሳብ ማፍረስ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## ከፍተኛ ሙቀት በነበረባት አውሮፓ ዝናብ የቀላቀለ አውሎ ንፋስ 13 ሰዎች ህይወት ቀጠፈ



መካከለኛው እና ደቡባዊ አውሮፓ ዝናብ በቀላቀለ ኃይለኛ አውሎ ንፋስ በመመታቱ ሦስት ሕጻናትን ጨምሮ ቢያንስ የ13 ሰዎች ሕይወት አልፏል። የአብዛኛዎቹ ሕይወት ያለፈው በዛፎች መውደወቅ ምክንያት ነው። በጣሊያን፣ ኦስትሪያ እንዲሁም በፈረንሣይ ኮርሲካ ደሴት ጉዳቱ መድረሱ ተዘግቧል።

በደሴቲቱ ከባድ ዝናብ እና ንፋስ አደጋ አድርሷል። ጣሊያን ቬኒስ የሚገኘው የሴንት ማርክ ቤተ መቅደስ ደወል ግንቡ መውደቁ ተዘግቧል። አውሎ ንፋሱ በአውሮፓ ለሳምንታት የዘለቀውን የሙቀት ማዕበል እና ድርቅ ተከትሎ ተከስቷል። በኮርሲካ በሰዓት እስከ 224 ኪሎ ሜትር የሚደርስ ንፋስ ዛፎችን ነቅሎ ተንቀሳቃሽ ቤቶችን ከጥቅም ውጭ አድርጓል።

የ13 ዓመቷ ልጅ ዛፍ ወድቆባት ሕይወቷ ማለፉን ባለሥልጣናት አስታውቀዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ግለሰብም ሕይወቱ ማለፉን ተናግረዋል። አንድ የዕድሜ ባለጸጋ መኪናቸው ውስጥ ሕይወታቸው ማለፉንም አስታውቀዋል። ሌሎች ሁለት ሰዎች በባሕር ዳርቻ ላይ ሕይወታቸው አልፏል።

በአውሎንፋስ የደረሰውን ጉዳት ለመመርመር ኮርሲካ የደረሱት የፈረንሳዩ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ጀራልድ ዳርማኒን የተጨማሪ ስድስተኛ ሰው ሕይወት ማለፉን ተናግረዋል። በደርዘን የሚቆጠሩ ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል። የዓይን እማኞች አውሎ ንፋሶቹ ያልተጠበቁ እንደነበሩ እና ምንም ማስጠንቀቂያ እንዳልተሰጣቸው ተናግረዋል።

የሬስቶራንት ባለቤት የሆነው ሴድሪክ ቦኤል ለሮይተርስ የዜና ወኪል "እንደዚህ ዓይነት ግዙፍ አውሎ ንፋስ አይተን አናውቅም" ብለዋል። በፈረንሳይ አንዳንድ ደቡባዊ አካባቢዎች የኃይል መቆራረጥ ሲያጋጥም የማርሴይ ከተማ ጎዳናዎች በጎርፍ ተጥለቅልቀዋል።

በኦስትሪያዋ ካሪንቲያ ሐይቅ አቅራቢያ በወደቀ ዛፍ ምክንያት የሁለት ታዳጊ ሴቶች ሕይወት አልፏል። በተመሳሳይ ሁኔታ ተጨማሪ ሦስት ሰዎች መሞታቸውን መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል። በጣሊያኗ ቱስካኒ ክልል ሁለት ሰዎች በተለያየ ቦታ በወደቀ ዛፍ ሕይወታቸው አልፏል። በቬኒስ ሴንት ማርክ አደባባይ የካፌ ዣንጥላዎች የተነቃቀሉ ሲሆን የካቴድራሉ የደወል ማማ ጡብ መውደቁ ተነግሯል።

በቱስካኒ እና በሊጉሪያ በስተሰሜን የሚገኙ የባሕር ዳርቻ መዝናኛዎች በአውሎ ንፋሱ ተጎድተዋል።በደቡባዊ ጣሊያን ደግሞ የሙቀት ማዕበሉ ቀጥሏል። በሲሲሊ እስከ 40 ሴንቲግሬድ የሚደርስ ሙቀት ተመዝግቧል። በአልጄሪያ በተከሰተ የደን ቃጠሎ ቢያንስ 38 ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል።

በብዙ የአውሮፓ አገራት ከፍተኛ ሙቀት እና ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሳምንታት ተመዝግቧል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከፍተኛ የሙቀት ሞገድ እና አውሎ ንፋሶችን ጨምሮ አስከፊ የአየር ሁኔታዎች በተደጋጋሚ ተከስተዋል። ይህም የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ ባደረሰው ጉዳት ሳቢያ በተባባሰው የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት መከሰቱ ተነግሯል።

ከኢንዱስትሪ ዘመን ጀምሮ አንስቶ ዓለም በ1.1 ሴንቲ ግሬድ ገደማ ሙቀቷ ጨምሯል። መንግሥታት ከፍተኛ የሆነ የልቀት መጠን መቀነስ ካላደረጉ የሙቀቱ መጠን እየጨመረ መሄዱን ቢቢሲ ዘግቧል።



## ምዕራባውያን ለዩክሬን የሚያደርጉት ወታደራዊ ድጋፍ እየደረቀ መምጣቱን ጥናት አመለከተ

የአውሮፓ ኅብረት አባል ሀገራት ለዩክሬን አዲስ ወታደራዊ ድጋፍ ለማድረግ ቃል አለመግባታቸው ተነገረ። ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የተደረገ ጥናት በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ሩሲያ ወታደሮቿን ወደ ዩክሬን ከላከች በኋላ የአውሮፓ ኅብረት አባል ሀገራት ወታደራዊ ዕርዳታ ለዩክሬን ለመላክ ቃል መግባት ካቆሙ 20 ቀናት መቆጠራቸውን አመላክቷል።

በጉዳዩ ላይ መረጃ ይፋ ያደረገው በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ላይ ጥናቶችን በመሥራት የሚታወቅ ጀርመን የሚገኝ ኪየል የተሰኘ ኢንስቲትዩት ነው።እንደ ጥናቱ የኅብረቱ አባል ሀገራት ለዩክሬን የሚሰጡትን ወታደራዊ ዕርዳታ እየቀነሱ መምጣታቸውን የሚያሳይ ምልክት እየታየ ነው።

ኢንስቲትዩቱ ለቭላድሚር ዜሌንስኪ የቀረበውን ዓለም አቀፋዊ ወታደራዊ አቅርቦት ፣ የገንዘብ እርዳታና ሰብአዊ ድጋፍ ሲከታተል እና በዝርዝር ሲለካ ቆይቷልም ነው የተባለው። የጥናቱ መረጃ እንደሚያሳየው ከአውሮፓ ለዩክሬን የሚደርሰው ወታደራዊ ዕርዳታ ከሚያዝያ ወር መጨረሻ ጀምሮ በሚታይ መልኩ እየቀነሰ መምጣቱን ፋርስ ኒውስ እና ፖለቲኮ ዘግበዋል።

አንድ የአሜሪካ የመረጃ ምንጭ በበኩሉ ከብሪታኒያ ፣ፖላንድ እና አሜሪካ ለዩክሬን የሚላከውን ወታደራዊ ዕርዳታ ባለማድረስ ጀርመንን እና ፈረንሳይን ተጠያቂ ማድረጉም ኤፍቢሲ ዘግቧል።

## መጋቢ አዕምሮ

# ኢላማ፤ ዓላማ

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

የትምህርት ዘመኑ አልቆ ተማሪዎች ከሰፈራቸው ተገናኝተው እየተጫወቱ ነው።የክረምቱ ጉም፤ ዝናቡ፤ የልጆቹ ከፍተኛ የጨዋታ ፍላጎት፤ የጎርፉ ድምጽ ወዘተ ልዩ ስሜት የሚፈጥሩባቸው አባት ደግሞ በሰፈሩ ውስጥ ይገኛሉ።እኒህ አባት በበጋ ወቅት "ምነው ክረምቱ በመጣና ሰፈሩን ሕይወት በዘሩበት" በማለት ልጆች በልዩ ሁኔታ የሚደምቁበትን ክረምትን ይናፍቃሉ።ሰፈሩ ሕይወት የሚኖረው ለእርሳቸው ልጆች ቀኑን ሙሉ ሲሯሯጡና ሲጫወቱ ማየት ነው።

እንሆ ክረምት ሆኖ አዛውንቱ ከዘራቸውን ይዘው ቤታቸው በር ላይ ካላቸው ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ፊትለፊታቸው ባለው ሜዳ ውስጥ የሚቦርቁትን ልጆች ይመለከታሉ።ሲጫወቱ ነፍሳቸውን አያውቁም፤ የልጅነት ጨዋታ።ቀኖች እየጨመሩ ሲሄዱ ሁሉም ልጅ ወደ ራሱ መስመር ውስጥ ገብቶ ይበታተናል፤ ልጆቹ ዛሬ እርሱን አያውቁም።በሕይወት የዓላማ ጉዞ ምናልባትም ነገ በተለያየ ጎራ ሆነውም የሚፋለሙ ሊሆኑ ይችላሉ።በምናባቸው አዛውንቱ የእርሳቸውን ዘመን የልጅነት ጓደኞቻቸውን እያሰቡ ነጎዱ።በሕይወት ጉዞ በተለያየ አቅጣጫ የተመመውን የእርሳቸውን ትውልድ።

አዛውንቱ ከእለታት በአንዱ ቀን ከፊታቸው የሚቦርቁትን ልጆች ሰብሰው አብረዋቸው ማውራት ፈለጉ።ከልጆቹ መካከል ከጫዋታው ውስጥ የእርሳቸውን የልጅ ልጅ ተጣሩ፤ "ዱጬ፤ ዱጬ" እያሉ ተጣሩ።"ዱጬ" እርሳቸው የልጅ ልጃቸውን የሚጠሩበት የቤት ስሙ ነው።ዱጬ "አቤት አባቴ" ብሎ እየሮጠ ወደ አያቱ ቤት ሄደ።"እስኪ ልጆቹን ሁሉ ወዲህ ጥራልኝ" አሉት።"እንዴ ምነው አባ፤ አንተም ወደቤት ግቡ ብለህ ጨዋታችንን ልታቋርጠን ባልሆነ?" አለ።አዛውንቱም "አይደለም ዱጬ ለሌላ ጉዳይ ነው" በማለት ምላሽ ሰጡት።ዱጬም የተሰጠውን ትእዛዝ ተከትሎ በጨዋታው እብድ ያሉትን ልጆች ተጣራ።አንዳንዶቹ ከጨዋታው ስልተቋረጡ ተነጫነጩ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ምን ይሆን ብለው ወደ አባባ ዘንድ ፈጠኑ።

አባባ ምን ሊሏቸው እንደሆነ ጓጉተው ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ አባባ ጋር ደረሱ።አባባም "እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ በመጀመሪያ ማንን ልጠይቅ አሉ?" ሁሉም "እኔን፤ እኔን" እያሉ እጃቸውን አወጡ፤ ልክ እንደ ትምህርት ቤት።አዛውንቱም "ቆይ ተረጋጉ እንጂ ከእድሜ ትንሹ ማንነው? ከእርሱ ጀምረን ወደ እድሜ ትልቁ እንሄዳለን" ብለው ሁሉንም በእድሜ ቅደም ተከተል አሰለፏቸው።

ከተሰበሰቡት መካከል በእድሜ ትንሹን ጠየቁት "ልጄ እያለቀ ባለው ዓመት ውስጥ ደስ ያለህ ነገር ምንድን ነው?" በማለት።ልጁም በልጅነት አንደበቱ "እኔ በጣም ደስ ያለኝ የልደት ቀኔ ሲከበር አክስቴ ከገጠር መምጣቷ ነው።ለእኔ ብላ ብዙ መንገድ ተጉዛ መምጣቷ በጣም ደስ ብሎኛል።ደግሞም ሳይክል ስለገዛችልኝ በጣም ደስ ብሎኛል"ሲል መለሰ።

ሁለተኛው ልጅ ደግሞ "አንተስ እያለፈ ባለው ዓመት ውስጥ በጣም ያስከፋህ ነገር ምን ነበር?" ሲባል ተጠየቀ፤ ልጁም "እኔ በጣም ያስከፋኝ አጎቴ ለጦርነት ሄዶ አለመመለሱ ነው።አጎቴ በጣም ይወደኛል ደግሞም አባባ እንደሚያውቁት አባቴና እናቴ ሲጣሉ የሚያስታርቃቸው እርሱ ነውና የእርሱ መሞት በጣም አስከፍቶኛል" ሲል መለሰ።

ሦስተኛው ልጅ ደግሞ "አንተ ደግሞ በዓመት ውስጥ ካደረከው ነገር ልዩ ስሜት የሚፈጥርብህ የቱነው?" ተባለ እርሱም "በዚህ ዓመት ውስጥ ደስ የማይሉ ነገሮችን አሳልፌያለሁ።ነገርግን በጦርነት ለተፈናቀሉ እኛ ተማሪዎች እንድናዋጣ ተጠይቀን አባቴና እናቴ በሰጡኝ ገንዘብ ፓስታ ገዝቼ መስጠቴ ደስ ብሎኛል።ደግሞም በትምህርቴ ጥሩ ውጤት ስላመጣሁም ደስ ብሎኛል።ከሁሉም በላይ ግን እኔ መማር ያለብኝ አንደኛ ለመውጣት ብቻ ሳይሆን የደረጃ ተማሪ ከመሆን ባሻገር የሰዎችን ችግር መፍታትን ግብ አድርጎ መንቀሳቀስ አስፈላጊ እንደሆነ ነው።ይህም አባቴ የመከረኝ ትልቅ ምክር ልቤ ውስጥ የተመዘገበበት ወቅት ስለነበረ ደስ ብሎኛል፡፡" በማለት ምላሽ ሰጠ።

የልጆቹ ደስታም ሆነ መከፋት ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚያገናኝ ጉዳይ መሆኑን አዛውንቱ አስተዋሉ።ምድር ላይም የሰው ልጅ ምንያህል እርስበእርሱ የተሳሰረና ደስታውም ሆነ ሃዘኑ በአብሮነት ጉዞ ውስጥ መሆኑን አሰላሰሉ።የሰው ልጅ አቅዶ በመተግበር ውስጥ ያለው ጉዞው ትርጉም የሚሰራው ሰውን ማእከል አድርጎ ሲከናወን መሆኑን ከራሳቸው ጋር አወሩ።ኢላማም ሆነ ዓላማ የሚሳኩት ሰውን ይዞ ከሰው ጋር ተሆኖ ሲተገበር ብቻም እንደሆነ በሃሳባቸው ብዙ ዓመታትን ወደ ኋላ ሄዱ፤ ጊዜ ቢኖራቸው ወደፊት ሊኖሩ የሚወዱትን ኑሮም አሰቡ።ግን ብዙም ጊዜ እንደሌላቸው ያውቃሉ። የኢላማ እና የዓላማ ሕይወትን በመረዳት ውስጥ የሚኖሩ ሕይወት ግን ቀናት አያልቅበትምና ሊኖሩት ተመኙት።

**ኢላማ**

ለአደን የተሰማራ ሰው ኢላማውን አስተካክሎ አንዳች ድል ይዞ መመለስ ፈልጎ ወደ ጫካው ውስጥ ይገባል።ኢላማው በራሱ ዓላማ አይደለም፤ ዓላማው ኢላማው ሲሳካ የሚያሳካው ነው።ኢላማውን በትክክል ከሰነዘረ ፤ ኢላማውን መትቶ አውሬውን ከጣለና ባዶ እጁን ከተመለሰ አንዳች ችግር እንዳለበት ይቆጠራል።ምክንያቱም ሕይወቱን አስይዞ የተሰለፈበት የኢላማ ፍልሚያው አላማ ገድሎ መመለስ አይደለምና።

በሕይወት ጉዞ ውስጥ ሰዎች ኢላማ የሚያደርጉት ብዙ ነገር አለ።ጎበዝ ተማሪዎች ኢላማ አድርገው የደረጃ ተማሪ ለመሆን ያጠናሉ።ካሰቡበት ደረጃ ተንሸራተው ሲገኙ አንዳች የጎደላቸው ነገር እንዳለ ይሰማቸዋል።በአንድ ወቅት በተማሪዎች የውጤት መቀብያ ቀን አንዱ ታዳጊ ተማሪ ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል።አንዳች ነገር እንደተፈጠረ እምባው ያሳብቅበታል።ምክንያቱ ደግሞ በአንድ ማርክ ተበልጦ ደረጃውን ማጣቱ ነበር።ኢላማ ያደረገው ነገር ነበርና ኢላማውን መምታት ባለመቻሉ የተፈጠረበት ሃዘን።

ከግለሰብ አልፎ የኢላማ ነገር በተቋማት ውስጥም ይሰራል።ተቋማት ግብ አስቀምጠው እያንዳንዱ ሰራተኛ እንደ ግለሰብ፤ ከእያንዳንዱ የስራ ክፍል እንደ ክፍል፤ ከአጠቃላይ ድርጅቱ እንደ ድርጅት ኢላማ ይደረጋል።ኢላማውም ይሳካ ዘንድ የተለያዩ ተግባራት ይከናውናሉ።ኢላማ በአግባቡ ታልሞ ውጤት ሲመጣ ደስታ ይሆናል።ኢላማ የተደረገው ነገር ሳይሳካ ሲቀር ደግሞ ምክንያቱ ይገመገምና የማስተካከያ መንገድ ይቀየስለታል፤ በዚሁ መንገድ የኢላማ ጉዞ ይቀጥላል።

ኢላማ ማድረግን እንደ ባህል በአደጉት ሀገራት ዘንድ የተለመደ ነው።ጃፓኖች የማኔጅመንት ሳይንስ እንዲዳበር የአሰራር ማሻሻልን በየጊዜው በማድረግ ኢላማን መምታት የሚቻልበት ደረጃ ላይ መድረስ እንዲቻል ምሳሌ የሚሆኑ አሰራሮችን ለዓለም አስተዋውቀዋል።ኢላማን ትኩረት ያደረጉ በጥራት፣ በሰው ሃይል አስተዳደር፣ በንግድ አስተዳደር፣ በንብረት አያያዝ ወዘተ ውስጥ አሰራሮችን አስተዋውቀው ውጤታማም ሆነዋል።

አንባቢው አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር ኢላማን በማለም ልምድ ያለው ሊሆን ይችላል።አንዳንዱ ሰው የአዲስ ዓመት እቅድን በልኩ አቅዶ ተግብሮ ራሱን ገምግሞ የመሸለም ልማድም አለው።በሂደት ውስጥ ከዛሬ ነገን በስራ መቀየር።ኢላማ እዚህ ውስጥ ያለው ድርሻ ትልቅ ነው።ኢላማ የምናደርገው ነገር ግልጽ ነው።በቁጥርም፤ በስፋትም፤ በርዝመት ወይንም በሆነ አንዳች መለኪያ አማካኝነት የሚለካ ስለሆነ።

ኢላማ አድርጎ ቀኑን በሰዓት ከፋፍሎ የሚንቀሳቀስና ቅርጽ በሌለው አካሄድ ቀኖቹን ተቀብሎ የሚሸኝ ተመሳሳይ ውጤት ሊኖራቸው አይችልም።ተማሪው፣ አርሶአደሩ፣ ነጋዴው፣ ሰራተኛው ወዘተ በኢላማ ውስጥ ስራቸውን ያከናውኑ ዘንድ ይመከራል፤ በዚህ መንገድ የሚያከናውኑት ለውጤት ደርሰው ይታያል።ከፍ ያለው ጥያቄ ግን አላማ ነው፤ ከኢላማ የሚገዝፈው፤ የኢላማ ድምር ውጤት የሚገልጸው።በትውልዱ ውስጥ ቦታ የተነፈገ የሚመስለው በኢላማ ተሸፍኖ የሚኖረው፤ ዓላማ!

**ዓላማ**

‹‹ማርክ ትዋይን›› የተባለ አሜሪካዊ ፀሀፊ "በሕይወት ውስጥ ወሳኝ የሆኑት ሁለት ቀናት ሲሆኑ፤ አንደኛው የተወለድክበት ሌላኛው የሕይወትህን ዓላማ ያገኘህበት ነው" ይላል።ዓላማ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ቦታ በሚገባ የሚያሳይ አባባል ነው።

የስድብ ጥሩ ባይኖረውም "አላማ ቢስ" የሚል ስድብ የሰዎችን ስሜት የመንካት አቅሙ ከፍተኛ ነው።ማንም ሰው ዓላማ ቢስ እንደሆነ ተደርጎ እንዲቆጠር አይፈልግም።በዘመናት መካከል ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ የደረሰችበት ምዕራፍ ላይ ለመድረስ ያለፉ በርካታ ስልጣኔዎች ነበሯት።እያንዳንዱ ዘመን ይዞት የነበረው ስልጣኔ በታሪክ መዝገብ ውስጥ ተጽፎ ከሚገኘው ባሻገር በእያንዳንዱ አካባቢ አሻራው ዛሬም ድረስ ይታያል።ኢትዮጵያውያን አንድ ሰው ዓላማ ብሎ የያዘውን ነገር ዳር በማድረስ ውስጥ የሚሰጡት ሙገሳ ወይንም አድናቆት የታሪካችን አካል ነው።ከዚህ አንጻር "አላማ ቢስ" የሚለው ቃል ለአንድ ኢትዮጵያዊ ስሜትን የሚጎዳ ቢሆን ሊገርመን አይችልም።

ቤተሰቦች ልጆቻቸው ትምህርትን በአግባቡ እንዲያጠኑ፤በአግባቡ እንዲከታተሉ ሲመክሩ ትምህርትን እንደ ዓላማ አድርገው በማቅረብ ነው።ሴት ልጅ ከሆነች ደግሞ ከዓላማዋ ሳትዘናጋ ትምህርቷን ዓላማ አድርጋ እንድትማር ትመከራለች።ለኃላፊነት ብቁ ሳይሆን ወደ ጾታዊ ግንኙነት መሄድም እንዲሁ ከዓላማ መስመር መሳት ተደርጎም ይቀርባል።አባቶቻችን በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ገብተው ሳይማሩ ከግልሕይወታቸው ተነስተው እስከ ሀገር ድረስ በዓላማ ውስጥ የመኖርን አስፈላጊነት ይገልጻሉ።

ባለንበት ዘመን ደግሞ ዓላማ የሚባለው ነገር ፈጽሞውኑ የጠፋ ነው ባንል እንኳን እየደበዘዘ የሄደበት ነው።ዓላማ እጅግ ጠቦ በየትም በኩል ተደርጎ ገንዘብ ላይ መድረስ የሚለው የሕይወት ዘይቤ የሰፋ ይመስላል።በስራ መንገድ ገንዘብ ላይ መድረስ የሚጠበቅ ቢሆንም ባልተገባ ስራ መድረስ እንዲሁም መነሻ ዓላማቸው ገንዘብ ባልሆኑ ዘርፎ እንደ ሃይማኖት፤ ፖለቲካ፤ ህዝብ አስተዳደር ወዘተ ከብዙሃን ጋር በሚሰጥ አገልግሎት ውስጥም ታልፎ ገንዘብ ጋር መድረስ ግብ ከሆነም ሰነባብቷል።ይህ ደግሞ ያሳዝናል።ዓላማን በገንዘብና በእውቅ ለመለካት የተሄደበት ርቀት ብዙ እንደሆነ በግልጽ የሚታይበት ወቅትም ነው።

መነሻችንን ዒላማ ያደረግነው በዒላማ ስሌት ዓላማ እየወደቀ ስላለ ነው።ገንዘብ የማግኘት ኢላማ ወይም ግብ ያለው ሰው በማንኛውም መንገድ አድርጎ ገንዘብ ጋር መድረስን ከሆነ የሚያስበው በመደበኛ ንግድ ገንዘብ ጋር ከመድረስ በኮንትሮባንድ መንገድ ላይ መሄድን ሊመርጥ ይችላል።በሙስና ገንዘብ ላይ መድረስን ኢላማ ያደረገ ሰው ካለበት አንድ ኃላፊነት ወደ ሚከተለው ሲያድግ ኢላማው በተጨማሪ ኃላፊነት ህዝብን ማገልገል ሳይሆን ለበለጠ ሌብነት ልምምድ ማድረግ ላይ ይሆናል።

የዒላማ ሕይወት በዓላማ ውስጥ ሲሆን፤ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን የሚያስረዱ አያሌ የማኔጅመንት ሳይንስ ጽንሰሃሳቦች አሉ።እውነታው ግን ዓላማ የለሽ በመሆን ውስጥ የበቀሉት ኢላማዎች ትርጉማቸው ማትረፍ እየመሰሉ መክሰር፤ ማግኘት እየመሰለ ማጣት፤ መገኘት እየመሰለ መጥፋት ነው።‹‹ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ›› ሊባል የሚችልባቸው ክስተቶች በየፈርጣታው ከዓላማ አንጻር በዝቷል።ያለእጅ መንሻ ውጤት ማግኘት በማይታሰብበት ዘመን ውስጥ ስንኖር በተለመደው መንገድ ወጥቶ የሚገባው ዓላማውን ለማሳካት በትክክለኛው መንገድ ላይ መሆን አዋጭ እንዳልሆነ ያስባል።በዚህም ተስፋው እየተሸረሸረ ሊሄድ ይችላል።



**የዓላማ ሕይወትን መኖር**

ዓላማን ውስብስብ አድርጎ ከማቅረብ በቀላሉ "ሰዎችን ማእከል አድርገን ልንኖረው የተገባው ሕይወት" ብለን ልናየው እንችላለን።በምድር ላይ የምንኖረው ኑሮ በጊዜ የተገደበ መሆኑ እሙን ነው።ሰው በመሆናችን በውስንነት ውስጥም እንኖራለን።በዚህ ሁኔታ ምድር ላይ ስንኖር ዓላማ ትልቁ ስንቃችን ነው፤ ልንኖር የተገባውን ሕይወት ላይ ያደረስነው ውሳኔም ነው።

እንደ ግለሰብ በውስጣችን ያለውን ተሰጥኦ ተጠቅመን ልንኖር የምንፈልገውን ሕይወት ለመኖር እውቀትን ማእከል አድርገን ስንመላለስ እርሱ ዓላማ ነው።የዓላማ ሕይወት ራስን ፈልጎ በማግኘት ለሌሎች የሚመነዘር ማድረግ ነው።አንድ ሰው በቁጥር አንድ ቢሆንም ለራሱ በቂውን ጊዜ ሰጥቶ ራሱን ፈልጎ ባገኘበት ርቀት ለብዙዎች የሚመነዘር ሊሆን ይችላል።የዓላማ ሕይወት ሰዎች ግራ ተጋብተው በሚኖሩበት ሁኔታ ውስጥ የተረጋጋን ሕይወት እንድንኖር የሚረዳ ነው።ራስን ፈልጎ ማግኘት በውጤቱም ለሌሎች መድረስ ነውና፡፡

ሮበርት ኤፍ. ኬኔዲ "የሕይወት ዓላማ ነገሮችን መልካም ለማድረግ በሆነ መንገድ የምናደርገው አስተዋጾ ነው" በማለት ዓላማን ከራስ አጥር ባሻገር መመልከት እንደሆነ ይገልጹታል።ይህ ሲሆን ለውስጥ ጩኸት ምላሽ መስጠት፤ ከፈጣሪም ከተፈጥሮም ጋር ታርቆ የመኖር ሕይወትን ይከተላል።ተልእኮ አድርጎ የሚወሰድን ነገር ዳር ማድረስ የሚያስችል ሕይወትም ይሆናል።

በመቃብራችን ላይ የሚገኙ ሰዎች ምን አድርገን እንዳለፍን ቢያውቁ ደስ ይለናል።የተጣላን አስታራቂ፣ ተስፋ ላጡ ተስፋን መመለስ፣ የተራቡትን የሚያበላ፣ በስራው ታታሪ ሆኖ ብዙ የስራ እድል የፈጠረ፣ በስፖርቱ ዓለም ተጽእኖ ፈጥሮ ለሰዎች በስፖርት መዝናኛ ምክንያት ሆኖ ማለፍ ወይንስ ምን? ፒካሶ እንዲህ ይላሉ። ‹‹የሕይወት ትርጉም ስጦታህን ማወቅ ነው።የሕይወት ዓላማ ደግሞ ስጦታህን ለሌሎች መስጠት፡፡›› እናም ዓላማ በተቻለው መጠን ራስን ማእከል ከማድረግ ወጥቶ ሌሎችን የሚያስብ መሆን ነው።

አንድ ሰው ነግዶ ገንዘብ ማግኘት ቢፈልግ እንደ ዓላማ መያዝ ያለበት በሚሰራው የንግድ ስራ ሰዎችን የሚጠቅምበትን ነው።ለአርሶአደሩ የሆነ እቃ አቅርቦ የአርሶአደሩን ችግር ፈቶ ገንዘብ ማግኘት ሲሆን፤ ትርጉሙ እንዲሁ ነግዶ ገንዘብ ማግኘት ከሚል ዓላማ ይሻላል።ገንዘብ ማግኘት ኢላማ ሲሆን የሚሰራው ስራ የሚጨምረው እሴት ካለ ዓላማ ይሆናልም። ዛሬ በኢላማ ውስጥ በመኖር ብቻ ያልሞላነውን የሕይወት ጉዞ በዓላማ በመኖር ምልዑ እናደርገው ዘንድ እድል አለንና የተግባር እርምጃን ስለሰው ብለን እናድርገው።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የካበተ ልምድና ዕውቀትን እንደ መነሻ ካፒታል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምሮ ቢዝነስ ነክ ነገሮች በእጅጉ ያስደስታቸዋል ፤ ይማርካቸዋል።ቢዝነስ ሲባል ታዲያ ትላልቆቹን ብቻ አይደለም።ከትንሹ የጉልት ንግድ ጀምሮ ያሉ የቢዝነስ ሥራዎችን አጥብቀው የሚወዱና የሚያከብሩ ናቸው።ቢዝነስ የሰው ልጆችን በሙሉ የሚ ያገናኝ፣ የሚያሰባስብ፣ የሚያስተዋውቅ የሥራ ዘርፍ መሆኑን ይገልጻሉ፤ እጅግ የተከበረና የተባረከ ሥራ አርገውም ይመለከቱታል።

በየአካባቢው የሚጀመሩ ትናንሽ ንግዶች ዓለም አቀፍ ወደሆነው ንግድ ማደግ የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ የንግድ ዓለምን ማነቃነቅ የሚችል ኃይል አላቸው። የዓለም አገራት በሙሉ ሁሉም ነገር የላቸውም፤ አንዱ ያለው ሌላው የለውምና አገራት የሌላቸውን ካላቸው በመውሰድ፣ እነሱ ያላቸውን ደግሞ ለሌሎች በማካፈል ፍላጎቶቻቸውን ያሟላሉ።በዚህ ምክንያት የሰው ልጆች በአንድ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው የሚቀባበሉትና የሚከፋፈሉት እንዳለ በቢዝነስ ውስጥ ባላቸው ቆይታ መረዳት የቻሉ ናቸው።

ለበርካታ ዓመታት በመንግሥት መስሪያ ቤት አገልግለዋል፤ በግላቸውም በተለያዩ የቢዝነስ ሥራዎች እየተሳተፉ የሚገኙት የእለቱ እንግዳችን የእርካብ ትራንዚት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መስራችና ባለቤት ወይዘሮ እመቤት ታፈሰ ናቸው።

ወይዘሮ እመቤት፤ በመንግሥት መስሪያ ቤት በተለይም በኢትዮጵያ ቆዳ ፋብሪካ ለረዥም ዓመታት በሥራ አስኪያጅነት አገልግለዋል፤ በኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማህበርም ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው አገልግለዋል።

በአሁኑ ወቅትም በሥራ ዘመናቸው ያካበቱትን ልምድና ዕውቀት መነሻ ካፒታላቸው በማድረግ በግላቸው በከፈቱት እርካብ ትራንዚት አማካኝነት በወጪ ገቢ ንግድ በርካታ አገልግሎቶችን ለበርካታ ወገኖች ተደራሽ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በቢዝነስ ውስጥ ረዘም ያለ ጊዜን ያስቆጠሩት ወይዘሮ እመቤት፤ ተወልደው ያደጉት በአዲስ አበባ ከተማ ነው።የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ ያገኙ ሲሆን፤ የተለያዩ የምስክር ወረቀቶችን እና ዲፕሎማዎችን ደግሞ በአካውንቲንግ አግኝተዋል።ከልጅነት ዕድሜያቸው አንስተው ለቢዝነስ የነበራቸውን ፍላጎት ተግባራዊ ለማድረግ ተማሪ እያሉ ጀምሮ በተለይም እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች በእጅጉ ያጓጓቸው እንደነበር በማስታወስ በዘርፉም በርካታ መጻህፍት ስለማንበባቸው አጫውተውናል።

ስለኢትዮጵያ የወተትና የወተት ተዋጽኦ እንዲሁም የስጋ ምርት በነበራቸው ጥልቅ ንባብ ብዙ ዕውቀት መቅሰም ችለዋል።ለእንስሳት ካላቸው ቅርበት የተነሳ የቆዳ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሲቀጠሩ በጣም ደስተኛ ሆነውም ነበር።ረዘም ላለ ዓመታትም በዚሁ ዘርፍ ቆይተዋል።‹‹ቆዳ በተፈጥሮ ከእንስሳት የምናገኘው አስተዋጽኦ ነው›› የሚሉት ወይዘሮ እመቤት፤ እንስሳት የሚሰጡት ጥቅም ዘርፈ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ለእንስሳት ልዩ ፍቅርና እንክብካቤ አለኝ ይላሉ፡፡

ከእንስሳት የሚገኘው ቆዳ የተለያዩ ሂደቶችን አልፎ ጋርመንት ውስጥ ገብቶ በፋሽን ኢንዱስትሪ አልፎ ዓለም ለብሶት ሲታይ በጣም ያስገርማልም ይላሉ።በተለይም የኢትዮጵያ ቆዳ በዓለም ላይ እጅግ ተፈላጊና ተመራጭ እንደሆነ የሚያነሱት ወይዘሮ እመቤት፤ በወቅቱም ትላልቅ የተባሉ ኤግዚብሽኖች የሚካሄዱባቸውን በርካታ የዓለም አገራት የማየት ዕድል አጋጥሟቸዋል፤ ትላልቅ የተባሉትን የሌዘር ኢንዱስትሪዎችን ጎብኝተዋል።በዚህም ዓለም ቆዳን እንዴት እየተጠቀመበት እንደሆነ መረዳት በመቻላቸው የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ እንዲያድግ ከፍተኛ ምኞት ነበራቸው።ምኞታቸው እንዲሳካም በነበራቸው ቆይታ ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉ ስለመሆናቸው ያስታውሳሉ።

የኢትዮጵያ ቆዳ በተፈጥሮ የታደለና እጅግ ተመራጭ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተለይም የጎጃም፣ ጎንደር፣ ሲዳሞና ኢሊባቦር አካባቢዎች የሚገኘው ቆዳ በዓለም ገበያ እጅግ ተፈላጊና ተመራጭ ይላሉ ወይዘሮ እመቤት። የፍየል ቆዳን በሚመለከትም ከባቲ ፍየሎች የሚገኘው ቆዳ በዓለም ላይ የትም ቦታ የማይገኝ እንደነበርና ዓለም አለኝ የምትለው የቆዳ ውጤቶችን የምታገኘው ከኢትዮጵያ ስለመሆኑሙም ይናገራሉ።


ወይዘሮ እመቤት ታፈሰ

‹‹የዓለምን ትኩረት መሳብ የቻለውን ይህን በተፈጥሮ የተሰጠንን እምቅ ሃብት በአግባቡ አልተጠቀምንበትም›› የሚሉት ወይዘሮ እመቤት፤ ዛሬ የኢትዮጵያ ቆዳ ከደረጃው ወርዶ በየቦታው ተጥሎ ሲመለከቱ በእጅጉ ያዝናሉ።እዚህ ደረጃ ሊደርስና ሊያስቆጭ እንደሚችልም በወቅቱ የነበራቸውን ስጋት ለሚመለከታቸው አካላት በሙሉ በጽሁፍ ሲያደርሱ እንደነበርም ያስታውሳሉ፡፡

እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች እጅጉን የሚያጓጓቸው ወይዘሮ እመቤት፤ ለእነዚህ ውጤቶች ልዩ ፍቅር እንዳላቸውም ይገልጻሉ።ለበርካታ ዓመታት የመሩትን የኢትዮጵያ ቆዳ ፋብሪካ ለቀው በግል ሥራ መሠማራት ሲያስቡ ታዲያ ለዘርፉ ካላቸው ፍቅር የተነሳ የመጀመሪያ ምርጫቸው ያደረጉት በቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ መሰማራት ነበር።ይሁንና በተለያዩና ውጫዊ በሆኑ ምክንያቶች ፍላጎታቸው ሳይሳካለቸው ቢቀርም፣ ሌሎች ውስጣዊ ፍላጎቶታቸውን በማዳመጥ ምላሽ መስጠት ችለዋል፡፡

ማንም ሰው ቀልጣፋና መልካም የሆነ አገልግሎት ሲሰጠው እንደሚደሰት ሁሉ ወይዘሮ እመቤትም ይህን ሰዎችን በብዙ ሊያስደስትና ሊያረካ የሚችለውን አገልግሎት የመስጠት ሥራ ለመሥራት ተዘጋጅተው ወደ ሎጅስቲክስ ሥራ ተሰማሩ።በድጋሚ ውስጣቸው የሚመኘውን ሥራ ለመሥራት ወደ ሎጅስቲክስ ዘርፍ ሲያመሩ ታዲያ ኢትዮጵያ በዘርፉ እጅግ ወደኋላ መቅረቷን በመረዳትም ነው።

ሰዎች በሚሰጡት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ምክንያት የሚያገኙት በርካታ ጥቅሞች እንዳሉ ሁሉ አገልግሎት የሚያገኘው አካልም በሚያገኘው አገልግሎት ልክ ተጠቃሚ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል የሚሉት ወይዘሮ እመቤት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ክፍተት ስለመኖሩ ብዙዎች የሚስማሙበት እንደሆነና እርሳቸው ደግሞ በተደጋጋሚ የገጠማቸው ጉዳይ በመሆኑ ነው ወደ ሎጅስቲክስ ዘርፍ የገቡት፡፡

‹‹አገልግሎት ፈልጌ በሄድኩባቸው አብዛኞቹ ቦታዎች የምፈልገውን አገልግሎት በተገቢው መንገድ አላገኘሁም›› የሚሉት ወይዘሮ እመቤት፤ ለግላቸው ሥራ በሄዱበት ቦታ ሁሉ ያጡትን አገልግሎት እኔ ብሆን እያሉ ይቆጩ እንደነበርና የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ምን ባደርግ ይበጃል፤ እኔ ያልረካሁበትን አገልግሎት ሌሎችን እንዴት ማርካት እችላለሁ በማለት ያወጡና ያወርዱም ነበር፡፡

በእነዚህና መሰል ገፊ ምክንያቶች ወደ ሎጅስቲክሱ የገቡት ወይዘሮ እመቤት፤ በተለይም በዓለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ኢትዮጵያ ጥራት ያለው አገልግሎት በወቅቱ ባለማድረስና መረጃ ባለመስጠት ብዙ ጊዜ ወቀሳ ይደርስባት ስለመሆኑ ያስታውሳሉ።በዚህ ምክንያት ደግሞ ዓለም አቀፍ የንግድ ሂደቱን ይደናቀፋል ስለዚህ ለሌሎች የሚከፈለው ዋጋ ለኢትዮጵያ አይገባትም በማለት በዓለም አቀፍ ንግዱ ማግኘት የሚገባትን ገቢ እንዳታገኝ ሆና ቆይታለችም ይላሉ።

አንድን ምርት ከተመረተበት ቦታ አንስቶ እሴት በመጨመርና ወደ መጨረሻው ተጠቃሚ ለማድረስ የምንሄድበት መንገድ የተመቻቸ እንዲሆን የግድ ነው።ይህም ማለት በፍጥነት፣ በጥራትና በጊዜ ማከናወን ሲሆን ይህን ማድረግ ሲቻል፤ አቅራቢው ተወዳዳሪና የተሻለ ተጠቃሚ ይሆናል።የመጨረሻ ተጠቃሚውም እንዲሁ በሚያገኘው ቀልጣፋ አገልግሎት እርካታን ከማግኘት ባለፈ እርሱም ተጠቃሚ መሆን ይችላል።ይህም ማለት ሻጩም ሆነ ገዢው ከሚከውኑት ንግድ የሚገባቸውን ጥቅም ያገኛሉ ማለት ነው፡፡

በዚህ እሳቤ የሎጅስቲክስ ዘርፉን የተቀላቀሉት ወይዘሮ እመቤት፤ በተለይም የቡና ወጪ ንግድን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እያሳለጡ ይገኛሉ።አብዛኞቹ ደንበኞቻቸው ቡና ላኪዎች ይሁኑ እንጂ ወደ ውጭ ገበያ ከሚላከው ቡና በተጨማሪም የተለያዩ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ ለሚያስመጡ አስመጪዎችም አገልግሎቱን ይሰጣሉ።

በሎጅስቲክስ አገልግሎት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የተለያዩ ምርቶችን ከጅቡቲ በማንሳት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋሉ።ወጪ ምርቶችንም እንደዚሁ ከደንበኞቻቸው በመረከብ አስፈላጊውን ሂደት በመከተል በጥሩ ሁኔታ ወደ ውጭ ገበያ ይልካሉ።ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡትም ሆነ ለውጪ ገበያ ለሚላኩ ምርቶች ድልድይ በመሆን የሚያሳልጡት ወይዘሮ እመቤት፤ የሚሰጡት አገልግሎት ጊዜውን የጠበቀና ቀልጣፋ በመሆኑ ተመራጭነታቸው እየሰፋ መጥቷል።

ከዚህ ቀደም ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚሰበሰበው ቡና አዲስ አበባ ለመድረስ ነጋዴው ይፈተን እንደነበር በማስታወስ፤ ሎጅስቲክስ ይህን እና መሰል ችግሮችን በማቃለል ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ስለመሆኑም ይናገራሉ።ይህም በወጪ እና ገቢ ንግዱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀሬ እንደሆነ ወይዘሮ እመቤት ይናገራሉ።ይህ ደግሞ በዓለም አቀፍ ገበያ የሚኖር ተወዳዳሪነትን ይቀንሳል፤ ስለዚህ የሎጅስቲክስ መሟላት በተለይም ለወጪ ገቢ ንግድ ወሳኝ ነው ይላሉ።

አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ እንደሆነ ያነሱት ወይዘሮ እመቤት፤ ጅቡቲ ላይ ባሏቸው ወኪሎች አማካኝነት የላኪውን እና የአስመጪውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ከጉምሩክ ጋር ባላቸው የኔትዎርክ ግንኙነት እንዲሁም ከጅቡቲ ውጭ ከኬኒያና ከሌሎችም አገራት ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት አገልግሎቱን ይሰጣሉ።በሚሰጡት ቀልጣፋ አገልግሎትም የወጪ እና የገቢ ንግዱን በመደገፍ አገሪቷ ይበልጥ ተጠቃሚ እንድትሆን እንዲሁም ድርጅታቸው እንዲያድግ ከላይ ታች እያሉ እንደሆነ አጫውተውናል፡፡

በዚሁ አገልግሎታቸው በተለይም በቡና ዘርፍ ሰፊ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን በመጥቀስ፣ በቀጣይም ሥራቸውን አጠናክረው የሚቀጥሉ ስለመሆኑ ሲናገሩ፤ በተለይም ለወጪ ንግዱ አዲስ የሆኑ ነጋዴዎችን በማቅረብ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል የማማከር አገልግሎት ይሰጣሉ።

በሎጅስቲክስ አቅርቦትና አስተዳደር ላይ እንደ አገር በርካታ ችግሮች እንዳሉ የሚያነሱት ወይዘሮ እመቤት፤ የመሰረተ ልማት ችግር አንዱ ስለመሆኑ ያስረዳሉ።የተሟላ መሰረተ ልማት ባለመኖሩ መኪኖች የምልልስ ጊዜያቸው እጅግ የረዘመ ነው።በመሆኑም እኤአ በ2016 በዓለም ከሚገኙ 160 አገራት መካከል ኢትዮጵያ 126ኛ እንደነበረችና በ2018 ደግሞ ወደ ኋላ በመሄድ 136ኛ ላይ የተቀመጠችበት ጊዜ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

ይህ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ በሎጅስቲክስ ዘርፍ እየሰጠች ያለችው አገልግሎት ዝቅተኛ ሲሆን በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን አልተቻለም ማለት ነው፤ በአጭር ጊዜ ሊሰራ የሚችለውን ሥራ በረዥም ጊዜ በመሥራት፤ አላስፈላጊ ለሆነ የመጋዘን ወጪ በመዳረግ ከግለሰቦች ባለፈ አገር ትልቅ ዋጋ እየከፈለች ያለበት ዘርፍ ነው ሲሉም ኢትዮጵያ በዘርፉ ያለችበትን ሁኔታ ያብራራሉ።በአንድ ምርት ውስጥ የሎጅስቲክስ ድርሻ 40 በመቶ እንደሆነም አጫውተውናል፡፡

ወይዘሮ እመቤት፤ በተሰማሩበት አጠቃላይ የሎጅስቲክስ ዘርፍ 26 ለሚደርሱ ዜጎች በቋሚነት የሥራ ዕድል መፍጠር የቻሉ ሲሆን፤ በተለየ ሁኔታ ደግሞ በቡናው ዘርፍ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ቁጥር ያለው የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ።ቡና በሚደርስበት ወቅት ሰፊ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል ያስፈልጋልና በአንድ ጊዜ እስከ 60 ለሚደርሱ ሠራተኞ የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ፡፡

ማህበራዊ ኃላፊነትን በተመለከተም በተለያየ መንገድ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ እንደሆነ ያጫወቱን ወይዘሮ እመቤት፤ የሥራ ዕድል መፍጠር በራሱ አንድ ነገር ሆኖ፤ ሰዎች በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ደስተኞች ሆነው መሥራት እንዲችሉ የተለያዩ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ።ለአብነትም ወላጆች ከወሊዳቸው ጊዜ ጀምሮ ለልጆቻቸው ጊዜ መስጠት እንዲችሉ ያደርጋሉ።ከዚህም ባለፈ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ወይዘሮ እመቤት ከሠራተኞቻቸው ጎን ይገኛሉ።በመሆኑም ከሠራተኞቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ጥሩ መንፈስ ያለውና ቤተሰባዊ እንደሆነ ይናገራሉ።ከዚህ ባለፈም በአገር ደረጃም ሆነ በአካባቢያቸው ለሚደረጉ ማንኛቸውም ጥሪዎች በአቅማቸው ይሳተፋሉ፡፡

‹‹ማንም ሰው መጥቶ ድንጋይና እሾሁን የሚያነሳልን የለም፤ ለእኛ ያለነው እኛው ራሳችን ነን›› የሚሉት ወይዘሮ እመቤት፤ በሎጅስቲክስ ዘርፍ በሚደረጉ ማንኛቸውም ሴሚናሮች ላይ በመሳተፍ ያላቸውን ዕውቀትና ልምድ ያካፍላሉ።በዚህም ኢትዮጵያ በተለይም ወደ ኋላ በቀረችበት በሎጅስቲክስ ዘርፉ የተሻለች ሆና ውጤት እንድታስመዘግብ ያላቸውን ዕውቀት ለማካፈል ጊዜያቸውን ሳይሰስቱ አሚጠው ይጠቀማሉ፡፡


‹‹ኢትዮጵያ በተፈጥሮ በታደለችው ጸጋ ከራሷ አልፋ ሌሎችን መመገብ የምትችል እንጂ፤ መራብ ያለባት አገር አይደለችም›› የሚሉት ወይዘሮ እመቤት፤ በቀጣይ በግብርናው ዘርፍ በመሰማራት ቡና እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬዎችን አልምተው ከአገር ውስጥ ገበያ ባለፈ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ዕቅድ አላቸው።በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የቅድመ ዝግጅት ሥራቸውን አጠናቅቀው ወደ ሥራው ለመግባት በመንገድ ላይ ናቸው፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# በሁለት ዩኒቶች ሁለተኛው ግዙፍ ግድብ

**መሳኩ ኤሮሴ**



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ሁለተኛውን ተርባይን ሥራ ባስጀመሩበት ወቅት

በኃይል አቅርቦት አለመኖር ሳቢያ በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ ዜጎችን ብርሃን ለማቋደስ እንዲሁም ለልማት እጅግ ተፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ አስተማማኝ የሃይል አቅርቦት አገልግሎት መኖር ነው። በቂ የኃይል አቅርቦት መኖር ለአንድ ሀገር በእጅጉ ወሳኝ ነው። የኃይል አቅርቦት አገልግሎት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን በሚያስችል መጠን፣ ጥራትና ዋጋ በማይገኝበት ሁኔታ፤ የሀገሮችን ዕድገት ማስቀጠልም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ መፍጠር አይቻልም።

የኢትዮጵያ መንግስት ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትን የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ የተለያዩ አማራጮችን ይዞ የኃይል ማመንጫዎችን ሲገነባ ቆይቷል። ይህም ግንባታ በሃገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል ልማት ታሪክ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ነው። በእነዚህ ጊዜያትም የዘርፉን አሰራሮች በማዘጋጀት፣ ለተግባራታቸው መዋእለ-ንዋይ በመመደብ የሃገሪቱን የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት ለማሻሻልና የኢኮኖሚውንም ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል።

የኃይል ፍላጎቱን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በየጊዜው የግድቦች ግንባታዎች ይካሄዳሉ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከግድቦች ግንባታ በተጓዳኝ ከጸሀይ ኃይልና ከንፋስ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ውስጥ ተገብቷል፤ ከጀነሬተር የሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል እንዳለ ሆኖ ማለት ነው። ከደረቅ ቆሻሻና ከጂኦተርማልም የተወሰነ መጠን ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ይመረታል።

የኃይል ማመንጫዎቹ የተገነቡት የየወቅቱን የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ፣ የሀገሪቱን የኃይል ማመንጫ መገንባት አቅም፣ የለጋሾችን ወይም አበደሪዎችን ለጋስነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንደመሆኑ በግድቦች የሚይዘው የውሃ መጠንና የሚያመነጨው የኃይል ብዛትም በዚያው ልክ የሚለካ ነው። በእዚህም በርካታ የኃይል ማመንጫዎች ተገንብተዋል።

ከነዚህ የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች መካከልም 14 ያህሉ ከውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጩ ናቸው። ከትላልቆቹ እንጀምር። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ጊቤ 3 (1870 ሜጋ ዋት)፤ በለስ (460 ሜጋ ዋት)፤ ግልገል ጊቤ 2 (420 ሜጋ ዋት)፣ ተከዜ (300 ሜጋ ዋት)፣ ግልገል ጊቤ 1 (184 ሜጋ ዋት) ፣ መልካ ዋከና (153 ሜጋ ዋት)፣ ፊንጫ (134 ሜጋ ዋት)፣ ፊንጫ አመርቲ ነሽ (95 ሜጋ ዋት) ይመነጫሉ፤ ከቀደምቶቹ መካከልም አባ ሳሙኤል (6 ነጥብ 6 ሜጋ ዋት)፤ ጢስ ዓባይ (73 ሜጋ ዋት)፣ ቆቃ (43 ነጥብ 2 ሜጋ ዋት)፣ አዋሽ 2 (32 ሜጋ ዋት)፣ አዋሽ 3 (32 ሜጋ ዋት)፣ (14 ነጥብ 4 ሜጋ ዋት) በአጠቃላይ ከውሃ 3ሺ 814 ሜጋ ዋት ያመነጫሉ።

ከንፋስ ደግሞ አዳማ 2 (153 ሜጋ ዋት) እና አዳማ 1 (120 ሜጋ ዋት) በድምሩ 324 ሜጋ ዋት በማመንጨት ላይ ሲሆኑ፣ አሉቶ ጂኦተርማልና ዲዝል 104 ሜጋ ዋት ኃይል እያመነጨ ነው። በቅርቡ ኃይል ማመንጨት የጀመሩትን የህዳሴ ግድብ ሁለት ተርባይኖች ኃይል ሳይጨምር ሀገሪቱ ከሌሎች የውሃ ኃይል፣ ከንፋስ እና ከእንፋሎት ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ከ4ሺ300 ሜጋ ዋት የማይበልጥ ኃይል በማመንጨት ላይ ትገኛለች።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ሀገሪቱ ከውሃ ኃይል ማመንጫዎች የምታገኘው ኃይል 33 በመቶ ለሚሆነው ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ኤሌክትሪክ እያዳረሰ ሲሆን፣ ከጸሃይ እና ከእንፋሎት ኃይል ደግሞ 11 በመቶ ገደማ የሚሆነው ህዝብ ኃይል ያገኛል። በአጠቃላይ ከውሃ፣ ከንፋስ እና ከእንፋሎት ኃይል ሀገሪቱ በምታመነጨው ኃይል ከሀገሪቱ ህዝብ 44 በመቶው ብቻ ነው ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እየሆነ ያለው።

ከሀገሪቱ ህዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ዛሬም የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም። ከዚህ አብዛኛው ህዝብ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሲጠናቀቅ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ይሆናሉ ብሎ ተስፋ እያደረገ ይገኛል።

በአፍሪካ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም ደረጃ ግዙፍ ከሚባሉ ታላላቅ የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች አንዱ የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታው ሲጠናቀቅ 13 የኃይል ማመንጫ ዩኒቶች (ተርባይኖች) የሚኖሩት ሲሆን፣. በእነዚህም በአጠቃላይ 5 ሺህ 150 ሜጋ ዋት ኃይል ያመነጫል ተብሎ ታቅዷል። አሁን ኃይል ማመንጨት የጀመሩት ተርባይን አስርና ዘጠኝ እያንዳንዳቸው 375 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት ይችላሉ።

ግድቡ 145 ሜትር ወደ ላይ የሚረዝም ሲሆን ወደ ጎን ደግሞ 1 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትሮችን ይሸፍናል ። ከግድቡ በአንደ ጎን ኮርቻ ግድብ የሚባል ግድብም ተገንብቶለታል፤ ይህ ኮርቻ ግድብ የግድቡ ውሃ የተፈለገው ከፍታ ላይ ሳይደርስ በፊት ውሃው በጎን አምልጦ እንዳይወጣ በሚል የተገነባ ነው። ይህ ግድብ 50 ሜትር ከፍታ እና ወደ ጎን ደግሞ 5 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትሮችን የሚሸፍን ነው።

ባለፉት ሁለት አመታት ግድቡ ሁለት ዙሮች የውሃ ሙሌት የተካሄደለት ሲሆን፣ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሌትም በቅርቡ ተጠናቅቋል። ይህን ተከትሎም ግድቡ በአሁኑ ወቅት ከ22 ቢሊየን ኪዩቢክ ሜትር በላይ ውሃ መያዝ ችሏል።

ባለፈው የካቲት ወር ወደ ኃይል ማመንጨት የገባው ተርባይን አስር በሙሉ አቅሙ ኃይል ማመንጨት ሲጀምር እስከ 375 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም አለው፤ በአሁኑ ወቅት ከ270 ሜጋ ዋት በታች እያመነጨ ነው። ዩኒቱ ኃይል ማመንጨት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን 540 ጊጋ ዋት ሰዓት በላይ አመንጭቷል።

በቅርቡ ኃይል ማመንጨት የጀመረው ተርባይን ዘጠኝም ኃይል የማመንጨት አቅሙ 375 ሜጋ ዋት ነው፤ አሁን ግን ከ270 ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል እያመነጨ ይገኛል። ግድቡ ሲጠናቀቅ ወይም ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ 640 ሜትር ሲደርስ ግን በሙሉ ኃይሉ 375 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም አለው።

ሁለቱ ተርባይኖች አሁን ባለው የግድቡ ከፍታ ከ550 ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል እያመነጩ ናቸው። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለቱ ተርባይኖች ወደ ስራ መግባት፣ ህዳሴ ግድብ ኃይል ማመንጨት አህዱ ባለበት በአሁኑ ወቅት ብቻ በሀገሪቱ ካሉት የውሃ ኃይል ማመንጫዎች ከግለገል ጊቤ 3 ቀጥሎ ሁለተኛው ትልቁ የኃይል ማመንጫ እንዲሆን አድርገውታል።

ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ተርባይን አስር እና ዘጠኝ እየተገኘ ያለው ኃይል ከሌሎች ኃይል ማመንጫዎች ጋር ሲወዳደር ግድቡ ትልቅ አቅም መፈጠሩን መጀመሩን ያመለከታል። እነዚህ ተርባይኖች ተከዜ፣ ሁለቱ የአዋሽ ኃይል ማመንጫዎችና ጊቤ 1 በሙሉ አቅማቸው ሊያመነጩ የሚችሉትን ኃይል እያመነጩ ናቸው ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩልም አባ ሳሙኤል፣ ግልገል ጊቤ 1፣ መልከ ዋካና ፣ ፊንጫ እና ጢስ አባይ የውሃ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚያመነጩት በላይ ኃይል ማመንጨት ይችላሉ። ሁለቱ ተርባይኖች በሙሉ አቅማቸው ማመንጨት ሳይጀምሩ ደግሞ ግልገል ጊቤ ሁለትና ተከዜ ከሚያመርቱት በላይ ማመንጨት መቻላቸው የግድቡን ግዙፍ ፋይዳ አጉልቶ የሚያሳይ ነው።

የግድቡ ሌሎች ተርባይኖችም በቀጣይ የሚካሄዱ የውሃ ሙሌቶች እየተከተሉ በሂደት ወደ ስራ እንደሚገቡ ይጠበቃል። ቀሪዎቹ ተርባይኖች እያንዳንዳቸው አራት መቶ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል አንደሚያመነጩ ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት።

ግድቡ ተገንብቶ ሲጠናቀቅ የሚያመርተው 5ሺ 150 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ደግሞ ሀገሪቱ በዚያም በዚያም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ አማራጮች በአሁኑ ወቅት እየመረተች የምትገኘውን የኃይል መጠን በእጥፍ እንደሚያሳድገው ይጠበቃል።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ በአሁኑ ወቅት የኤሌክትሪክ ኃይል ለመጠቀም ያልታደሉ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር ከ60 ሚሊየን በላይ ይደርሳሉ። እነዚህ ዜጎች የኤሌክትሪክ ኃይል ለመጠቀም ባለመታደላቸው ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና የጤና ችግሮች ሲጋለጡ ኖረዋል። ኃይል ማመንጨት የጀመሩት ሁለቱ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ተርባይኖች የነዚህን ዜጎች ችግር በማቃለል ረገድ የሚኖራቸው ፋይዳ የላቀ ነው።

ካለፉት አስርት ዓመታት ወዲህ በሀገራችን በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ መልካም ጅምሮች የታዩ ቢሆንም፣ በኃይል እጥረት ምክንያት አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚጠበቅባቸውን ያህል ማምረት ሳይችሉ ቆይተዋል። ኃይል ማመንጨት የጀመሩት ሁለቱ ተርባይኖች የኢንዱስትሪዎቹን የኃይል እጥረት ችግር ለመቅረፍ ትልቅ እገዛ ይኖራቸዋል። አምራች ኢንዱስትሪዎቹ በሙሉ አቅማቸው በማምረት የሀገር ውስጥ የምርት ፍላጎት ለመሸፈን እና ወደ ውጭ ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሬ እንዲገኝ የሚያስችሉ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ የራሱን ሚና ይወጣል።

ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ለውጭ ገበያ እያቀረበች መሆኑ ይታወቃል። ሱዳንና ጅቡቲ የዚህ ተጠቃሚዎች ከሆኑ ቆይተዋል። ከእዚህም የውጭ ምንዛሬ እየተገኘ ስለመሆኑ በቅርቡ የወጡ ዘገባዎች ያመለክታሉ። በተጠናቀቀው በጀት አመት ብቻ 95 ነጥብ 4 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል።

የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ኬንያ ለመዘርጋት የሚያስችሉ ስምምነቶች ተደርገው የመሰረተ ልማቶች ግንባታ መካሄዱም ይታወቃል። ሌሎች ሀገሮችም ፍላጎቱ እንዳላቸው መረጃዎች ያመለክታሉ። ለአዚህም የሁለቱ ተርባይኖች ወደ ስራ መግባት በቀጣይም የሚደረጉ የውሃ ሙሌቶችን ተከትሎ ወደ ስራ የሚገቡ ተርባይኖች ፋይዳ ከፍተኛ ነው።

የግድቡን የግዝፈት ልክ በሁለት ተርባይኖች ላይ ተመስርተን ተመልከተናል። በእርግጥም ግዙፍ ነው። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ገና በመጀመሪያዎቹ ኃይል የማመንጨት አቅሞቹ ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ መረዳት አስችሎናል። ግድቡን በሁለት አመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ታቅዷል። እዚያ ድረስ ደግሞ ከሁለቱ ተርባይኖች አቅም በላይ ኃይል የሚያመነጩ ተርባይኖች በሂደት ኃይል ወደ ማመንጨት እንደሚገቡ ይጠበቃል። ለእነዚያ የምስራቾች ደግሞ ያብቃን።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአሸባሪው ህወሓት ሀይል አምላኪነት በቅርቡ ግብአተ መሬቱ ይፈጸማል !

በየዘመኑ የተነሱ ሀይል አምላኪ ግለሰቦች እና ቡድኖች የወጡበትን ማህበረሰብና ሀገር ብሎም አለምን ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል። በአለም የታሪክ መዝገብ ውስጥም የሰውን ልጅ ሰብአዊ ማንነት የሚፈታተኑ ብዙ ጥቁር ታሪኮች እንዲመዘገቡ ምክንያት ሆነው አልፈዋል።

ገና ከጅምሩ ከፍ ባሉ ውስብስብ የስነልቦና ችግሮች ሰለባ የሆኑት እነዚህ ግለሰቦችና የግለሰብ ስብስቦች /ቡድኖች/ አንድም እውነታዎችን በትክክለኛ ቁመናቸው ለመረዳት የሚያስችል አቅም ባለቤት አለመሆናቸውና ይህንንም አለማወቃቸው፤ ከዚህም በላይ ከሚሰሯቸው ስህተቶች ለመታረም የሚያግዝ የአእምሮ ውቅር የሌላቸው መሆናቸው ለጥፋታቸው ዋነኛ ምክንያቶች እንደሆኑ ይታመናል ።

እነዚህ ግለሰቦች በታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩ ማህበራዊ ክፍተቶችን በመጠቀም ወደ ስልጣን በመጡባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የሀይል አምላኪነት በሽታቸውን ማህበረሰቡ ውስጥ በመዝራት ፤ በተለይም ወጣቱን ትውልድ በባዶ ፕሮፓጋንዳ የበሽታቸው ሰለባ በማድረግ ከፍ ላለ እልቂት ዳርገውታል፤ ዛሬም እየዳረጉት ይገኛሉ።


በአብዛኛው ከበታችነት ስሜት የሚቀዳው ይህ የነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች የስነ ልቦና ችግር ፤ለራስ ከፍ ያለ ዋጋ በመስጠት የሚገለጥ፣ ይህንንም ተጨባጭ አድርጎ ለማየት የሚኖሩበትን ማህበረሰብ የትኛውንም አይነት ዋጋ ለማስከፈል ምንም የሚያቆማቸው የአስተሳሰብ መሰረት የሌላቸው ናቸው ።

ለነሱ ሰላምና የሰላም መንገድ ሁሌም የትንሽነት መገለጫ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በሰላም መንገድ ውስጥ ማለፍ ለእነሱ ሽንፈት ነው ። ለሰላም ከሚከፈል ዋጋ ይልቅ ለሀይል የሚከፈለውን የጥፋት ዋጋ የተሻለ አማራጭ አድርገው ይወስዳሉ። ሁሌም ቢሆን ለጥፋት እስከ መጨረሻው ጥግ በመሄድ የራሳቸውም ፍጻሜ ሳይቀር የከፋ እንዲሆን በመትጋት ላይ መሆናቸውን አያስቡትም።

በነዚህ አይነት ግለሰቦችና ቡድኖች ምክንያት አለም ከፍ ባሉ ጦርነቶች ውስጥ አልፋለች፤ በጦርነቶቹ የተፈጠሩ እልቂቶችም አለም ራሷን ከእንደነዚህ አይነት ግለሰቦችና ቡድኖች እንድትጠብቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥተው ያለፉ ናቸው።

ይህም ሆኖ ግን አሁንም ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው ግለሰቦችና ቡድኖች የወጡበትን ማህበረሰብና ሀገር ብሎም አለምን ችግር ውስጥ እየከተቱ ናቸው ። አለምም ቢሆን ከቀደሙት ጥፋቶች መማር ባለመቻሉ ዛሬም የችግሩ ሰለባ እየሆነ ይገኛል፤ በእኛም ሀገር አሸባሪው ህወሓት እየተጓዘበት ያለው የጥፋት መንገድ የዚህ ታሪክ አንድ አካል ሆኗል።

የቡድኑ ጥፋት አለም ቀደም ሲል ካስተናገደቻቸው የጥፋት ታሪኮች የሚለየው የጥፋት አድማሱ በአንድ ማህበረሰብና በሀገር ላይ ያነጣጠረ መሆኑ ላይ ብቻ ነው። የአስተሳሰብ መሰረቱም ሆነ የጥፋት ልኬቱ ሰብአዊ እሴቶችን ከማጠልሸት አንጻር ሲሰላ



ተመሳሳይነቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው ።

የቡድኑ መስራቾች ገና በጠዋቱ ይዘውት የተነሱት "የታላቂቷ ትግራይ" ህልም አለምን በቀደሙት ዘመናት ከፍያለ ዋጋ ካስከፈሉት እብዶች /ከሄትለር፣ ከመሶሎኒ፣ ወዘተ. / ጋር ያመሳስላቸዋል፤ ስነ ልቦናዊ መሰረቱም ተመሳሳይነት ያለው፣ ራስን አሳንሶ ከማየትና ይህን ባልተገባ መልኩ ለማካካስ ከሚደረግ አደገኛ የማንነት ግንባታ የመነጨ ነው።

በርግጥ እነዚህ ግለሰቦች የወጡበት የትግራይ ሕዝብ ከፍ ያለ መንፈሳዊ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች አሉት፣ በዚህም በራሱም ሆነ እንደ ሀገር በሀገሩ የሚኮራ የማንነት በሽታም ሆነ ሕክምና የሚያስፈልገው ሕዝብ አይደለም። ዘመናትን ማሻገር ያስቻሉ ከፍ ባሉ ሰብአዊ እሴቶች የተገነቡ ማንነቶችም ባለቤት ነው።

ሀይልን በማምለክ ሳይሆን እግዚአብሄርን በመፍራት ላይ የተገነባ ስብእና ያለው ፤ከራስ ወዳድነት ይልቅ ተካፍሎ መኖርን የህይወት መርሁ ያደረገ፣ ትውልዶችን በዚሁ መርህ አሳድጎ ለራሱና ለሀገር ተስፋ ለማድረግ ቀን ተሌት የሚተጋ፣ ለዚህም የማንንም ምስክርነት የማይፈልግ ህዝብ ነው።

የአሸባሪው ህወሓት መስራቾች ግን ከቡድኑ መመስረት ማግስት ጀምሮ በትግራይ ህዝብ ላይ ለእምነቱ ፣ ለማህበራዊ እሴቶቹና ባህሉ ባይተዋር የሆኑ አስተሳሰቦችን በሀይል በመጫን ማህበራዊ ምስቅልቅል ውስጥ ከተውታል፤ ተስፋ አድርጎ የሚያስባቸው ትውልዶቹም ደም የቡድኑ የሀይል ፖለቲካ አቅም እንዲሆን አድርገውታል።

በዚህም የትግራይ ህዝብ ላለፉት አምስት አስርት አመታት የከፈለው ዋጋ እስከ ዛሬ ድረስ ላለው የቡድኑ ሀይል አምላኪነትና የሀይል ፖለቲካ አቅምና ተስፋ ሆኗል። አሁን ላይ ለሚያካሂደው የተሳሳተ የማንነት ግንባታ እና ግንባታው ለፈጠረው መፋነን ሰለባ እንዲሆንም ዳርጎታል ።

ይህ የቡድኑ የሀይል አምላኪነት እርግማን ከመጣበት ረጅም መንገድና ከፈጠረው መንፈሳዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ እድፍ አንጻር ከዚህ በላይ ሊራመድ የሚችልበት አቅምም ሆነ ማህበራዊ መሰረት ሊኖረው አይችልም።

ቡድኑ የተሰጡትን የእድሜ ማራዘሚያ እድሎች በሙሉ ላለመጠቀም ያሳየው ግትርነትም የሀይል አምላኪነቱ በቅርቡ ግብአተ መሬቱ እንደሚፈጸም አመላካች ነው። በሀገሪቱ ታሪክም በሀይል አምላኪነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አስተሳሰብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳያንሰራራ ሆኖ ተፈጥሯዊ ሞቱን የሚሞትበትን ክስተት ፈጣሪ ነው።

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢ.ሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ‹‹ስለፍቅር ሲባል ስለፀብ ካወሩን ...››

**ታምራት ተስፋዬ**

አሸባሪው ህወሓት ቡድኑ ከአራት ኪሎ ቤተ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ከስልጣን ተባሮ መቀሌ ከመሸገ ወዲህም አዲሱን ለውጥ ሲያጥላላና ሲቃወም የለውጡ ትሩፋትም ለትግራይ ህዝብ እንዳይደረስ እንደ ጎሊያድ መንገድ ሲዘጋ መቆየቱ ይታወሳል። በለመደው የከፋፍለህ ግዛ መርህ፣በብሔሮችና በአጠቃላይ ሕዝቡ መካከል ‹‹encouraging blood feuds›› የእርስ በርስ ጥላቻና መርዝ ሲያሰራጭ ሲያራግብ ከፍ ሲልም ስለ ጦርነት ሲዘምር ሰንብቷል።

ኢትዮጵያን መምራት የምችለው ብቸኛ ድርጅት ‹‹እኔ ነኝ›› ኢትዮጵያን የምፈልጋትም እኔ እስከገዛሁኝ በበላይነትን እስከቀጠልኩኝ ብቻ ነው በሚል እብሪት ተውጥሮም የኢፌዲሪ መከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት በመሰንዘር ኢትዮጵያ ላይ በገሃድ ጦርነት ከፍቷል።

ኢትዮጵያም በቡድኑ እብሪትና ጥቃት ምክንያት ሳትፈልግ ጦርነት ውስጥ ለመግባት ተገዳለች።ቡድኑ በተሳሳተ ስሌት በለኮሰው እሳትም የትግራይን ህዝብ ለስቃይና መከራ ዳርጎታል።መንግስት ለህዝቡ በማሰብ መቀሌን ለቆ መውጣቱን ተከትሎ መቃብር ፈንቅሎ ከወጣና መቀሌን በዊልቸርና ክራንች ታግዞ ከያዘ በኋላም ነፍስ ያለው ሁሉ ጦር እንዲታጠቅና እንዲሞትለት የክተት አዋጅ ለፍፎ በርካቶችን ለጦርነት ማግዷል።

በማህጸን ውስጥ ከሚገኝ ጽንስ ካልሆነ በቀር ለስክሪፕቶና እርሳስ ያልጠነከረን እጅ ክላሽ እንዲጨብጥ በማድረግ በዓለም ታሪክ የጭካኔ ጥግ የታየበትን ዘግናኝ ተግባር ፈፅማል።ትርጉም ለሌለው ጦርነት አዛውንቶችና ህጻናት በመላክ እንደቅጠል እረግፋል።ጥይት ወደሚጮኽበት የመትረየስ ላንቃዎች ወደሚያስካኩበት ቀጠና በደመነፍስ በማግተልተል በርካቶችን የእሳት እራት አድርገዋል።

ምንም እንኳን ወደ አጎራባች ክልሎች በመዝለቅ መጠነ ሰፊ ጥፋትና ኢ- ሰብአዊ ድርጊት እና የጭፍጨፋ ተግባር ቢፈፅምም የቋመጠለትን ስልጣን ግን መቆጣጠር አልሆነለትም።ይልቁንም ‹‹በማንኛውም ግዳጅ ወይም ተግባር የላቀ ውጤት››በሚል እሴት በተገነባው፣በየትኛውም ሁኔታ በማንኛው የአየር ፀባይ ማንኛውም ግዳጅ በውጤት የማጠናቀቅ አንፀባራቂ ድል የማስመዝገብ አቅም ባለው የኢትዮጵያ ሰራዊትና ልዩ ሃይልና ሌሎችም የቁርጥ ቀን ልጆች ተቀጥቅጦ ወደ መጣበት ተመልሷል።

ወደ መጡበጥ ከፈረጠጡ ወዲህም የቡድኑ አባላትና አሻጃግሬዎቻቸው የስልጣን አባዜ የሚያመጣው እብደት ከእኛ በላይ ላሳር በሚል ትእቢት ተወጥረው ፤ጤንነታቸውን በሚያጠያይቅ መልኩ ስልታዊ ማፈግፈግ ከሚለው ጀምሮ የበሬ ወለደ አይን ያወጣ የውሸት ፕሮፖጋንዳቸውን ሲነዙም ከርመዋል።አስከፊው የሽንፈት ፅዋው እንዳሰከራቸው በሚያስታውቅ መልኩ ወደ ለየለት እብደት በመጢጋት ህዝቡን ዳግም ወደ መጨቆን ገብተዋል።

ኢትዮጵያ በአንጻሩ የጦርነትን አስከፊነት በመረዳትና በማስረዳት ለሰላም እጆቿን በተደጋጋሚ ዘርግታለች።ግጭቱ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ መንግስት ለሰላም እድል ለመስጠት ተደጋጋሚ ሙከራዎችን ሲያደርግ ቆይቷል።የተናጠል የሰብዓዊነት ተኩስ አቁም ማወጅን ጨምሮ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ማንሳት፣ እስረኞችን መፍታት፣ የሰብዓዊ ድጋፍን በከፍተኛ ሁኔታ የማሳለጥ እና መሰል እርምጃዎችን ወስዷል።

ከእነዚህ ርምጃዎች በተጨማሪ፣ መንግስት ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ ሰፊ እንቅስቃሴ እና ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ የሰላም ንግግር ያለቅድመ ሁኔታ በየትኛውም ቦታ እና ጊዜ ለመጀመር ያለውን ዝግጁነት መግለፁ ይታወሳል።

ሁሉም የወያኔ አመራሮች በአንፃሩ እጃቸው በንፁሐን ደም የተጨማለቀ ስለሆነ፤ ራሳቸውን ከተጠያቂነት ለማዳን ሠላምን በፍፁም አይፈልጉም።በዓለም ላይ መስማት የማይፈልገው ‹ሠላም የሚለውን ቃል ነው።ቃሉን ከጨቅላው የአስተሳሰብ መዝገበ ቃላታቸው ላይ ከሰረዙትም ቆይተዋል።

የጁንታ አባላት ሕፃናት እውቀት በሚሰጡ አሻንጉሊቶች ሲጫወቱ የሚናደዱና በጠብ መንጃ አሻንጉሊት ሲጫወቱ እንደ ሕፃን የሚቦርቁ የጀብደኞች ስብስብ በመሆናቸው እነርሱ ሠላም ማለት ሥልጣንን በጦርነት አግኝቶ እየዘረፉ ከበሮ ይዞ መደለቅ ነው።

በእነርሱ እምነትና ግምት ሁሌም ሠላም የሚመነጨው ከጦርነት ነው።ሁሉም የቡድኑ አባላት ስለ እውነተኛው የህዝብ ሠላም ፈፅሞ መስማት አይፈልጉም።ሆደ ሰፊውና ለዘላቂ ሠላም ሁሌም የሚተጋው የኢትዮጵያ መንግሥት የሠላም ንግግር ረጅም ርቀት እጁን ሲዘረግ ፤ተሽቀዳድመው ቅድመ ሁኔታ የሚደረድሩት ለዚህ ነው።

የሽብር ቡድኑ አመራሮች ሠላምን በጠረጴዛ ዙሪያ ሳይሆን፤ በጦርነት ለማግኘት የሚሹ ጦር ሰባቂዎች ናቸው። ትናንት ለስልጣን የበቃነው በትጥቅ ትግል ነው ብለው ስለሚያስቡ፤ዛሬም በዚያው በደደቢት በረሃ እሳቤ ተቸንክረው ጠብመንጃ ማወዛወዝ ቀድሚ ምርጫቸው ነው። ለሰላም እጅ መዘርጋት ዋጋው ውድ መሆኑን ፈፅሞ መረዳት አይፈልጉም።

የሰላም ጥሪውን በሰላም ከመመለስ ይልቅ፤ለማደናገሪያነት ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር ባንክ፣ ቴሌኮም፣ መብራት... ወዘተ የመሳሰሉ መሰረታዊ አገልግሎቶች ይለቀቁልኝ እያለ ሲፎግር ቆይታል።እበትናታለሁ ከሚላት ሀገር መሠረታዊ አገልግሎቶች የሚጠይቁት የአሸባሪው ቡድን አባላት፣በዚህ ሰሞን ደግሞ ለዳግም ለጦርነት እጃቸውን እየሰበሰቡ መሆኑን እየነገሩን ነው። ስለፍቅር ሲባሉ ስለ ፀብ እያወሩ ናቸው።

ቡድኑም ጦርነት ለመጀመር ያመቸው ዘንድ የተለመደ አታካች የውሸት ትርክቱን እንደ አዲስ ጀምሯል። የጁንታው አፈቀላጤ ጌታቸው ረዳም በቲዩተር ገፁ‹‹የመንግሥት ኃይሎች በተለያዩ ግንባሮች በትግራይ ታጣቂዎች ላይ ትንኮሳ ፈፅመዋል››በማለት የተለመደ ቀደዳውን አሰምቷል። በሚያስቅ ሁኔታም‹‹ ፌዴራል መንግሥቱ የሰሜኑን ጦርነት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ፍላጎት የለውም›› በማለት ክሱን እያራገበ ነው።

በመሪው ደብረፅዮን በኩል የትግራይ ሕዝብ ‹‹የታገለ›› እና ‹‹ያልታገለ››ብሎ በሁለት ከፍሎ እየዛተበት ነው። ከእንግዲህ ትግራይ ታጥቀው ለታገሉት ብቻ ነው የምትሆነው፣ ያልታገሉ ሰዎች ትግራይ ውስጥ ቦታ የላቸውም፤ አይኖራቸውምም። በሚል ከጎኔ ካልቆማችሁ እድሜ አይኖራችሁም ሲልም በአደባባይ ፎክራል።

ምንም እንኳን ቡድኑ ባለፉት አመታት በአንዳንድ የትግራይ ህዝብ ላይ (Conceptual Colonization) የአስተሳሰብ ባርነት መፍጠር ቢችሉም፣ አብዛኛው የትግራይ ህዝብም ሆነ ትግራይ ግን የሁሉም እንጂ የእነ ደብረፅዮንን ሐብት ለማስመለስ የሚታገሉት አይደለችም።

ስለ ፍቅር ሲባሉ ስለ ፀብ የሚያወሩት የቡድኑ አባላት ፍላጎታቸው ሰላም ባለመሆኑም አሁን ላይ ‹‹የኢትዮጵያ ሠራዊት ማጥቃት ሰንዝሮብናል እያሉ የውሸት ጣቃቸውን እየተረተሩ ናቸው። ቡድኑም በመሰል የበሬ ወለደ ሲስኩል የቀረበለትን የሰላም ማእድ ረግጦ ወደ ናፈቀው የትግራይ ወጣቶችን የማስጨረስ የእልቂት ማዕበል ወደሚያስከትለው ጦርነት ለመግባት ቋምጧል።

ከሽብር ቡድኑ በውጭ ኃይሎች ታዝሎ ስልጣን ላይ የመውጣት ታሪካዊ አመጣጥና ከቡድኑ ጦር አምላኪነት አኳያ፤ መሰል የፕሮፖጋንዳ ልፈፋው የሚጠበቅ ባህሪው በመሆኑ ብዙም የሚደንቅ አይደለም።ይሑንና ከጀርባው ያስጮኸው ሰይጣን አለና ድንፋታውም እንዲሁ በቀላል የሚታለፍም አይደለም።

አመራሮች የንፁሃን ደም አስከራቸው ከአንበሳ ጋር መግጠም ይከጅል እንጂ አንድ መታወቅ ያለበት ሃቅ ቢኖር በአሁን ወቅት የወረደ ወታደራዊ ቁመና እና የሞተ የውጊያ ሞራል ያለው የህውሓት ስብስብ ከጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን ጋር በማንኛውም መስፈርት ለንፅፅር የሚበቃም አይደለም።ኢትዮጵያን ለመበተን የተማማሉት የወያኔ ባህላዊ ጄኔራሎች ይሕ ሃቅ ፈፅሞ አይጠፋቸውም።

በሰሞኑ መንገድ ተጓዡ ቡድኑ በእብሪት ተወጥሮ ለሰላም የተዘረጋን የኢትዮጵያ እጅ ካልቆረጥኩኝ የሚል ለሆነ ግን እጅግ በጠነከረ ወታደራዊ ቁመናና የስነ ልቦና ዝግጁነት ላይ በሚገኘው ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን ዳግም እንዳያንሰራራ አድርጎ ድባቅ እንደሚመታውም ጥርጥር አይኖርም። ስለ ፍቅር ሲባል ስለ ፀብ የሚያወሩት የአሸባሪው መሪዎች አናት ይፈራርሳል እንጂ ኢትዮጵያ መቼም አትፈርስም።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆአስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## መልካም ሚስት - የባሏ ዘውድ

**ሰላማዊት ውቤ**

‹‹መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት ››ይባላል፡፡አዎ! እንዲህ አይነቱን ቃል መስማት የብዙዎችን ልብ ያሞቃል።የአባባሉ ትርጉምና ውጤት ድንቅ ነውና ለሰውልጆች የህይወት ተምሳሌት ቢሆን እሠዬው ነው። በርካቶቻችን ሚስቶች ለባሎቻቸው ዘውድ የመሆናቸውን እውነት ደጋግመን ሰምተነዋል። ይህን ሀቅ ተከትለው ሀሳቡን ዕውን ያደረጉ ደግሞ በህይወታቸው ብዙ አትርፈዋል።

የየዕምነቱ ቅዱስ መጻፍትም ሀሳቡን አጠናክረው በተለያየ መልኩ ተንትነው ጽፈውታል።በእነዚህ ማሳያዎች ባልና ሚስት አንዳቸው የሌላቸው ግማሽ አካል በመሆናቸው እስከ ሕይወት ፍፃሜ ተሳስበው፣ መዝለቅ እንዳለባቸው ያስረዳሉ። በተለይ በአንዳቸው፣ የደረሰውን ችግር እንደራሳቸው ተቀብለው እስከ መጨረሻው ተደጋግፈው መኖር እንደሚገባቸው እነዚሁ ሐይማኖታዊ መጽሐፍት በጽኑ ይመክራሉ።

አንዳንድ የማህበራዊ ጉዳይ ጠበብቶችም ቢሆኑ የጥንዶቹ የትሰስር ጥግ አንዳቸው ለሌላው ያላቸውን የፍቅር ጽናት የሚያሳይ እንጂ በቀለበትና በሰርግ ድግስ ጋጋታ ብቻ የሚለካ ግንኙነት እንዳልሆነ ሲናገሩ ይደመጣል።

ዛሬ ላይ በስፋት እንደሚስተዋለው ግን እንዲህ ያለው ጠንካራ የመተሳሰብ እውነታ እየተሸረሸረ መጥቷል ለማለት የሚያስደፍሩ ማሳያዎች ጎልተዋል ። የሚጠቀሱ ምክንያቶች እንደየሁኔታው ቢለያይም ጋብቻቸውን በመሰረቱ ሰሞን ፈጥነው ለፍቺ የሚበቁ፣ ጎጇቸውን የጭቅጭቅና የንትርክ ገበያ አድርገው ትዳርን የሚጀምሩ ጥንዶች ቁጥር ተበራክቷል።

የዛሬዋ እንግዳችን የወይዘሮ የኔነሽ ታዬ እና የባለቤታቸው ትዳር ከነዚህኞቹ በእጅጉ ይለያል። በተለይ ወይዘሮ የኔነሽ ለባለቤታቸው ሲሉ በሕይወታቸው ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። በዛሬው ጽሑፋችንም ይሄንኑ እውነታ የሚዳሰስና አርአያነቱ የጎላ የትዳር ታሪክ ልናካፍላችሁ ወደናል።

ወይዘሮ የኔነሽ ታዬ ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ልዩ ስሙ አዲስ ከተማ አካባቢ ነው። እስከ 12ኛ ክፍል ጎበዝ ተማሪ ነበሩ። ትምህርት ቤት ሳሉ ለጎበዝ ተማሪዎች ‹‹ስፔሻል›› ተብሎ በተለየው ክፍል የመማር ዕድል አግኝተዋል። ቤተሰቦቻቸው ለሀብትና ክብር ትልቅ ቦታ የሚሰጡ ታዋቂ የሶዶ ጉራጌ ነጋዴዎች ነበሩ።

ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ የጉራጌ ክትፎን ጨምሮ የሴት የተባሉ ሙያዎችን ሁሉ ሲማሩ አድገዋል። አንድ ዕለት ለየኔነሽ የወላጆቻቸው ሰራተኛ አንድ ሚስጥር ሹክ አለቻቸው።ሰሞኑን ባልተለመደ ሁኔታ ሽር ጉዱ የበዛው እጅግ ሀብታም ለሆነና የአባት ያህል በዕድሜ ለሚበልጣቸው ሰው ሊዳሩ እንደሆነ አረዳቻቸው፡፡ይህን ሲያውቁ ወይዘሮዋ ጊዜ አላጠፉም። ሻንጣ መሸከፍ፣ጓዝ ማንሳት አላስፈላጋቸውም። በለበሱት ልብስ በአጥር ዘለው አመለጡ። ተወልደው ካደጉበት ቤት ጠፉ።

ራሳቸውን በመደበቅ በየሆቴሉ ማዕድ ቤት እየተሸሸጉ የምግብ ዝግጅት ሥራን ጀመሩ። ወላጆቻቸው በፍለጋ ደክመው እስኪያጡዋቸውና ተስፋ ቆርጠው እስኪቀመጡ ድረስ በየሆቴሉ ብዙ ሰሩ። የመጨረሻው የሆቴል ስራቸው ካዛንችስ ያለው አድዋ ሆቴል ነበር ።ይህ ጊዜ የስራቸው ፍጻሜ የትዳር አጋራቸው መገኛ ሆነ ፡፡

የኔነሽ ልባቸው የፈቀደው ሰው አካልጉዳተኛ ነው። የዛኔ ደግሞ ሕብረተሰቡ ለአካል ጉዳተኞች ያለው አመለካከት እጅግ ፈታኝና አሽማቃቂ ነበር። አካል ጉዳተኞች እንደ ሌላው የሚያገቡና የሚወልዱ አይመስለውም ። ቤተሰቦቻቸውም የተዛባ አመለካከት ቁራኛዎች ነበሩ። እሳቸውም ቢሆኑ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ሁለቱም እጆቹና እግሮቹ የማይንቀሳቀሱ አካል ጉዳተኛ የትዳር አጋር እሆናለሁ የሚል ሀሳብ አልነበራቸውም። ያውም 10 ዓመታትን በመታዘል፣ በሰው ትከሻ ሲንቀሳቀስ የኖረ፤ የሚጎርሰው፤ የሚፀዳዳው፤ የሚለብሰው ሁሉ በሌሎች ድጋፍ የሆነ ሰው ፡፡እሱን አግብቼ ልጅ እወልዳለሁ የሚለው ዕውነት ፈጽሞ ውሳጣቸው አልነበረም።

ለትዳር የመረጡት ሰዉ በተፈጥሮ እጆች የሉትም። በመቀመጫው እየተፏቀቀ በየቤተክርስቲያኑ ቁራሽ




**ወይዘሮ የኔነሽ ታዬ**

የሚናፍቅ፣ በየቡና ቤቱ ደጃፍ እጁን የሚዘረጋ ምጽዋተኛ ነው፡፡የዚህ ሰው ፍቅር የወጣቷን ልብ ገዛ፡፡ጥንዶቹ ውሎ አዳራቸው በአንድ ሆነ።ሌሎች ተገርመው ቢያነውሯቸውም ፈጽሞ ጆሮ አልሰጡም ። ትዳር መሰረቱ፣ ልጅ ወልደው ሳሙ፡፡

አካል ጉዳተኛውን ዮሴፍ በቀለን አባወራቸው ሲያደርጉ ለእንጀራ የመረጡት የሆቴል ስራ ትዳር ጭምር እንደሰጣቸው አይዘነጉትም።በወቅቱ የምግብ ሥራ ባለሙያዋ ወጣት የኔነሽ ለእንግዶች ያዘጋጁትን ምግብ በወጥ ቤቱ መስኮት ለአስተናጋጆች ማቀበል አንዱ ግዴታቸው ነበር። እግረ መንገዳቸውንም በምግብ ቤቱ እልፍኝ የታደሙ ደንበኞችን ቃኘት ማድረግ ልምድ አድርገዋል።

አንድ ቀን ታዲያ እንደወትሮው ዓይናቸውን ጣል ሲደርጉ ከመመገቢያው ሳሎን በአንድ ጥግ ለየት ያለ ጉዳይ ያያሉ። ጠረጴዛው በርከት ባሉ ጎረምሶች ተከቧል። ሁሉም ጉርሻ የጠቀለለ እጃቸውን ወደ አንድ ሰው ሰንዝረዋል። በሳቅና በጫጫታቸው ውስጥ ‹ልታንቁኝ ነው እንዴ የስንታችሁን ልጉረስ ?› የሚል ድምፅ ሰሙ። ተንጠራርተው ተናጋሪውን ሊያዩ ቻኮሉ ፡፡ይህ ሰው የዛሬው ባለቤታቸው አቶ ዮሴፍ በቀለ ናቸው። ጓደኞቻቸው ተራ በተራ የሚያጎርሷቸው እጅ ስሌላቸው መሆኑ የገባቸው ጥቂት ቆይቶ ነበር ። ይህ ብቻ አይደለም ፡፡ሰውየው እግራቸው ጭምር የእንቅስቃሴ ችግር ስላለበት የሚቀመጡት በሌሎች እገዛና በመከራ መሆኑን አስተዋሉ። ሁኔታው ውስጣቸውን ነካው፣ከልብ አዘኑ ።ዓይናቸው ማረፍ አልቻለም።ይሄንኑ ትዕይንት ሰርክ መከታተል ጀመሩ።ሰውዬው ሁሌም ምግብ ባዘዙ ቁጥር የሚያጎርሳቸው ።የሌላ ሰው እጅ ነው።

በአንድ ዕለት ምሳ ሰአት እንደተለመደው አንገታቸውን በመስኮቱ አስግገው ተመለከቱ።እነዚያ ወጣቶች ከሰውዬው ጎን አልነበሩም። አቶ ዮሴፍ ያዘዙት ምግብ ከፊታቸው ተቀምጧል። ባልንጀሮቻቸው ስለሌሉ የቀረበውን አልነኩትም፡፡የኔነሽ አንገታቸውን ብቅ እያደረጉ ሰዎቹን ጠበቁ፡፤ብቅ ያለ የለም።ምግቡ ሳይበላ ሰዓታት ተቆጠሩ።ዮሴፍ አቀርቅረው በትካዜ ተቀምጠዋል።የኔነሽ ውስጣቸው ተነክቶ ልባቸው ከፋኛ ቢያዝን ከኩሽናው ዞረው ወደ እሳቸው አቀኑ።

ምግቡን እያዩ በትካዜ ወደአቀረቀሩት ሰው ቀርበው ደረሱና ለምን እንደማይበሉ ጠየቋቸው። ውስጣቸው የሚያጎርሳቸው ሰው ያለመኖሩን አሳምሮ ያውቃል፡፡ያም ሆኖ ከሰውየው አንዳች ምላሽ ጠበቁ፡ዮሴፍ ያሰቡትን እውነት ዘርዝረው ነገሯቸው፡፡አጠገባቸው ቁጭ አሉና ፍቃዳቸውን ሳይጠይቁ ያጎርሷቸው ያዙ፡፡አብልተው ውሀ ካስጎጭዋቸው በኋላም ከአጠገባቸው አልራቁም፡፡

የዛን ቀን አቶ ዮሴፍ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክስርስቲያን ሄደው የአራት ወር ህፃን ልጅ ጥላባቸው የሞተችውን የቀድሞ ባለቤታቸውን እያስታወሱ ለምን ሲሉ ለፈጣሪያቸው ያለቀሱበትና ከብቸኝነት ኑሮ የምታላቅቅ ውሃ አጣጪ እንዲሰጣቸው የለመኑበት ነበር ።

በጨዋታቸው መሀል የኔነሽ ለምን ሁልጊዜ ሆቴል እንደሚበሉ ጠየቋቸው። ሚስት እንደነበረቻቸው፣ ህፃን ልጅ ጥላባቸው እንደሞተች ነገሯቸው።አሁንም የኔነሽ ዕንባ እያነቃቸው በእጅጉ አዘኑ። ዕለቱን ሲሰነባበቱ ተመልሰው እንደሚመጡ ያውቁ ነበር። ከዛን ቀን ጀምሮ የኔነሽ የዮሴፍ ቀኝ እጅ ሆኑ።ሰርክ ያጎርሷቸው፣ያጠጡዋቸው ጀመር። መላመድና ይበልጥ መግባባት ሲጀምሩ ዘወትር እየመጡ እንዲጫወቱ ይጋብዟቸው ያዙ ።

ዮሴፍ የሚያጎርስ የሚያደምጣቸው አገኙ።በሁለት እግር ለመቆም ያስቻላቸው የቅዱስ ዑራኤል ጸበል፣ በሞት የተለየች የቀድሞ ባለቤታቸው እና ወላጅ እናታቸው መሆናቸውን አጫወቷቸው። የሚተዳደሩትና ቤተሰባቸውን የሚደጉሙት ቤተክርስቲያን ተቀምጠው በሚያገኞት ምፅዋት መሆኑን አልደበቋቸውም።

የኔነሽ ለዮሴፍ ጆሮ ሰጥተው አዳመጧቸው ።ሲወለዱ ሁለቱ እጆችና እግሮቻቸው እንደማይሰሩ፣ መቆም ባለመቻላቸው በሰው ትከሻ ይንቀሳቀሱ እንደነበር፣ እናታቸው፣ ታላቅ እህታቸውና በሕይወት የሌለው ወንድማቸው ለ10 ዓመት ያህል አዝለው ሲያንቀሳቅሷቸው እንደቆዩ ተረኩላቸው። ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያን ገቢ በሚገኘው የቄስ ትምህርት ቤት ከፊደል እስከ ንባብ መማራቸውን ጭምር ነገሯቸው፡፡

ለወይዘሮ የኔነሽ ባለቤታቸው የአራት ወር ህፃን ልጅ ጥላባቸው መሞታቸውን ሲያወሱ ስቅስቅ ብለው እያለቀሱ ነበር። ሟች ሚስታቸው አብሮ አደጋቸውና የሰፈራቸው ልጅ ነበረች። ይህች ሴት ጓደኛቸው ከመሆኗ በፊት እዛው ወላጆቻቸው አጠገብ ያሉ ጎረቤት ለጅ በመሆኗ ሲለምኑ ቆይተው ከምሽቱ አምስትና ስድስት ሰዓት ሲመጡ በሩን የምትከፍትላቸው እሷ ነበረች ። መግባባቱ ሲጨምር ከህመማቸው እንዲፈወሱ በየሳምንቱ ፍልውሃ ይዛቸው ትገባና ታጥባቸው ነበር።ይህ ግንኙነት ቀስ በቀስ ወደ ፍቅር ተቀየረ። ይሄን ያወቁ በርካቶችና ወላጆቿ ለእነሱ የነበራቸው አመለካከት ጥሩ አልሆነም ። የገዛ ወንድሞቿና እህቶቿ ወንድ አጥተሽ ነው ወይ እሱን ያፈቀርሽው በሚል ትችት ይሰነዘሩባት ያዙ።

እሳቸውም ቢሆኑ ስድቡንና ግልምጫቸውን አልቻሉም። በነሱ ፍቅር መንደርተኛው ሁሉ ጉድ ማለቱ አሳቃቃቸው። ሁለቱ ፍቅረኛሞች ከቤተሰብ የሚደርስባቸውን ስድብና ግልምጫ ሲብስባቸው፣ ፈቃደኝነቷን ጠይቀው እሽ ስላለቻቸው ይለይላቸው ብለው ከምፅዋት የሚገኘውን ገቢ ተማምነው ቤት ተከራይተው በመጋባት መኖር ጀመሩ።አንዲት ሴት ልጅም ወለዱ።

በዚህ ወቅት ሕብረተሰቡ የሚያደርስባቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ይበልጥ ተባብሶ ቀጠለ ። ፍቅራቸው ሳይቀዘቅዝ፣ ኑሮን መቋቋም ያዙ።በድንገት ግን ባለቤታቸው የአራት ወር ህፃን ጥላባቸው አለፈች።ዮሴፍ ።ሌላው ቀርቶ፣ ጡጦ ለመስጠትና አቅፎ ለመንከባከብ የሚያስችል እጅ ስለሌላቸው በእጅጉ ተቸግረው ቆይተዋል። በዕጣ ፈንታቸውም ለመጀመርያ ጊዜ በእጅጉ ያዘኑበት ወቅት መሆኑን አልሸሸጉም፡፡ይህን ችግር ለማለፍ የወለዷትን ጨቅላ ይዘው፣ ወደ ቤተሰቦቻቸው ቤት ለመመላለስ መገደዳቸውን በዕንባ እየታጠቡ አወጓቸው።

ዮሴፍ የህፃንዋን ወተት ጨምሮ እናታቸውን ለማገዝ ምሽቱን በየቡናቤቱ እየዞሩ ምፅዋት ማሰባሰብ እንደሚጠበቅባቸው አልደበቋቸውም። የተሻለ ገቢ ለማግኘት ባላቸው ጥረትም እስከ ሌሊት የሚዘልቅ ቆይታ ሊገጥማቸው ይችላል ። በዚህ አጋጣሚ በአንድ የበዓል ዋዜማ እስከ ሌሊቱ አስር ሰዓት ቆይተው በር የሚከፍትላቸው እስከማጣት ደርሰዋል፡፡ላለፉት ሦስት ዓመታት ለመግለጽ በሚከብድ ችግር ተዘፍቀው ኑሮን እየገፉ ስለመሆኑ ለየኔነሽ ሲያወጓቸው በትካዜ ተውጠው ሆነ፡፡

የኔነሽ ይህን መሰሉን ታሪክ ሲያደምጡ ውስጣቸው በተለየ ስሜት ተነካ።ዮሴፍ ወደሆቴሉ ብቅ በሚሉበት አጋጣሚ ሁሉ ከጎናቸው ተቀምጠው ማጉረሱን ስራዬ ብለው ቀጠሉ።ይህ ብቻ አይደለም።ዮሴፍ ባሻቸው ጊዜ እየመጡ እንዲጫወቱ ጭምር ፈቃዳቸውን ሰጡ፡፤መግባባት ፤መቀራረቡ ቀጠለ።መተሳሰቡ ጠነከረ፡፡

የሁለቱ ብርቱ ግንኙነት ለአብሮነት ጋበዛቸው።የኔነሽ ልክ እንቀድሞ ሚስታቸው አጋር ሊሆኑላቸው ቃል ገቡ። የመጀመሪያ ውጥናቸው ቤት ተከራይተው ከሆቴሉ መውጣት ነበር ።አብረው መኖር ሲጀምሩ ሆቴሉ ከችግር ወደቀ ።የባለሙያዋ እጅ ባለመኖሩ በቀድሞው ሁኔታ መቀጠል አልቻለም፡፡ቀስ በቀስ ደንበኞች እየራቁ እስከመዘጋት ደረሰ፡፤ይህኔ የሆቴሉ ባለቤት ተበሳጩ።ለየኔነሽ አለመኖርና ለሆቴሉ መዘጋት ሰበብ የሆኑትን ዮሴፍን ጠሏቸው።ሊገሏቸው ያሳድዷቸው ጀመር።ፈተናው በዛ ።ቤተሰብና ወዳጅ ዘመድ ጋብቻውን ኮነኑት።ሁሉም በትችትና በስድብ አላስቆም አላስቀምጥ አሏቸው፡፡

የዛኔ የኔነሽ የዮሴፍን ህጻን ልጅ ሊያሳድጉ ባመጡ ጊዜ የባለቤታቸው ዘመዶች የተናገሯቸውን ክፉ ቃል ዛሬ ድረስ አይረሱትም።ሰዎቹ የልጅቷንና የባለቤታቸውን ተመሳሳይ እንክብካቤ በእኩል መዝነው « ሁለት ህጻናት ማስተዳደር ትችያለሽ ወይ ? » ብለዋቸው ነበር፡፡

ህይወት ከባድና ፈታኝ ቢሆንም የኔነሽ ተንገዳግደው አልወደቁም።ህጻንዋ አራት አመት ሳይሞላት ትምህርት ቤት እንድትገባ አደረጉ ።ይህኔ ባለቤታቸው የእጃቸውን ገቢ መዝነው ቄስ ትምህርት ቤት ትግባ ሲሉ ሞገቷቸው ።እሳቸው ግን እኩዮቿ የሚማሩበት የግል ትምህርትቤት ትዝለቅ በሚል አቋማቸው ጸኑ።በወቅቱ «ልጅቱን አስመዝግበው ሲመለሱ መንገድ ላይ ከባለቤታቸው ተጨቃጭቀዋል። «ብሩ ከየት ይመጣል ሲሉ ተጣልተዋቸዋል።በእርግጥ በጊዜው ምንም ገቢ ለሌላቸው ባልና ሚስት ለግል ትምህርት ቤት በየወሩ 80 ብር መክፈል ይከብዳል። ወይዘሮ የኔ ነሽ ልጅቱን ትምህርት ቤት ያስገቧት ግን ባለቤታቸውን ከመንከባከብ ባሻገር በወር አንዴም ቢሆን የድግስና የሆቴል ምግብ አዘጋጅተው በሚያገኙት ገቢ ክፍያውን እሸፍናለሁ በሚል ነበር።

እሳቸው ይህን ቢያስቡም ሁኔታዎች አልተቃኑም። ባለቤታቸውን ከማፀዳዳት ጀምሮ አስከማልበስ፣ የቤት ስራውን ሸፍኖ ከጎን ሆኖ እስከመደገፍ፣ ሲወጡና ሲገቡ በር ከፍቶ አስከመዝጋት ያለውን ግዴታ የሚሸከመው የእሳቸው ጫንቃ ብቻ ነበር። ጊዜ ተረፏቸው እንዳሰቡት በሥራ አልዋሉም ።

የወይዘሮ የኔነሽ ቅንነት ግን ብቻውን አልቀረም።ውሎ አድሮ የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት ልጅ እናት ለመሆን በቁ።አካል ጉዳተኛ በመሆናቸው የተነወሩባቸው ባለቤታቸውም የሦስት ልጆች አባት ሆነው ሙሉነታቸውን አስመሰከሩ፡፡

### ያስፈው ትናንት በዛሬ ...

እነሆ! ዛሬ የትናንቱ ታሪክ በዛሬው እውነት ተሽሯል።በአራት ወሯ እናቷን በሞት ያጣችው የዛኔዋን ህጻን ጨምሮ አንደኛው ልጃቸው በወጉ ተምረው በዲግሪ ተመርቀዋል። ይህ ብቻ አይደለም፡፡ባለቤታቸው አቶ ዮሴፍ በውስጣቸው የኖረውን የስዕል ችሎታ የሚያሳዩበት ጊዜው ደርሷል፡፡እ ጅ ባይኖራቸውም በአፋቸው የሚስሏቸው ድንቅ ስዕሎች ባክነው አልቀሩም፡፡

ባለቤታቸው የኔነሽ ለሙያቸው ትኩረት ሰጥተው ባደረጉት ጥረት ሙያቸውን የሚያስመሰክሩበትን ዕድል አመቻችተዋል።ዛሬ ዮሴፍ በስነ-ስዕል የዲፕሎማ ተመራቂ ሆነዋል ።ትናንት ከልመናና ከምጽዋተኝነት ታሪክ ተሻግሮ ዛሬ ላይ ለደረሰው ህይወት መሰረቱ የብርቱዋ ሴት የማይላላ ጥንካሬ ነው።አሁንም ይህች መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ የመሆኗ እውነት አልተሻረም።እንደትናንትናውና ዛሬ ሁሉ ነገም የግማሽ አካሏን ማንነት ሙሉ አድርጋው ትቀጥላለች።

# ስፖርት



## የፌዴሬሽኑ መግለጫና የጠቅላላ ጉባኤው የቦታ ለውጥ

**ብርሃን ፈይሳ**

ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንታዊና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ የቀረቡ የመጨረሻ እጩዎች ዝርዝር ይፋ ተደርጓል።ምርጫውን ተከትሎ በፌዴሬሽኑ ላይ እየተነሱ ያሉ ጉዳዮችን በተመለከተም ፌዴሬሽኑ ከትናንት በስቲያ መግለጫ ሰጥቷል።

የአራት ዓመት የስራ ዘመኑን ያጠናቀቀው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቀጣይ ሳምንት መጨረሻ በሚካሄደው ምርጫ እንደሚተካ ይታወቃል።ይህንን ተከትሎም የተቋቋመው የምርጫ አስፈጻሚ እና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ከየክልሉ በደረሱት ተወካዮች የመጨረሻዎቹን የፕሬዚዳንታዊና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እጩዎች አሳውቋል።በዚህም መሰረት ለፕሬዚዳንታዊው ምርጫ ሶስት እጩዎች የቀረቡ ሲሆን፤ ያለፉትን አራት ዓመታት ፌዴሬሽኑን ሲመሩት የቆዩት አቶ ኢሳያስ ጂራ ኦሮሚያ ክልልን በመወከል በእጩነት ቀርበዋል።የአማራ ክልላዊ መንግስትን በመወከል አቶ መላኩ ፈንታ የቀረቡ ሲሆን፤ ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ደግሞ አቶ ቶኩቻ አለማየሁ የፕሬዚዳንታዊ ምርጫው እጩ ሆነዋል።በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት ምርጫውም 32 የሚሆኑ እጩዎች የተለያዩ ክልሎችን በመወከል ለውድድር ቀርበዋል።

በመጪው ሳምንት መጨረሻ ነሃሴ 21 እና 22/2014ዓም ከሚደረገው የፌዴሬሽኑን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ጋር በተገናኘ በኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ አክሲዮን ማህበር አስመራጭ ኮሚቴው ትችቶችን ሲያስተናግድ መቆየቱ የሚታወስ ነው።ይህንን ተከትሎም ፌዴሬሽኑ ያለአግባብ የስም ማጥፋት ደርሶብኛል ባላቸው ርዕሶች ላይ በፕሬዚዳንቱ አቶ ኢሳያስ ጂራ አማካይነት በጋዜጣዊ መግለጫ ማብራሪያ ተሰጥቷል።ፕሬዚዳንቱ ካነሷቸው ነጥቦች መካከልም ከገንዘብ አወጣጥ ጋር የተያያዘው አንዱ ሲሆን፤ እርሳቸው ወደ ስልጣን በመጡበት ዓመት ፌዴሬሽኑ 16 ሚሊየን ብር እዳ የነበረበት መሆኑን ጠቁመዋል።በዚህም ምክንያት ቡድኖች አህጉር አቀፍ ውድድሮች ላይ መሳተፍ እስከማይችሉበት ሁኔታ ላይ ተደርሶ እንደነበር አስታውሰዋል።ነገር ግን አቅም በማደራጀትና የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን በመስራት በዚህ ወቅት ፌዴሬሽኑ በአካውንቱ ከ45 ሚሊየን ብር በላይ እንዳለው ጠቁመዋል።

ይህም ፌዴሬሽኑ በተለያዩ የዕድሜ እርከን ከሚመራቸው ብሔራዊ ቡድኖች፣ የወዳጅነት ጨዋታዎች፣ የስፖርት ልማት ስራዎች፣ ሌሎች ወጪዎች እንዲሁም ለየክልል ፌዴሬሽኖች ከተሰጠው 12 ሚሊየን ብር ውጪ ነው።ከዚህ ጋር በተያያዘ ስማቸው የተነሳ ግለሰቦች ለፌዴሬሽኑ ከሚያስገኙት ገቢ ጋር ሊያገኙት የሚገባቸውን ገንዘብ ለልማት ስራዎች እንዲውሉ በማድረግ ጭምር በመሆኑ ሊመሰገኑ እንጂ ሊወቀሱ እንደማይገባ ገልጸዋል።

ከፌዴሬሽኑ ህንጻ ግዢ እና ስም ማዘዋወር ሂደት ጋር በተያያዘ ለተነሳው ትችትም ፕሬዚዳንቱ ምላሽ ሰጥተዋል።በዚህም በፊፋ ድጋፍ በ95 ሚሊዮን ብር ወጪ የተገዛውና ፌዴሬሽኑ እየተገለገለበት ያለው ህንጻ፤ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር እንዲሁም የኮንስትራክሽን ቢሮ ባለሙያዎችን አካቶ በወጣ ጨረታ የተገዛ መሆኑን አቶ ኢሳያስ ተናግረዋል። ከስም ዝውውሩ ጋር በተያያዘም የተለያዩ ሂደቶችን ያለፈ ሲሆን፤ ፌዴሬሽኑን የማያሳምን ጉዳይ በመፈጠሩ ምክንያት በህግ እንዲያዝ ተደርጓል።በመሆኑም ህንጻው የፌዴሬሽኑ አይደለም የሚባለው ስህተት መሆኑ እንዲሁም ካርታ፣ ሙሉ ውክልና ያለው እና መሸጥ ቢፈልግም የሚችል መሆኑን አብራርተዋል።

ከትጥቅ አቅራቢው ድርጅት ጋር በተያያዘም በቅድሚያ በነጻ የቀረበ መሆኑን በመጠቆም፣ በወቅቱ በተነሳው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት አንዴ የቀረበውን ትጥቅ ለሶስት ዓመት ለመጠቀም ተገዷል።በቀጣይም ፌዴሬሽኑ 12ሺ.500 ትጥቆችን በመግዛትና 10ሺ የሚሆኑትን በመሸጥ 10 ሚሊየን ብር እንዳገኘ ገልጸዋል። ይህም ፌዴሬሽኑ ራሱን ለማቋቋም ካደረጋቸው ጥረቶች መካከል አንዱ ነው ብለዋል።

ከምርጫው ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀደም በአርባ ምንጭ ከተማ በተካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው የፌዴሬሽኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ በጎንደር ከተማ እንዲካሄድ ነበር።ይሁንና ከተማው ለዚሁ የሚሆነውን ዝግጅት እያደረገ ባለበት ሁኔታ ውዝግቦች መነሳታቸው አልቀረም። በፌዴሬሽኑ አስቸኳይ ኮሚቴም ጠቅላላ ጉባኤው የሚካሄድበት የቦታ ለውጥ መደረጉን ፌዴሬሽኑ አሳውቋል። ይህም የሆነው ከአማራ ክልል የስፖርት ቢሮ ምክትል ኋላፊ ወደ ፌዴሬሽኑ በተደረገ የስልክ ጥሪ ምክኒያት መሆኑ ተገልጿል። እንደፌዴሬሽኑ ገለጻ፣ የክልሉ ምክትል ቢሮ ኋላፊው ‹‹ከክልሉ ክለቦች የተላኩ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ወኪሎች ስሞች መቀየር እንዳለባቸው እና ይህንን እንዲያደርጉ፤ ካላደረጉ ግን ጉባኤው እንዲስተጓጎል እንደሚያደርጉ በማስፈራራት ጭምር ስሜታቸውን መግለጻቸው ኮሚቴው ባደረገው ማጣራት አረጋግጧል››።በመሆኑም ኮሚቴው የጉባኤው ውጤታማነት ላይ ስጋት ስላደረበት ምርጫው ቀድሞ ከተያዘው ጎንደር ከተማ ወደ አዲስ አበባ እንዲዘዋወር ውሳኔ ያሳለፈ መሆኑን አስታውቋል።

ፌዱሬሽኑን የምርጫ ጠቅላላ ጉባኤ ቦታ እንዲቀየር ያሳለፈውን ውሳኔም ተገቢነት እንደሌለው የጎንደር ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት መምሪያ ገልጿል። የከተማው ኮሚኒኬሽን ትናንት የመምሪያው ኃላፊ አቶ አበበ ላቀውን ጠቅሶ በማህበራዊ ገጹ ያወጣው ዘገባ እንደሚያመለክተው፣

ፌደሬሽኑ በከተማዋ ጉባኤውን እንዲካሂድ ካሳወቀ በኃላ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ከፌዴሬሽኑ አብይ ኮሚቴ ጋር በቅንጅት በተሳካ ሁኔታ ማከናወን መቻሉን ገልፀዋል።

ይሁን እንጅ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቀው ከተማዋ ጉባኤውን ለማስተናገድ በመጠባበቅ ላይ ባለችበት ወቅት አሳማኝ ባልሆነ ምክኒያት ፌደሬሽኑ ጉባኤው የሚካሄድበትን ቦታ መቀየሩን በቀን 12/12/2014 ዓ.ም አሳውቋል። ስለሆነም ፌዴሬሽኑ የወሰነው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን የመምሪያ ኃላፊው ገልፀው፣ ፌደሬሽኑ የወሰነው ውሳኔው ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ውሳኔውን በድጋሜ ሊጤን እንደሚገባው መምሪያ ኃላፊው ገልፀዋል።


## ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በካፋ ዞን ጊምቦ ወረዳ ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በ2015 የበጀት ዓመት በወረዳ ዉስጥ ለሚገኙ ባለበጀት መ/ቤቶች የተለያዩ ግዥዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል ::

ሎት, 1ኛ የተለያዩ የጽህፈት መሣሪያና የጽዳት ዕቃዎች

ሎት , 2ኛ የተለያዩ ሞዴልና ዓይነት ያላቸዉ የመኪናና የሞተር ሳይክል ጎማ ከነ ከለማንዳሪያ

ሎት, 3ኛ የተለያዩ ዘመናዊ የቢሮ ወንበርና, ጠረጴዛ (ፈርኒቸር )

ሎት , 4ኛ/ የጥበቃና ጉልበት ሠራተኞች የደንብ ልብሶች

ሎት, 5ኛ/ የተለያዩ ህትመትና ማስታወቂያ

ሎት , 6ኛ, የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስና ተዛማጅ ዕቃዎች

ሎት, 7ኛ| የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስና ሞተር ሣይክሎች ጥገና

ሎት , 8ኛ የእንስሳት መድሀኒቶችና መገልገያዎች መሣሪያዎች ሲሆኑ:-

**በዚህ መሰረት**

1ኛ.. በዘርፉ ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለዉ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TIN NO) ፤የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና በመንግስት ግዥ እንዲሳተፉ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡

2ኛ..የጨረታ ማስከበሪያ CPO ለእያንዳንዱ ሎት ከ1-5ላሉት ብር 30,000(ሠላሳ ሺህ ብር ) ከሎት ከ6- 7 ላሉት ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር ) በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

3ኛ/ ጨረታዉ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት ዉስጥ የጨረታዉን ሠነድ ከጊምቦ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 14 በመቅረብ የማይመለስ ብር 200(ሁለት መቶ ብር) በመክፈል መዉሰድ ይችላሉ፡፡

4ኛ.ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተዘረዘረዉ መጠይቅ መሰረት ብቻ ዋጋዉን ሞልቶ በመፈረምና ህጋዊ የድርጅቱን ማህተም በሁሉም ገጽ ላይ በማሳረፍ ጨረታዉ ከወጣበት በ16ኛዉ ቀን በዕለቱ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን ለጨረታ በተዘጋጀ ሣጥን ዉስጥ የመጫረቻ ሰነድ ፖስታ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

5ኛ/ጨረታዉ ከቀኑ 8፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ባይገኙም የጨረታዉን መከፈት አያስተጓጉልም፡፡

6ኛ.ተጫራቾች ለሎት3/ ፈርኒቸር ዕቃዎችን በከለር ፎቶግራፍ አያይዞ ማቅረብ የሚችልና ለሎት 1እና6 የዕቃዎቹን ናሙና በጨረታ አከፋፈት ወቅት ይዞ የማቅረብ ግዴታ አለባቸዉ፡፡ናሙናዉን ይዞ የማይቀርብ ተጫራች በጨረታ እሺጋ ወቅት ከጨረታዉ ዉጪ የሚሆን ይሆናል፡፡

7ኛ. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ጨረታዉን ማሸነፉ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 የስራ ቀናት ዉስጥ ቀርቦ ውል ገብቶ ከዉሉ አጠቃላይ ዋጋ 10% በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

8ኛ.አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈበትን ዕቃዎችን ሙሉ በሙሉ ደረሰኝ በመቁረጥ እስከ ጊምቦ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት አቅርቦ ገቢ የማድረግና ገንዘቡን የመዉሰድ ግዴታ አለበት፡፡

9ኛ.ጨረታዉ የሚታሸግበት ቀን ቅዳሜ ፤እሁድ ወይም የበዓላት ቀን ከሆነ በሚቀጥለዉ የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይሆናል ፡፡

10ኛ. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡

11ኛ. ተጫራቾች ያሸነፉትን ዕቃ በገቡት ዉል መሠረት ባያቀርቡና በአሰራራችን ላይ ችግር ቢፈጠር የግዥ አዋጅን በመከተል ህጋዊ እርምጃ በመዉሰድ ለክልሉ ግዥ ኤጀንሲ በደብዳቤ የምናሳዉቅ መሆኑን እንገልፃለን ::

ለበለጠ መረጃ 047220055 ደዉለዉ መጠየቅ ይችላሉ

**የጊ/ወ/ፋ/ጽ/ቤት**